## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አራት (4)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የለውጥና የግንኙነት ደረጃዎችን ምንነት ከዚህ መጽሐፍ ሐሳብ በመነሳት አብራሩ፡፡
2. በመጽሐፉ የተጠቀሱና ከዚያም ባሻገር በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ ለውጦችን በመጥቀስ በስፋትና በግልጥነት ተወያዩ፡፡
3. በመጀመሪያ በአንተ/ች/ ከዚያም በትዳር አጋርህ/ሽ/ ያስተዋላችሁት ለውጥ ምንድን ነው? ለውጡ በእያንዳንዳችሁ ላይ የፈጠረው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ አለን? ካለስ ምንድን ነው?
4. የአምስቱን የግንኙነት ደረጃዎች ባሕርያትን በመዘርዘር የትዳር ግንኙነታችሁ በየትኛው ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ የሚያስችል ግልጽና በቂ ውይይት አካሂዱ፡- ለአንድ አፍታ ወደ ኋላ ዘወር በማለት የጫጉላ ቤት ጊዜያችሁን እንዴት እንዳሳለፋችሁና ዛሬ ላይ የደረሳችሁበትን የግንኙነት ሂደት በቅኝት መልክ በመዳሰስ ተነጋገሩበት፡፡
5. እውነታን በምትጋፈጡበት ደረጃና ልጆች ትኩረታችሁን በሚወስዱበት ወቅት እንዴት የትዳር ግንኙነትን ሚዛን መጠበቅ እንደቻላችሁ ምክክር አድርጉ፡፡
6. ዛሬ ላይ በመቆም በትዳር ሕይወታችሁ ከገጠሟችሁ የተለያዩ ግጭቶች በመነሳት በምርጫችሁና በውሳኔያችሁ ላይ የተፈጠረውን የተለያየ ስሜትና ድባብ በመግለጽ ልምምዳችሁን ተከፋፈሉ፡፡





# ምዕራፍ አምስት(5)

# በጋራ መወሰን (ውሳኔ አሰጣጥ)

## I. በጋራ የመወሰን ምንነት

ጥንዶቹ በትዳር ሕይወታቸው፣ በኑሯቸውና በቤተሰባቸው የተለያዩ ምርጫዎችንና ውሳኔዎችን ጠያቂ የሆኑ የጋራ ጉዳዮች ላይ የመነጋገር፣ የመመካከር፣ አንዱ ለሌላው ጥቅም፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ማንነት የመጠንቀቅ ልምድ ሊኖራቸው ይገባል። በጥንዶች የትዳር ሕይወት በጋራ መወሰን ማለት የጋራ ውሳኔ የሚያሻቸው ጉዳዮችን፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎችን እንዲሁም የቤተሰቡን የዛሬና የወደፊት ሁኔታ የሚመለከቱ የምርጫና የውሳኔ ሂደቶችን የእግዚአብሔርን ቃል መርህ መሠረት ባደረገ እንዲሁም ለቤተሰቡ መታነጽ በሚያመጣ መንገድ በመምራት በጋራ ከመወሰን ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎችንና የመፍትሔ አሳቦችን አስቀድመው የማሰብና ትዳራቸውን አብረው የመገንባት የሁለትዮሽ ኃላፊነታቸውን የመወጣት ሂደት ነው፡፡

በዚህ ርዕስ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈለገው ጥንዶች በመከራከር ሳይሆን በጋራ በመመካከር፣ በመደፋፈር ሳይሆን እርስ በእርስ በመከባበር እና በግጭት ሳይሆን በስምምነት አብረው መወሰንን እንዲለማመዱና የትዳር ግንኙነታቸውና የቤተሰባቸው ጤንነት እንዲጠበቅ ለመጠቆምና ለመርዳት በማሰብ ነው። በጥንዶች ሕይወት ትዳር የጋራ ውሳኔ በሚጠይቁ ምርጫዎችና ገጠመኞች የተገነባ ኑሮ ነው። ይህ እውነት የጥንዶችን በትዳር ሕይወታቸው በገጠማቸውና ሊገጥማቸው ባለ የጋራ ጉዳይ ላይ አስፈላጊነቱን፣ አንገብጋቢነቱንና አስቸኳይነቱን በሚመለከት እርስ በርስ በመነጋገር፣ በመመካከርና በመስማማት ወደ አንድ ውሳኔ የመምጣትን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው። ጥንዶች ለጋራ ጉዳይ በጋራ ለመወሰን አብረው ቢቀመጡና ቢነጋገሩ በሁሉ ነገር ይስማማሉ ወይም መስማማት አለባቸው ማለት ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ግጭት አልባ በሆነ አለመስማማት ተስማምተው ልዩነትን በሰላም እያስተናዱ የትዳርን ግንኙነት ጤናማነትና የጋራ ደስታን ግን ለመጠበቅ መትጋት ይኖርባቸዋል።

**የጋራ ውሳኔዎችን በመከራከር ሳይሆን በመመካከር፣ በመደፋፈር ሳይሆን በመከባበር እንዲሁም በግጭት ሳይሆን በስምምነት ለመወሰን ጥረት እናድርግ።**

## II. በጋራ የመወሰን አስፈላጊነት

ሕይወት ምርጫና ውሳኔ የበዛባት ጉዞ ናት። በምርጫችንና በውሳኔያችንም ተጠያቂዎች እኛው ሰዎች ራሳችን ነን! እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ነጻ ፈቃድ ያለው፣ የወደደውን የመምረጥ ችሎታ ያለውና ደግሞም በመረጠው ምርጫ ሊጠየቅ የሚችል

አድርጎ እንደፈጠረው ገና ከፍጥረት ጅማሬ መመልከት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ **በዘፍ 2፡ 16-17** *"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፦ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።"* ብሎ በመናገር በምርጫውና በውሳኔው ተጠያቂ ፍጡር እንደሆነ ግልጥ ያደርግልናል፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ላይ አዳምና ሔዋን በእባብ የሐሰት ቃል በመታለል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትተው የራሳቸውን ምርጫና ውሳኔ በመከተላቸው በውጤቱ ተጠያቂ ሆነዋል፡፡

ምርጫና ውሳኔ በግለሰቦች የግል ሕይወት የሚከሰት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በትዳር በተጣመሩ ባለትዳሮች መካከልም የሚፈጠር የትዳር ጉዞ ቋሚ ገጽታ ነው። ጋብቻ በየግል የራሳቸውን ኑሮ ሲመሩና በየግላቸው ሲመርጡና ሲወስኑ የነበሩ ሁለት ተቃራኒ ጾታ ያላቸው ሰዎች በፍቅር ተዋደው በጋራ ለጋራ የትዳር ሕይወታቸው በመስማማት የሚወስኑበት ተቋም ነው። ሰው አባትና እናቱን በመተው ከሚስቱ ጋር የሚተባበር መሆኑ የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጽሐፈት ትምህርት ነው። **በዘፍ 2፡ 24** የተነገረው *"...ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* የሚለው የእግዚአብሔር ንግግር **በማቴ 19፡ 15** የተገለጠው *"... ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"* የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስ ለጠያቂዎቹ የሰጠው መልስ እና የጥንቷ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች የነሐዋሪያው ጳውሎስ ጋብቻን በሚመለከት *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /**ኤፌ 5፡ 31**/ በማለት የሰጧቸው መመሪያዎች ባል እና ሚስት ግላዊ ምርጫወቻቸውንና ውሳኔዎቻቸውን በመተው በጋራ ለመኖር የሚበጃቸውን ጉዳይ አብረው ለመምረጥና ውሳኔ ለመወሰን ጋብቻ የሚባለውን ተቋም የመሠረቱ ወይም የሚመሠርቱ መሆኑን በግልጥ የሚያረጋግጡ መርሆዎች ናቸው፡፡

ከጫጉላ ጊዜ እስከ መጀመሪያው አስር ዓመት የጋብቻ ዘመን የሚገኙ ባለትዳሮች ባብዛኛው የጋራ የትዳርና የቤተሰብ ማሕበራዊ ሕይወት ጉዳዮችን አብረው መምረጥና መወሰን ሲገባቸው በግል ወደ መወሰን የሚያዘነብሉ በመሆናቸው በትዳር ላይ አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት ይፈጠራል። ጊዜያቸውን በአግባቡ ለሚጠቀሙ ተጋቢዎች ዕድሜና ቆይታ ለእድገታቸውና ለብስለታቸው ገንቢ አስተዋጾ አለው። ይህ እውነታ ግን እንደ ባለትዳሮች የጋብቻ ዘመን እንዲሁም ከገጠመኞቻቸው የመማርና የመለወጥ አቅምና ችሎታ መጠን የተለያየ ይሆናል፡፡ ይህንን ባለመረዳትም በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች በጋራ መወሰንን አይለማመዱም፡፡ በዚህም ምክንያት ትዳራቸው ግጭት የበዛበት ይሆናል፡፡ ጥንዶች ግራ ተጋብተውም፦ " ምክንያቱ ምንድን ነው? ችግሩ የግል (የአንድ ሰው) ትዳር ብቻ ነው ወይስ የሌሎችም ሰዎች? በእኛ ቤት የትኛው ችግር ጎልቶ ይታያል? ችግሩስ እያመጣ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ምንስ ብናደርግ ጤነኛ ግንኙነት ያለን ደስተኛ ጥንዶች ልንሆን እንችላለን?..." የሚሉ መሠረታዊ





ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ፡፡ ለእነዚህ ጥያቄዎቻቸውም ምላሽ ማግኘት ይገባቸዋል። የችግሮቻቸው መሠረታዊ መነሻ በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ማንኛውንም ጉዳይ በመመካከር፣ በመግባባትና ስምምነት ላይ በመድረስ አብረው መወሰን አለመቻላቸው ነው፡፡

በአንድ ቤት ውስጥ በየግል መኖርን በመቀነስ በጋራ ማሰብን፣ መመካከርንና ማንኛውንም የትዳር ጉዳይ በጋራ የመወሰንን አስፈላጊነት ተረድተው የመተግበር ልምድ በቤታቸው ውስጥ እንዲኖር ማድረግና ራሳቸውን ለዚህ መርህ በቋሚነት ማስገዛት ይገባቸዋል፡፡ በብስለት በዚህ መርህ መሠረት መኖርን ሲለማመዱ ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ይፈታሉ፡፡ ጥያቄዎቻቸውንም በአግባቡ ይመልሳሉ፡፡ በሚቀጥለው ርዕስ ውስጥ የሚዳሰሱ አሳቦች በዚህ ሁኔታ ላይ ባልና ሚስት የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያግዟቸዋል።

## III. በጋራ በመወሰን ሂደት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

### 1. ሳይነጋገሩ በየግል መወሰን

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከውሳኔ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር አንደኛው ችግር ጥንዶቹ በትዳራቸውና ከትዳራቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሳይወያዩ ብቻቸውን መወሰናቸው ነው። እንግዳ መጋበዝ፣ ከፍተኛ ገንዘብ ወጭ ማድረግ፣ ቤተሰብንና ሌሎችን ሰዎች መርዳት፣ ወደ ሌላ አገር መሄድ የመሳሰሉ የጋራ ውሳኔን የሚጠይቁ ጉዳዮችን በግል ተነሳሽነትና ውሳኔ ብቻ የመፈጸም ዝንባሌ ከጥንዶቹ አንደኛው ያላቸው ከሆነና ይህንንም ወደ መተግበር የሚያመሩ ከሆነ በጋራ የመወሰን ሂደት ላይ ችግር ይፈጠራል።

እንዲህ ዓይነቱ በግል የመወሰን ዝንባሌና ተግባር ሊፈጠር ከሚችልባቸው ምክንያቶች መካከል **አንደኛው** ከማግባታችን በፊት ራሳችንን በራሳችን ስናስተዳድርና ውሳኔወቻችንንም በግላችን ስንወስን የነበረ መሆኑ ነው። ይህ ቅድመ ጋብቻ ላይ የነበረ የግል ልምምድ አሁንም በትዳር ላይ መቀጠሉ የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ነው። ብዙ ዓመት አብሮን የቆየና የእኛ የሆነን ልምምድ በአንድ ጊዜ ለመተው መሞከር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ የግለኝነት ልምምድ አብሮን ከቀጠለ ደግሞ በትዳራችን ውስጥ ችግር ይፈጥራል። ስለዚህ በእርጋታ አስበንበት መለወጥ በምንችልበት መንገድ ላይ በትጋት ለውጡን በሕይወታችን እስክናይ ድረስ ራሳችንን ለማሻሻል መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

ሌላው **ሁለተኛው** ምክንያት ደግሞ የባልና የሚስት እይታ ልዩነት ነው፡፡ ሰው በሕይወቱ ውስጥ ዋጋ የሚሰጠው እሴትና ነገሮችን የሚያይበት አስተሳሰብ የተለያየ ነው። አንዱ ምናለበት ሲል ሌላው ችግር አለበት ይላል፡፡ አንዱ ነገር ሲያቃልል ሌላው ያካብዳል፡፡ አንዱ ውጤቱ ላይ ሲያተኩር ሌላው ሂደቱ ላይ በማተኮር በግልና በጋራ መወሰን አለብን የሚሉ ትግሎች በባለትዳሮች መካከል ይፈጠራሉ። በጋራ ለመወሰን የግድ አንድ ዓይነት ሰዎች ልንሆን ወይም አንድ ዓይነት እይታና ባሕርይ ሊኖረን

አይገባም፡፡ ሊኖረንም አይችልም!! ነገር ግን በትዳር ሕይወታችን ጉዳዮችን ከተለያየ እይታ አንጻር በማየት፣ በጋራ በመወያየት፣ በጋራ በመተማመን፣ እንዲሁም ባለመስማማትና በመስማማት በጋራ እየወሰንን መተግበር ወደ ትዳር ስንገባ ልንኖርበት የተቀበልነው የጋብቻ ሕይወት መርህ ነው። በዚህ መርህ ደግሞ ልንኖርበትም ይገባል።

## 2. በግል ተወስኖ ሊፈጸም ያለን ጉዳይ ትክክለኛ በሆነ ጊዜ አለማሳወቅ

ሌላው ከሚፈጠሩት ችግሮች መካከል አንዱ በግል ተወስኖ ሊፈጸም ያለን ጉዳይ በጊዜው አለማሳወቅ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ስናል በሕይወታችን ጊዜ የማይሰጥ ምርጫና ውሳኔ ሊያጋጥመንና ፈጣን ውሳኔ እንድንወስን ልንገደድ እንችላለን። ነገር ግን ውሳኔውን ከወሰንን በኋላ ጊዜ ስናገኝ ለምንና እንዴት ውሳኔውን እንደወሰንን በእርጋታ በማብራራት ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ለትዳር አጋራችን መግለጥ ይኖርብናል። ይህንን በጊዜው ሳናደርግ ከቀረን ወይም ደግሞ ጉዳዩ ጊዜ ሰጭና የትዳር አጋርን ምክር፣ አስተያየት፣ ስምምነትና ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ ሳለ እንዲሁ በማን አለብኝነት በግል ወስነንና አከናውነን ጊዜው ካለፈ በኋላ ወይም ሌላ ሁኔታን በመጠቀምና በእግረ መንገድ አጋጣሚወች እንዲሰሙና እንዲያውቁ ማድረግ የግጭት ምክንያት መሆኑ አይቀሬ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር አንዳንድ ጊዜ ሊፈጠር የሚችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ከሆነ አለማወቅ፣ አለመልመድ፣ መርሳትና ለነገሩ ክብደት አለመስጠት የችግሩ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነቱን ስህተት በእርጋታ ከተነጋገሩ በግል የወሰነው አካል በመደንገጥና ስህተቱን በመረዳት ወደ ፊት በውሳኔው የትዳር አጋርን የማካተት እርምጃ እንዲወስድ ይገደዳል።ከዚህ ውጭ የሆነ ሃሳብና እንቅስቃሴ ለግጭት መንስኤና ማባባሻ ሊሆን ስለሚችል ጉዳዩ በጥንቃቄና በብስለት ሊያዝ ይገባል።

ሌላው መጠቀስ ያለበት ከባህላችን አንጻር የሴት ልጅን ሃሳብ ዝቅ አድርጎ በማየት ሚስቶችን በውሳኔ ላይ የአለማሳተፍ ችግር ነው፡፡ በውሳኔ ሰጭነት እንዲሳተፉ እድል አለማግኘት ብቻ ሳይሆን ስለተወሰነው ነገር ምንም የማያውቁ የትዳር አጋሮች የተደረጉ ሚስቶች ቁጥር ጥቂት አይደለም። ይህ ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የአንዳንድ ወንድሞች አመለካከት ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ውጭና የሰለጠኑ በሚባሉ አገሮች የሚኖሩ የአንዳንድ ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወንዶችም የሚጋሩት ችግር ነው።

ለሴት ልጅ ያለንን ዝቅተኛ አመለካከት አስወግደን በትዳራችን ያለእነርሱ ተሳትፎ ትዳርንና ቤተሰብን በጠንካራና ጤናማ መሠረት ላይ ማቆም ፈጽሞ የማይቻል መሆኑን በመገንዘብ በውሳኔ ሰጭነት ተግባር ላይ በእኩልነት ማሳተፍ መጀመርና አብሮ ወደ መወሰን መምጣት ተገቢ ነው። እንዲያውም ለሚፈጠሩ ችግሮች ሴቶች ከወንዶች የተሻለ የመፍትሔ ሃሳብ የማፍለቅ ተፈጥሮ እንዳላቸው በመገንዘብ በውሳኔ ሰጭነትና በመፍትሄ አምጭነት ለትዳራቸው ምትክ የለሹን ሚናቸውን እንዲያበረክቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የባሎች ኃላፊነትና ግዴታ ነው።





ሌላው ከጾታና ከባህል በዘለለ በትዳር የተጣመርን ጥንዶች አንዳችን ከሌላችን እንበልጣለን ብለን የምናስብባቸው ልምምዶች፣ እውቀቶች፣ ችሎታዎችና ጠንካራ ጎኖች በትዳር ሕይወት ውሳኔዎች ላይ አንዱ ሌላውን እንዳያሳትፍ የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው፡፡ በየትኛውም ደረጃ ከትዳር አጋራችን የምንሻልባቸው ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩንም ሁል ጊዜም የትዳር አጋሮቻችን ደግሞ ከእኛ የሚሻሉባቸው ጠንካራ ጎኖች ይኖሯቸዋል፡ ፡ እነዚህን ቁም ነገሮች አለማወቅና ለማወቅም ዕድል የማይሰጡ መሆን ሌላኛው በትዳር ውስጥ የሚከሰት አደገኛ ችግር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ *"በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ ሊታድርጉ፥ ነገር ግን ሊያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤"* /ፊል 2፡ 2-3/ በማለትና የኢየሱስ ክርስቶስን የሕይወት ምሳሌ በመጥቀስ ትህትና እንድንማር ይመክረናል። ከትዳር አጋሮቻችን የምንበልጥበትና የምንሻልበት

**ከትዳር አጋሮቻችን የምንሻልበትና የምንበልጥበት ጉዳይ እንዳለ ቢሰማንና ብናምንም የተሻለና የሚበልጥ ጉዳይ ከትዳር አጋሮቻችንም ዘንድም እንዳለ ማሰብ፣ ማወቅና ማመን ያስፈልገናል።**

ጉዳይ እንዳለ ቢሰማንና ብናምንም እንኳን ሐቁ ግን የተሻለና የሚበልጥ ጉዳይ ከትዳር አጋሮቻችንም ዘንድ እንዳለ ማሰብ፣ ማወቅና ማመን አስፈላጊ መሆኑ ነው።

## 3. የራስ ፍላጎትና አሳብ ብቻ እንዲፈጸም ጥረት ማድረግ

በጋብቻ ውስጥ የትዳር አጋርን ሳያሳትፉ በግል ከመወሰን ጋር በተያያዘ በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የሚታይ ሌላው ችግር የራስ ፍላጎትና አሳብ ብቻ እንዲፈጸም ጥረት ማድረግ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ችግር ሊፈጠር የሚችለው እንዲፈጸም በምንፈልገው ጉዳይ ይበልጥ ተጠቃሚ እንሆናለን ብለን ስናስብ ነው፡፡ ከመሸነፍ ይልቅ ማሸነፍ፣ ከመታዘዝ ይልቅ ማዘዝና ሌሎች ተኮር ከመሆን ይልቅ ራስ ወዳድ መሆን በአስተዳደጋችን ሁልጊዜ ትክክል ናችሁ እየተባልንና ሁልጊዜ በማሸነፍ ብቻ የምንታወቅ ሁነን በማደጋችን የሚመጣ ችግርም ሊሆን ይችላል፡፡ በየትኛውም መንገድ የመጣ ይሁን ችግሩ በሕይወታችን ካለ ለዛሬው የትዳር ሕይወት ትግል ምክንያት ይሆናል። ሌላው አንዳንዶቻችን የየግላችንን ፍላጎት፣ ሃሳብ፣ ምርጫና ውሳኔ መተው ወይም መልቀቅ የሚባል ጽንሰ አሳብ የሌለን ሁነን ማደጋችንና መኖራችን ለችግሩ መከሰት ከፍተኛ አስተዋጾ አለው።

ወደ ትዳር ከመግባታቸው በፊት አንዳንድ ሰዎች እኔ ብቻ ትክክልና አዋቂ ነኝ ወይም የሌሎች ሰዎች ምንም አስተዋጽኦ የማያስፈልገኝ ብቻየን በቂ ነኝ የሚል ከፉ የእኔነት በሽታ የተጠናወታቸው ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ለእኔ በቂ የሚሆን የትዳር አጋር የለም እያሉ የራሳቸውን ዋጋ ከፍ የሚያደርጉና ሌሎችን የሚያጣጥሉ ናቸው፡፡ ምናልባትም በእጮኝነት ጊዜያቸው በዚህ አስቸጋሪ ባህሪያቸው ምክንያት ብዙ

ጊዜ በግጭት ውስጥ የሚያልፉና በጓደኞቻቸው ወደፊት ይለወጣሉ በሚል ሰበብና ተስፋ የታለፉ ሊሆኑ ይችላሉ። በአገልግሎት ቢሮየ ውስጥ ባለትዳሮችን በማማከርበት ወቅት ወደ ኋላ ያለፈ የልጅነት አስተዳደጋቸውንና የእጮኝነት ጊዜያቸውን በመጠየቅ ችግሩ የቆየ መሆኑን ለማወቅ በጥያቄና መልስ ለመረዳት ጥረት አደርጋለሁ። አንዳንዶችም ይለወጣል (ትለወጣለች) በሚል ተስፋ ተቀባይነት ያገኙ ስለሆኑ እንጂ ከበፊትም ችግር የነበረባቸው ናቸው፡፡ በዚህ ችግር ምክንያት እጮኝነታችን ፈርሶ ነበር ሌሎች ሰዎች ታገሳት (ታገሺው) በማለት ገፋፍተው ለዚህ ከፍተኛ ችግር ዳረጉኝ እንጅ የሚሉ ጥንዶች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

ትዳር ማለት የራሣችንን ፍላጎትና ጥቅም የምናስጠብቅበት መድረክ ሳይሆን ለትዳር አጋራችን መልካም ፍላጎት ሙላት ሆነን የምንኖርበት ተቋም ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና የጳውሎስ ትምህርት እንዲህ የሚል ነው፡- *"እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፥" /ፊል 2፡ 4-6/*፡፡ ይህን እውነት መሰረት ባደረገ የሕይወት መስጠት ለራሳችን ፍላጎት ሳይሆን ለሌላው ጥቅም የመኖርን ክርስቶስ መሰል ሕይወት

> **ትዳር ማለት የራሳችንን ፍላጎትና ጥቅም የምናስጠብቅበት መድረክ ሳይሆን ለትዳር አጋራችን መልካም ፍላጎት ሙላት ሆነን የምንኖርበት ተቋም ነው!**

የምንኖርበት የመጀመሪያው መኖሪያችን ትዳር (ቤተሰብ) ነው፡፡ ይህን የሕይወት መርህ መመሪያችን ካደረግን ቤታችን በመግባባትና በሰላም ይሞላል፡፡ የዚህን ሕይወት ተቃራኒ በመምረጥ ራስ ተኮር ከሆንን ግን ከትዳር ጓደኛችን ጋር ያለን ሕብረት የጦርነት መደ መሆን ይቀየራል፡፡ ራስ ወዳድነት ባለበት የትዳር ግንኙነት ውስጥ ሁልጊዜም አለመግባባት፣ ግጭትና መለያየት መኖሩ ደግሞ አይቀሬ ነው።

## 4. ከጋብቻ በፊት በውሳኔ ሲረዷቸው የነበሩ ሰዎችን ጣልቃ ማስገባት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል በውሳኔ ሂደት ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱም ወደ ጋብቻ ሕይወት ከመግባታቸው በፊት በተለያዩ የኑሮ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሲወስኑ ይረዷቸው የነበሩ ሰዎችን በትዳር ውስጥ ጣልቃ ማስገባታቸው ነው። ከአሁን በፊት ይረዷቸው በነበሩ ሰዎች ላይ ያላቸው ከፍተኛ የሆነ እምኔታ አሁንም ያለእነርሱ መወሰን የማይችሉ ጥገኛ ሰዎች እንዲሆኑ ስላደረጋቸው በየጊዜው ምርጫና ውሳኔ በሚፈልጉ ጉዳዮች ጣልቃ እንዲገቡ ዕድል መስጠት ይጀምራሉ። እነዚህ ውሳኔ በመወሰን ሂደት ድጋፍ ይሰጡ የነበሩ ሰዎች የቤተሰብና የቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ወዳጆች፣ አገልጋዮችና አማካሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።





በውሳኔ የሚረዱ ሰዎችን መፈለግ ብልህነት ቢሆንም የምናማክራቸው ሰዎች እንዲመርጡልንና እንዲወስኑልን መፍቀድ ግን ሰው መሆንን ትተን ስብእናችንን ሌሎች ሰዎች የሚያንቀሳቅሱን ሮቦቶች ለመሆን አሳልፈን መስጠት ነው። እኛ የሚያውቁ፣ የሚያስቡ፣ የሚያመዛዝኑና ውሳኔ ማሳለፍ የሚችል በቃት ያላቸው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠሩ ሰዎች ነን፡፡ ስለዚህ ያለ አማካሪዎቻችን የማንተነፍስ እስክንሆን ድረስ በእነርሱ መተማመንና መደገፍ የለብንም። አማካሪዎችና ድጋፍ ሰጭዎች በአስፈላጊ ጊዜ ለውሳኔ የሚረዳ አሳብ በማፍለቅ በጋራ የመፍትሔ አሳብ የሚያፈላልጉና ውሳኔውን ለእኛ የሚተውሉን መሆን መቻል አለባቸው። አማካሪዎችም የምናማክራቸውን ሰዎች ያለእኛ የማይንቀሳቀሱ ሁልጊዜ በእኛ ተረጅና ጥገኛ ሰዎች ልናደርጋቸው አይገባም። አንድ ወቅት ላይ የማማከር አገልግሎታችን ሊያቆም ይገባል። ባለትዳሮች በራሳቸው እንዲቆሙና ለችግሮቻቸው ራሳቸው እንደ ባለትዳር ተነጋግረው መፍትሔ እንዲያፈላልጉ መፍቀድና መንገዱን ማሳየት መቻል አለብን።

ከጋብቻ በፊትና በትዳር ሕይወት ውስጥ ሁነው በየጊዜው ስልክ እየደወሉ፣ በአካል እየተገናኙ ምክር መጠየቅ አስፈላጊ ቢሆንም የሚያማክሩንን ሰዎች ምስክርነት፣ ማረጋገጫ፣ ተቀባይነትና አስተያየት ሳንሰማ አለመወሰን ሌላ አደገኛ ችግር ነው። እንደ ባለትዳር በአንድ ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ስለዚህ ጉዳይ እነርሱ ምን ይላሉ? እነርሱ ምንም ካላሉ ምንም እርምጃ መውሰድ የለብንም፣ እነርሱ አልተስማሙበትም... የሚሉ የተለያዩ ባሎችና ሚስቶች በጋራ ተነጋግረው ውሳኔ መወሰን እንዳይችሉ ድፍረታቸውን የሚያስጥሉና ግንኙነትን ሊያሻክሩ የሚችሉ ልምዶች በተለይ በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች የሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች ናቸው። እነዚህን ተግዳሮቶች በመቀነስ ለችግሮች በመረዳዳትና በጋራ መፍትሔ እያፈላለጉ ጤነኛ ግንኙነት ያለውና ደስተኛ የሆነ የትዳር ሕይወት ለመኖር መትጋት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

## IV. በጋራ በመወሰን ላይ ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. *መቀመጥ፡-* በጋራ ለመወያየትና ለመጸለይ መቀመጥ

በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች ባልና ሚስት ተገቢ ውይይት አድርገውባቸው በስምምነት ሊወስኑ ይገባል፡፡ ወደ ትክክለኛ ውሳኔ የሚያደርስ ገንቢ ውይይት ማካሄድ የሚቻለው ደግሞ ጥንዶቹ የጋራ ጊዜ ኖሯቸው አብረው መቆየት ሲችሉ ነው፡፡ ስለዚህ ባለትዳሮች የትዳራቸውን ሰላም፣ መልካም ኅብረትና የሕይወት ዘመን እግዚአብሔርን አክባሪ ስኬታማ ጉዞ እንዲኖራቸው አብረው ለመጸለይና ለመወያየት በመቀመጥ የጋራ ጊዜ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ባለትዳሮች በጋራ በምንቀመጥበት ወይም የጋራ ጊዜ በምንወስድበት ወቅት መጠንቀቅና ራሳችንን መፈተሽ ያለብን የውስጥ መነሻ አሳባችን ላይ ነው። በጋራ በምንቀመጥበት ጊዜ በጉዳዮቻችን ላይ ትኩረት አድርገን ያሰብነውን ለመፈጸም እንዳንችል ነጻነት የሚነፍጉ ጉዳዮችን ማስወገድ አስፈላጊ ነው። ለመወያየትና ለመመካከር የምንቀመጠው

በማሸነፍና በመሸነፍ፣ በፍርሃትና በጭንቀት፣ በከርክር፣ በጠብና በቁጣ መንፈስ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል:: ላለመስማማት ራስን አዘጋጅቶና ዝግ አድርጎ ከመምጣትና ከመቅረብ ራስን ማጽዳት በጋራ ተቀምጦ ለመወያየት፣ ለመጸለይና የተለያዩ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦችን በነጻነት ለማንሸራሸር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

## 2. መግለጥ፡- ውሳኔ የሚጠይቀውን ጉዳይ መግለጥ

ግልጥነቱ ይበልጥ እንዲታወቅና እንዲጎላ ውሳኔ የሚፈልገው ርዕሰ ጉዳይ አስፈላጊነት ላይ ተወያይቶ መተማመን የሚኖረው ገንቢ ስተዋጽኦ አጠያያቂ አይደለም። አሳቡን ወይም ችግሩን በግልጥነት ማስቀመጥ ለመግባባትና ወደ አንድ ውሳኔ ለመድረስ የሚሰጠው እገዛ ቀላል አይደለም። ለትዳር ግንኙንታችን የሚሰጠውን ጠቀሜታ ማንሳት ብቻ ሳይሆን አስቸኳይነቱንና አንገብጋቢነቱን ጭምር መግለጽ ይበልጥ በጋራ የመወሰን እድሉን ከፍ ያደርገዋል። ነገሮችን ከብዙ አቅጣጫ በመመዘንና በመመልከት ለትዳራችንና ለቤተሰባችን የትኛው ይበልጥ ይጠቅማል? ጥቅሙ ወይስ ጉዳቱ ያመዝናል? የትኛውስ ቢቀድም መልካም ነው? በማለት የተለያዩ አማራጭ የመፍትሔ አሳቦችን በማቅረብ ለትዳር ግንኙነታችን የሚበልጠውን በጋራ ተስማምቶ ለመወሰን የምንችለውን ሁሉ ጥረት ማድረግ ቤተሰባችንን በመተማመንና በነፃነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያስችለዋል።

## 3. መመከር፡- ለትክክለኛና ጽድቅ ለተሞላው ውሳኔ በእግዚአብሔር ቃል መመከር

ስለእያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳዮቻችን ከእግዚአብሔር ቃል ቀጥተኛ ጥቅስ ልናገኝላቸው አንችልም! ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላል? እየተጓዝን ያለነው ጽድቅ በሞላበት አካሄድ ነው ወይስ በአመጽ? ይህ ጉዳይ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል ወይስ ያሳዝናል? ያሰብነው ሃሳብ ትዳራችንን የሚደግፍ ነው ወይስ የሚያፈርስ? ውሳኔያችን የእኛ የግል ፍላጎት ብቻ ነው ወይስ በእግዚአብሔር ቃልም የተደገፈ ነው? የሚሉ የተለያዩ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መመካከር አስፈላጊ ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስንመካከር ለቃሉ ለመሸነፍና ለመታዘዝ እንጂ ቃሉን ወደ ምንፈልገው ወደ ራሳችን የግል ፍላጎት ማስፈጸሚያነት ለመጠምዘዝ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገናል /2ኛጢሞ 3:16/።

## 4. መውሰድ፡- በቁጣና በስሜት ውሳኔ እንዳንወስን አስቀድሞ በቂ ጊዜ መውሰድ

በቁጣና የእኔ አሳብ ብቻ ይፈጸም በሚል ጭፍን ስሜት ውሳኔ እንዳንወስን ውጥረቶችን በማለዘብና የእኛን የውስጠኛ መነሻ አሳብ ለመፈትሸና ለመመዘን በቂ ጊዜ በመውሰድ ውሳኔን ለመወሰን ዝግጁ መሆን በትዳር ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ግብዓቶች አንዱ ነው:: ይህን ማድረጋችን ተጸጽተን ነገሮችን በመተው፣ በይቅርታና በሰላም ለትዳር አጋሮቻችንና ለቤተሰቦቻችን እንድናስብ ዕድል ይሰጠናል። በጊዜው





በርዕሰ ጉዳዮቻችን ላይ መስማማት ካቃተን የግድ ዛሬ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ የሚለውን የሞኞች ችኩልነት በመተው በጥሩ ልብና በተረጋጋ ስሜት የተሻለ የውሳኔ አሳብ መፍለቅ እንዲችል እስኪ በሌላ ጊዜ፣ በሚቀጥለው ቀን፣ ሳምንት... በዚህ ጉዳይ ላይ እንመለስበት በሚል ስምምነት ቀጠሮ ሰጥተነው በሂደት ነገሮችን መቃኘቱ ብልህነት እንጂ ተሸናፊነት አይደለም!! ከብዙ አቅጣጫ ነገሩን ለማየት ማለትም ለማሰብ፣ ለመጸለይ፣ ሌሎችን ሰዎች ለማማከርና የሌሎችን ልምምድ ለመጠየቅ ጊዜ መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ጊዜ መስጠት ዛሬ በጭፍን የወሰንነው ጉዳያችን ነገ እንዳይጸጽተን፣ ቀላሉ ነገር ውስብስብ እንዳይሆን፣ ለትዳራችን ጥቅምና ሰላም የፈለግነው ጉዳይ ሰላም የሚነሳንና ልብ የሚያሳዝን ብሎም ለመለያየት በር ከፋች እንዳይሆን ከወዲሁ ተረጋግቶ በሰከነ ስሜትና በትዕግስት ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚረዳን አስፈላጊ እርምጃ ነው።

## 5. መፈለግ፡- በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ድጋፍ የሚያደርጉልን አማካሪዎችን በጋራ መፈለግ

ለውሳኔ ያቀረብነው ወይም እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚጠይቅ በሚሆንበት ጊዜ የሌሎች ሰዎች ምክር፣ ተሞክሮና ድጋፍ የሚያስፈልግ ሊሆን ይችላል። ምናልባት የምንነጋገርባቸውና ውሳኔ የምንፈልግባቸው ጉዳዮች ልጅ መውለድና ማሳደግ፣ የለመድነውን አገር ወይም አካባቢ መልቀቅና ወደ ሌላ አገር መሄድ፣ ሥራ መቀየር፣ የጤንነትና የሕክምና ጉዳይ ላይ መፍትሄ መሻት፣ አገልግሎት፣ ከፍተኛ የገንዘብ ወጭ የሚጠይቅ ፕሮጀክት... ሊሆኑ ይችላሉ። እንደነዚህ ዓይነት ታላላቅ ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ከመወሰናችን በፊት ከትምህርት፣ ከመንፈሳዊነት፣ ከሙያና ከልምድ አንጻር የሚመከሩንና አቅጣጫ የሚያሳዩን ባለሙያ ሰዎች ያስፈልጉናል።

ሌሎችን ሰዎች ማማከር ማለት ሽንፈት፣ አላዋቂነት፣ ገመናን አውጥቶ ማሳየት፣ እንዲሁ በከንቱ ጊዜ ማጥፋት እና ሌሎች ሰዎች ውሳኔውን እንዲወስኑልን ማድረግ አይደለም ነገር ግን እኛ ያላየነውን፣ የማናውቀውን እና የሌለንን የተለያየ ሃሳብና መረጃ ከሌሎች በመቀበል ለውሳኔ እንድንደረስ በአማካሪዎች መረዳት ነው:: እንዲህ ዓይነት እርዳታ በሚያስፈልገን ጊዜ ወደ ትክክለኛ አማካሪዎች በመሄድ ድጋፋቸውን መጠየቅ ጠቃሚና ምትክ የማይገኝለት ትልቅ አስተዋጾ እንደሆነ ልንገነዘብ ይገባል። ይህ ሲሆን በጋራ በመስማማት ካልሆነ በስተቀር አማካሪ መፈለግ አንድ ጉዳይ ሆኖ እያለ እነማን ይሁኑ፣ ምን ዓይነት ሙያና ልምድ ያላቸው፣ መቼና እንዴት የሚሉ ሌሎች አነጋጋሪና ስምምነት ጠያቂ ጉዳዮች መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም። በተቻለ መጠን ለጋራ የትዳር ሕይወት በጋራ ማሰብ፣ መወያየትና የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ተግቢ ነው።

በባለትዳሮች መካከል የተለያዩ ቀውሶች መፈጠራቸው አይቀሬ ነው። እነዚህን በትዳር ውስጥ የሚያጋጥሙ የተለያዩ ለግጭት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ክስተቶች በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። ***የመጀመሪያዎቹ*** ያልተጠበቁ የሕይወት ክስተቶች

(ገጠመኞች) ናቸው። ገጠመኞቻችን በሰው ሕይወት ሲከሰቱ የነበሩና አሁንም የሚከሰቱ ቢሆኑም ያልተጠበቁ ገጠመኞች ያልናቸው ያልጠበቅናቸው ክስተቶች ስለሆኑ ነው። እነዚህ ክስተቶች ውርጃ (ጭንገፋ)፣ ሕመም፣ ድብርት፣ የተለያዩ አደጋዎች፣ የሚወዱት የቤተሰብ አባል በድንገተኛ ሞት መለየት፣ ኢኮኖሚያዊ ክስረትና ሌሎችም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

**ሁለተኛዎቹ** የሚጠበቁ ክስተቶች ናቸው። የሰው ልጅ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። በወሊድና በእድገት ወቅት ደግሞ የሚከናወኑ ብዙ የሕይወት ውጣ ውረዶች መኖራቸው ይታወቃል። በባለትዳሮች መካከል ራሳቸው ጥንዶችም ሆኑ ቤተሰብና ሌላው ሰው የሚጠብቋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ልጅ መውለድ፣ የልጆች እድገትና ትምህርት ቤት መግባት እና ቀጣይ እድገታቸው የሚያመጣቸው ለውጦች ከሚጠበቁ ክስተቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ለውጦች ተከትሎ በትዳር ግንኙነት ውስጥ ችግሮች ይፈጠራሉ፡፡ እንደ ችግሮችና እንደሚያሻቸው ውሳኔ የሌሎችን ሰዎች ወይም የአማካሪዎችን እርዳታ አጥብቆ መፈለግ ብልህነት ነው። መልካም መካሪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ይመክራልና፡- *"መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ሕዝብ ይወድቃል በመካሮች ብዛት ግን ደኅንነት ይሆናል።"* /ምሳሌ 11፡ 14/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ አምስት (5)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በጋራ መወሰንን እንዴት ትገልጡታላችሁ? ባልና ሚስት ሆነን ስንኖር በሁሉ ነገር መስማማት አለብን ወይ? ካልሆነስ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
2. የባለትዳሮች በጋራ መወሰን የሚሰጠውን ጥቅም በማንሳትና ከትዳር ሕይወታችሁ ጋር በማያያዝ ተወያዩበት።
3. ባልና ሚስት እንደ ባለትዳር በጋራ መወሰን እንዳይችሉ የሚያደርጓቸው የተለያዩ ምክንያቶች ምንድን ናቸው? ምክንያቶችን በመዘርዘርና በእናንተ ትዳር የግጭት ምክንያት የሆኑባችሁን ሰበቦች በማንሳት በፍጹም ግልጥነት ተወያዩባቸው፡፡
4. እንደ ባለትዳር ለጋራ የትዳር ሕይወት በጋራ እየተመካከሩ መወሰን እንዲቻል ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
5. ዛሬ በእናንተ የትዳር ሕይወት በግልና በጋራ ልትወስዷቸው የሚገቡ ተግባራዊ የመፍትሔ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? በጋራ ለውጥ ለማምጣትና በጋራ ለመረዳዳት ቃል በመግባት እርምጃውን ተግባራዊ ለማድረግ እቅዱ።

# ምዕራፍ ስድስት(6)
# የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት

በባለትዳሮች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አብይ ከሚባሉት አንዱ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ነው። ይህ ምዕራፍ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር ላይ ትኩረት በማድረግ ከባህላችን አንጻር የቤተሰብ አባላት እነማን እንደሆኑና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ምን እንደሆነ በመዳሰስ በቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችንና *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።"* /**ዘፍ 2፡ 24**/ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ መሰረት ያደረጉ መፍትሔዎቻቸውን ይጠቁማል።

## I. ቤተሰብና የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምንነት

ቤተሰብ ማለት በመወለድ፣ አብሮ በማደግ እንዲሁም በጠበቀ ወዳጅነት በተፈጠረ ማሕበራዊነት የተጣመረ ግንኙነት ያለው ቤተ-ዘመዳዊ ትስስር ነው። በአብዛኛው የቤተሰብ አባላት በመባል የሚታወቁት አባትና እናት፣ ወንድምና እህት፣ እንጀራ ልጆች፣ አያትና ቅደመ አያት፣ አክስትና አጎት፣ የአክስትና አጎት ልጆች ሲሆኑ እንደ ሰዎች ቅርበት የልጆች አሳዳጊዎች፣ የቅርብ ወዳጆችና ጓደኞችን እንደ ቤተሰብ የመቁጠርና የማጠጋጋት ባህልም አለን። ባልም ሆነ ሚስት የሚያድጉትና የሚቀረጹት በዚህ ሕብረት ውስጥ በመሆኑ ካደጉና ወደ ራሳቸው ትዳር ከገቡ በኋላ እንኳን የዚህ ማሕበራዊ መረብ ጥልፍልፎሽ በአእምሮአቸው፣ በአይታቸው፣ በልምዶቻቸው፣ በፍላጎታቸውና በአጠቃላይ በሁለንተናቸው ውስጥ ሊረዱት ከሚችሉት በላይ ማረፊያ ቦታና ዋጋ አለው፡፡

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ስልን አንድ ሰው ከቤተሰብ ኅብረት ወጥቶ ትዳር ከመሠረተ በኋላ በሚኖረው የትዳር ሕይወት ላይ የቀድሞው ቤተሰብ አባላት አዲስ ቤተሰብ የመሠረተውን የቀድሞ የቤተሰባቸው አባል እንደ ቀድሞው ለማስተዳደር የመፈለግና ጥረት የማድረግ ሂደት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተለያየ መንገድ ሊገለጥ ይችላል። ከአዲሶቹ ተጋቢዎች መካከል የአንዳቸው ወይም የሁለቱም የቤተሰብ አባላት እንደ ቀድሞው የልጅነት ኑሮ በጥንዶች ሕይወት ላይ ለመወሰን ፍላጎት ማሳየታቸውና ሙከራ ማድረጋቸው እንዲሁም የጥንዶችን የፍቅር ግንኙነት በተለያየ መንገድ መሻማት መፈለጋቸውና ለመሻማት መታገላቸው ዋናው የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት መገለጫ ነው።

## II. አባትንና እናትን መተው

**በዘፍጥረት 2፡ 24** የተጻፈውን ክፍል በማጣቀስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አገልግሎቱ ለፈርሳዊያን ጥያቄ **በማቴ 19፡ 5** በሰጠው ምላሽ *"... ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"* /**ማቴ 19፡ 5**/ በማለት ሰው ወደ ጋብቻ ሕይወት ሲገባ አስቀድሞ ከቤተሰቡ ጋር የነበረውን ጥብቅ ቁርኝት በማላላት ራሱን ችሎ የተገነባ አዲስ ቤተሰብ የመሰረተ መሆኑን አሻሚ





ባልሆነ መንገድ ግልጥ አድርጎታል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስም **በኤፌ 5፡ 31** ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልዕክት ይህንኑ መርህ ሲያረጋግጥና ሲያጠናክር መመልከት እንችላለን።

በእርግጥ *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል"* የሚለውን ቃል ሚዛኑን ያልጠበቀ ትርጓሜ በመስጠት ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የተረዱትን አንዳንቹን ጥንዶች ከወላጆች ጋር ፈጽሞ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዳይኖር የመፈለግ ዝንባሌ እንዲያንጸባርቁ ዳርጓቸዋል፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ሌሎች ጥንዶች ደግሞ ሊተገበር የማይችል መርህ እንደሆነ ቆጥረውት ይህንን እውነት ወደ ጎን በመተው ድንበር የለሽ በሆነ መቀላቀል ትዳራቸውን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመጋራት ባልተፈለገ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ትዳራቸውን በቀውስ አደጋ ላይ ሲጥሉት ይታያል። ስለዚህ ባልም ሆነ ሚስት ወደ ትዳር በሚገቡበት ወቅት ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ያሉት ቅዱሳት መጽሐፍት በስምምነት የመሰከሩለትንና የገለጡትን እውነት ከጽንፈኝነት በጸዳ እንዲሁም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ሊረዱት ይገባል፡፡ ለዚህ እውነት ራስን ለማስገዛት በተዘጋጀ ማንነትና በቆረጠ ፈቃደኝነትም አዲሱን ቤተሰብ መመሥረት ኃላፊነታቸው ነው፡፡ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ይወጡት ዘንድ ደግሞ ከሚከተሉት አሳቦች ጋር መግባባት አለባቸው፡-

## I. አባትና እናትን የመተውን መርህ በትክክል መረዳት

አስቀድሞ እንደተገለጠው ትዳር የመሠረቱ ጥንዶች *"ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል"* የሚለውን አምላካዊ ቃል ትክክለኛ በሆነ፣ ትዳርን ሊያንጽ እና ሊተገበር በሚችል መንገድ ሊረዱት ይገባል፡፡ አንደኛው መገንዘብ ያለባቸው እውነት አባትና እናትን መተው ማለት ከቤተሰብ ጋር ፈጽሞ ቤተሰባዊ ግንኙነት አለማድረግ ወይም ከቤተሰብ ጋር ያለን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ማቋረጥ ማለት አይደለም። ተጋቢዎች ማስተዋል ያለባቸው ጉዳይ የእኛ ወይም የትዳር አጋራችን ቤተሰቦች ቤተሰቦቻችን መሆናቸውን ነው። የትዳር አጋራችን ቤተሰብ አባላት የባል ወይም የሚስት ወላጆች (አባትና እናት)፣ እህት፣ ወንድም... መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ወደን ያገባናቸው የትዳር አጋሮች የተገኙበትና አቅማቸው በፈቀደ መጠን የትዳር ጓደኞችንን አሳድገው ለቁም ነገር ያበቁ እነዚህ የቤተሰብ አባላት ናቸው፡፡ ስለዚህ የአክብሮት፣ የፍቅር፣ የወዳጅነትና የበጎ አመለካከት ምላሽ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ይህን ሐቅ በመቀበል በተቻለ መጠን ጤናማ ቤተሰባዊ ግንኙነት እንዲኖር መጣር መልካም ነው።

ሌላው **"*መተው*"** ማለት ፈጽሞ ቤተሰብ ለባለትዳሮች፡ ባለትዳሮች ደግሞ ለቤተሰብ የተለያየ ድጋፍ ማድረግ አያስፈልገንም ማለት አይደለም። የትዳርን ጤንነትና ደስታ በማያደፈርስ መንገድ፣ በሚያስፈልግ ጊዜና ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች መመካከር፣ መረዳዳትና መደጋገፍ ተገቢ ነው። ለወላጆቻችን እንደ ልጅና እንደ ትዳር አጋሮቻችን

ቤተሰብ በሚያስፈልጋቸው ነገር አቅማችን በፈቀደ መጠን በመመካከር ልንረዳቸው፣ አብረናቸው ልንቆምና የልጅነት ኃላፊነትና ግዴታችንን ልንወጣ የግድ ነው። ነገር ግን በትዳር የተጣመርነውና አዲሱን የባልነትና የሚስትነት ዝምድና የፈጠርነው እኛ (ባልና ሚስት) በመሆናችን ጥንዶች በሚኖረን ግንኙነትና የትዳር ኃላፊነት ውስጥ ቤተሰብ እኩል ድርሻ ኖሮት አብሮን በጉዳዮቻችን ላይ ይወያያል፣ ውሳኔ ይወስናል ወይም መመሪያ ይሰጣል ማለት አይደለም፡፡ ወደ ትዳር ስንገባ ከቤተሰብ ጋር ያለን ጥብቅ ትስስር መላላትና ከትዳር አጋራችን ጋር ያለን ትስስር ግን የሌላ ሰው ጣልቃ ገብነትን ንፋስ በማያስገባ መንገድ ጠበቅ ማለት ይኖርበታል፡፡ ይህ መርህ ሁል ጊዜ መጣስ የሌለበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጋብቻ ሕግ ስለሆነ በተጋቡ ጥንዶች ሁሉ መከበር አለበት፡፡

## 2. የቤት- ዘመድ ጣልቃ ገብነትን ምንነት መረዳት

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነትን ምንነት፣ መቼ፣ በምንመልኩና እንዴት እንደሚከሰት መረዳት ድንበር ዘለል የሆነው ቤተሰባዊ ግንኙነት የተመሠረተውን የትዳር ሕይወት እንዳይጎዳ አስቀድሞ ለመጠንቀቅ ይረዳል። ለመሆኑ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ምን ማለት ነው።

**አንደኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት፡ የቤተሰብ አባል የሆኑ ቤት- ዘመዶች በሙሉ ወይም በከፊል በጥንዶች የትዳር ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የመፈለግና ጥንዶቹም በጋራ ወይም በተናጠል ከትዳር አጋሮቻቸው በፊት ለቤተ-ዘመድ በማንኛውም ጉዳይ ቅድሚያ መስጠት የመጀመር ሂደት ነው።

**ሁለተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት፡ የቤተ-ዘመድ አባል የሆኑ ሰዎች የጥንዶችን የትዳር ፍቅር በመጋራት ወይም በመሻማት ጥንዶቹ ከትዳር አጋራቸው ጋር ሰፊና የተመረጠን ጊዜ ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት፣ ከትዳር አጋራቸው እንዲሰጣቸው የሚፈልጉትን ትኩረት እንዲሁም ማግኘት የሚፈልጉትን ፍቅርና እንክብካቤ በአግባቡ እንዳያገኙ እንቅፋት የመሆን ሂደት ነው፡፡ ወይም የተወደዱ እናት፣ አባት፣ ልጅ፣ ወንድም፣ እህት... ለትዳር ጓደኛ የሚሰጥን ፍቅርና እንክብካቤ ለራሳቸው ለመውሰድ ሲንቀሳቀሱ ከዚያም አልፎ ባለትዳሮችም ሲፈቅዱላቸው የሚጠቁም ወይም የሚያሳይ ሁኔታ ነው።

**ሦስተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተ- ዘመድ አባል በተለይ ወላጆች፣ እህትና ወንድም ወይም ሌሎች ቤተ-ዘመዶችና ከጥንዶቹ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በጥንዶች የትዳር ሕይወት ጣልቃ በመግባትና የባልና የሚስትን ሚና በመጋፋት ወይም በመንጠቅ አዲስ የተመሰረተውን ቤተሰብ መምራትና ማስተዳደር ሲጀምሩና በተለያየ ምክንያት ጥንዶችም የቤተሰብ አባል የሆነ ሰው ይህን እንዲያደረግ እድል ሲሰጡ የሚያሳይ ሂደት ነው።





**አራተኛ፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተሰብ አባት በባለትዳሮች ሕይወት፣ ምርጫና ውሳኔ ላይ ለመሳተፍና ለመወሰን ዕድል እንዲሰጣቸው ሲጥሩና ጥንዶችም በጋራ ወይም በግል ፈቅደው በውሳኔዎች ሁሉ እንዲሳተፉ በር የመክፈት ሂደት ነው።

**አምስተኛውና የመጨረሻው፡-** የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት የቤተ-ዘመድ አባል የሆነ ግለሰብም ይሁን በአጠቃላይ የቤተሰብ አባላት ከጥንዶቹ ጋር እኩል በሆነና ከእነርሱ ባልተናነሰ መልኩ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ከጥንዶቹ የትዳር ሕይወት ተጠቃሚ መሆን ሲፈልጉ፣ ሲጀምሩና እንዲጠቀሙ ባለትዳሮች ሲፈቅዱላቸውና ዕድል ሲሰጧቸው የሚያሳይ ሂደትና ሁኔታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

በአጠቃላይ እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች በባለ ትዳሮች ኅብረት ውስጥ የሚፈጠሩ ከሆነ በጥንዶቹ የተመሠረተው ትዳር ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ይገባል፡፡ ጉዳዩ በጊዜ ካልተስተካከለም ወደ ፍች ሊያደረስ ይችላል፡፡ ይህንን እውነታ በመረዳት ጥንዶች የትዳራቸው ጤንነት ጠላት ከሆነው ከዚህ በሽታ አስቀድመው ትዳራቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ችግሩ ከተከሰተ በኋላ ካወቁት ደግሞ ግልጥ በሆነ ውይይትና በማያወላውል ውሳኔ አግባብነት ያለው እርምጃ በመውሰድ ትዳራቸውን ከቀውስ ማዳን ይጠበቅባቸዋል፡፡

# III. በቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለግጭት ሊያጋልጡ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከቤተ-ዘመድ ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች ምንድን እንደሆኑ መረዳት ብዙ አመት ሳንጓዝና የትዳር ግንኙነታችንን ሳያበላሽ በጊዜ ለመንቃት፣ ለመመካከር፣ ለመወሰንና እርምጃ ለመውሰድ ጠቃሚ ነው። ለቤተሰብ ድንበር ዘለል የሆነ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ የሚያደረጉንን ምክንያቶች በማወቅ ሚዛኑን በጠበቀ ግንኙነት፣ ከቤተሰብ ጋር መቀራረብና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ቤተሰባዊነትን መጠበቅ እንችላለን። በሐበሻው ሕብረተሰብ መካከል ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ከሚያደረጉን ምክንያቶች መካከል ጥቂቶቹ እያንዳንዳችን ለቤተሰብ ያለን ቤተሰባዊ የሆነ ፍቅር፣ የቤተሰብ ባህሎቻችን የፈጠሯቸው እሴቶችና ልምዶች፣ የኢኮኖሚ ችግሮቻችን፣ አንዱ የሌላው ጥገኛ መሆንና የሥራን ጫና ለመጋራት (ለመደጋገፍ) በተለይ በወሊድ፣ በሕመም፣ ልጆችን በማሳደግና ለመማርና የተሻለ ሥራ አግኝቶ ለመሥራት መፈለግ የመሳሰሉት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሰበቦች ምክንያት ባለትዳሮች ይበልጥ ከቤተሰብ ጋር ይቀራረቡና ለችግሩ የበለጠ ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ የሚከተሉት ለችግሩ ተጋላጭ የሚያደርጉን ነጥቦች ይህንን አሳብ የበለጠ ለማብራራት ያስችሉናል፡፡

## I. አባትንና እናትን አለመተው

አስቀድሞ በሚገባ እንደተገለጠው መጽሐፍ ቅዱስ *"ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?"*

/ማቴ 19፡ 5፣ ኤፌ. 5፡ 31/ የሚል ግልጥ መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ የሰጠ ቢሆንም በቅርብ የተጋቡ እንዲሁም ጥቂት ለማይባሉ አመታት በጋብቻ ውስጥ የቆዩ ባለ ትዳሮች ይህንን እውነት በመረዳት በዚህ መርህ ትዳራቸውን ሲመሩ አይታዩም፡፡ ይህ ችግርም በተለይ በአዲስ ተጋቢዎች የጋብቻ ሕብረት መካከል የቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት እንዲከሰት ሰበብ ከሚሆኑ ምክንያቶች መካከል እናትና አባትን አለመተው ከዋናዎቹ አንዱ እንዲሆን አድርጎታል።

ብዙዎቹ አዲስ ተጋቢዎች ቀድሞ ከቤተሰባቸው ጋር የነበራቸው የብዙ አመት ግንኙነት፣ አስተዳደግ፣ ቅርበትና ባሕርይ ተደማምሮ የተቀረጹበትን የቀድሞ ዓለም ለመተው ይቸገራሉ። አባትንና እናትን ባለመተው ከትዳራቸው በፊት እነርሱን በማስቀደምና ለትዳር ጓደኛቸው መስጠት ያለባቸውን ፍቅር እንዲሻሙ በመፍቀድ ከትዳራቸው ይልቅ ቤተሰብን ማስበለጣቸው ለሌላ ተያያዥ ችግር የሚያጋልጣቸው ሆኗል። ይህ ሁኔታ በትዳር ውስጥ በሚደረግ ምርጫና ውሳኔ ጣልቃ እንዲገቡና አዲሱን ቤተሰብ እንዲያስተዳድሩ ለወላጆች ወይም ለዘመዶች የማይገባቸውን ፍቃድና መብትም ይሰጣቸዋል፡፡

በማንኛውም ሁኔታ ከትዳር ሕይወታቸው ተገቢ ባልሆነ መንገድ ቤተሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረጉ ከመጠን ላለፈ የቤተሰብ አስተዳደር ጣልቃ ገብነት አዲሱ ትዳር ተጋላጭ ይሆናል። ችግሩ የሚያስከትለው አፍራሽ ተጽዕኖ ሁሉቱም ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ አንዱ ከጋብቻ በፊት ይኖሩት የነበረውን የአኗኗር ዘይቤ ካገቡ በኋላ እንዳይተውትና አብሯቸው እንዲቀጥል በማነሳሳት ባለትዳሮች ሆነው ሳለ ትቸዋለሁ ወዳሉት የብቸኝነት ኑሮ የኋሊት እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል፡፡ ይህም ከስተት በባለትዳሮች መካከል የአስከፊ አለመግባባትና ግጭት ምክንያት ይሆናል፡፡ ነገሩ ከከፋም ለፍች ሊዳርጋቸው የሚችል ቀውስ ይሆናል።

## 2. ከቤተሰብ አባል የለመዱትን ከትዳር አጋሮቻቸው ማጣትና የለመዱትን መፈለግ መጀመር

ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር አዲስ ተጋቢዎች ተጋላጭ እንዲሆኑ የሚያደርጋቸው ሌላው ምክንያት ከጋብቻ በፊት በቤተሰብ አባሎቻቸው መካከል ሲሆኑላቸው የነበሩትን ልዩ ልዩ ጥቅሞችና እንክብካቤዎች ከትዳር አጋሮቻቸው መጠበቅ መጀመራቸው ነው። ሚስቶች ከአባታቸውና ከወንድሞቻቸው የለመዱትን ባሎቻቸው እንደ አባትና እንደ ወንድም በመሆን እንዲያሟሉላቸው ይጠብቃሉ፡፡ የጠበቁትን ሳያገኙ ሲቀሩ ደግሞ ሊናደዱ፣ ሊያጉረመርሙ፣ ሊያማርሩና በትዳር ግንኙነታቸው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊመጣ ይችላል። እንዲሁም ባሎች የእናታቸውንና የእህቶቻቸውን ባሕርይ፣ ልምምድና እንክብካቤ ... ከሚስቶቻቸው ማግኘት ጠብቀው ሳያገኙ ሲቀሩ ይጎዳሉ፡፡ ጉዳዩም ላለመግባባትና ለግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል።





ይህ ችግር ባጋጠማቸው ጊዜ ከትዳር አጋሮቻቸው ማግኘት ያልቻሉትን ነገር ፍለጋ ወደ ቤተሰቦቻቸው ይመለሳሉ፡፡ ከትዳር ጓደኛቸውም ይልቅ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ቅርበታቸውን ያጠናክራሉ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ችግሩ አድጎ ትልቅ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ቀውስ በትዳር ውስጥ ይፈጥራል፡፡ ለዚህም ነው አዲስ ተጋቢዎች ከጋብቻ በፊት ስለቤተሰባቸውና ስለአስተዳደጋቸው መነጋገር፣ መተዋወቅ ብሎም አንዳንድ ነገሮችን አስቀድሞ ማስተካከል የሚያስፈልጋቸው። አስቀድመው ያወቁት ነገር አያስደነግጥም፣ ግራ አያጋባም፣ ደግሞም ራስን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

## 3. ቤተሰብን ለመርዳትና ከቤተሰብ እርዳታ በመፈለግ መካከል የሚፈጠር ውጥረት

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል እንዲህ ዓይነቱ ችግር እንዲፈጠር የሚያደርገው ምክንያት ወቅቱ የሽግግር ጊዜ መሆኑ ነው። በቤተሰብ ሲተዳደሩ የነበሩ ወይም በግል ራስን በራስ ሲያስተዳድሩ የነበሩ ላጤዎች ወደ ጋብቻ በሚገቡበት ወቅት የቤተሰብ አስተዳደር ጥገኝነት ዝንባሌ ወይም የራስን በራስ ለመምራት የመምረጥና የመወሰን ችግር ሊታይባቸው ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚፈጠሩ ችግሮች በሁለት አቅጣጫ ሊከሰቱ ይችላሉ። የመጀመሪያው የመጡበት የቤተሰብ የኑሮ አቅም ደካማ ሆኖ ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የማይችሉ ሲሆንና ለወላጆቻቸው የገንዘብና የተለያዩ ነገሮች እርዳታ ማቅረብ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን የሚፈጠር ችግር ነው። ቤተሰብን ለመርዳት የሚደረገው ጥረት ሂደት ከትዳር አጋር ጋር ሊያጋጫቸውና ለትዳራቸው ችግር ሊሆን ይችላል። የተረጂው ቤተሰብ አባላትም የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅምና ድጋፍ እንዳይቋረጥባቸው በልጆቻቸው ትዳር ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ፡፡

ሌላው በትዳር ላይ ያሉ ልጆች በወላጆች እርዳታ ሥር የወደቁና አግብተውም የቤተሰብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወይም ጥገኛ ከሆኑ ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ክስተቱም በባለትዳሮች መካከል ሰላም እንዲጠፋ፣ እንዳይግባቡና እንዲጋጩ ያዳርጋል። ብዙ ጊዜ በገንዘብ ጥገኛ የሆኑ ሰዎች በራሳቸው የመምረጥና የመወሰን ብቃታቸው ላይ ጥገኝነታቸው አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያመጣባቸው ይችላል። አንዳንድ በገንዘብ የሚረዱ ሰዎች በተጋቢዎች መካከል ጣልቃ በመግባት በሚረዷቸው ሰዎች ኑሮ ላይ የመምረጥ፣ የመወሰንና የማስተዳደር የባለስልጣንነት አዝማሚያ ይታይባቸዋል። እነዚህ ሁለት ውጥረቶች በጥንዶች ትዳር ውስጥ መልካም የሆነ ግንኙነት እንዲጠፋ፣ በመካከላቸው ሰላምና ደስታ እንዳይኖርና እንደ ባለትዳር በጋራ እየወሰኑ የመኖር ዋስትናቸው ጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ በማስገደድ ከፍተኛ የሆነ እንቅፋትን ይፈጥሩባቸዋል።

## 4. የአንዱ የትዳር አጋር ቤተሰብ ላይ ብቻ ያተኮረ እርዳታና ቅርብ ግንኙነት መፍጠር

ሌላው ችግር ሊሆን የሚችለው ባል ወይም ሚስት ከአንዳቸው ቤተሰብ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረጋቸው ነው። ወደራስ ቤተሰብ ብቻ ያጋደለ የገንዘብና የቁሳቁስ... እርዳታ በማድረግ የሌላውን የትዳር አጋር ቤተሰብ መርሳት፣ መተውና ችላ ማለት ሲጀመር በትዳራቸው መካከል አለመግባባትና ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሊሆን ይችላል። አድሏዊነት በተሞላ መንገድ አንዱ የትዳር አጋር ሳይፈቅድና ደስተኛ ሳይሆን ከአንደኛው ቤተሰብ ጋር ብቻ የተለየ ቅርበት፣ ግንኙነት እና ኅብረት ማድረግ በትዳር ውስጥ ችግር እንዲፈጠር ከማድረጉ ባሻገር ለሌሎች የተባባሱ ግጭቶች አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል።

## 5. የትዳርና የትዳር ጓደኛ በቤተ-ዘመድ ዘንድ ተቀባይነት ማጣት

ስለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ባለን የባህል ተጽዕኖና አሉታዊ አስተሳሰብ ምክንያት ስለትዳር አጋሮቻችን ቤተሰብ መልካም አለማሰብ ሊፈጠር ይችላል። መልካም የሆነ አስተሳሰብ ካለመኖሩ የተነሳም በትዳር ጓደኞችን ቤተሰብ ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት እያለን እንዳልተቀበሉን ሊሰማን ይችላል። በዚህ ወቅት የምናስባቸው ሃሳቦች፣ የምናሳያቸውና የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ለትዳር አጋሮች በትዳራቸውና በቤተሰብ መካከል የመሆን ውጥረት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። ባላረጋገጥነው ጉዳይ የራሳችንን የተሳሳተ ግምት በመውሰድ ለትዳራችንና ለቤተሰብ ሰላምና ደስታ መደፍረስ ምክንያት ልንሆን እንችላለን፡፡ ስለዚህ በማስተዋል ነገሮችን በመያዝ ከተሳሳተ ግምት የጸዳ አስተሳሰብ እንዲኖረን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ነገር ግን ሁልጊዜ ችግር የሚፈጠረው በተሳሳቱ ግምቶች ምክንያት ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለትዳር ጓደኞቻቸው ቤተሰቦቻቸው ዘንድ መልካም አስተሳሰብ ያላቸው ተጋቢዎችም የችግሩ ሰለባዎች የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች ከቤተሰቦቻቸውና ከአማቾቻቸው ጋር ያላቸው መልካም ግንኙነት የመፍጠር ተስፋ እንደ ጠበቁትና በቀና ስሜት እንደ አሰቡት ሳይሆን ሲቀር ሁኔታው ወደ ግጭትና አለመግባባት ያመራል። ሲያገቡ ከቤተሰቦቻቸውና ከትዳር አጋሮቻቸው ቤተሰብ ጋር እንዲኖራቸው የሚፈልጉት መልካም ግንኙነት፣ ቅርበትና መረዳዳት እንደፈለጉት ሳይሆን በመቅረቱ ያዘኑ የትዳር አጋሮች በንግግርና በድርጊት ተቃውሞቻቸውን ማሰማትና ማሳየት ይጀምራሉ። በዚህ ወቅት በባለትዳሮች መካከል የቃላት ጦርነት፣ የመኮራረፍና በከፍተኛ ሁኔታ የመጋጨት ዕድሎች ይበዛሉ።

የባለትዳር ቤተሰቦችም ልጃቸው በማግባቱ ምክንያት የግል ጥቅማቸው ሊቀር እንደሚችል ወይም እንደ ቀረባቸው ማሰብና ማየት ከጀመሩ የሚያሳዩትና የሚያንጸባርቁት የተለየ ጸባይ በባለትዳሮች መካከል ስምምነት እንዳይኖርና ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል። ይህ ሲከሰት የተሳሰተ ግምትን በመልካም ድርጊትና ፍቅርን በሕይወት በማሳየት በመልካምነት ማሸነፍ ተገቢ ነው። ቀድሞ ይደርግላቸው የነበረ





የግል ጥቅም ለምን እንደ ቀረ ማሳየትና የታሰበ ልዩ የሆነ ዕቅድ ካለ በመልካም ግንኙነት በመነጋገር ማሳወቅ፣ ማስረዳትና ነገሮችን ግልጥ ማድረግ ችግሩን ለመከላከልና ለመቀነስ ጠቃሚ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ለትዳርና ለትዳር ጓደኞች ቤተሰብ እንግዳ ከሆነ አዲስ ልምምድ፣ የሌላውን አካል ቤተሰብ ባህል ካለማወቅ፣ እንዴት መቀራረብና መነጋገር እንደሚቻል ካለመገንዘብ፣ የሚወዱትንና የሚጠሉትን እንዲሁም ዋጋ የሚሰጡትን ነገር ካለማወቅና ካለመረዳት የተነሳ ከትዳር አጋር ቤተሰብ ጋር የሚፈጠር አለመግባባትና ጥላቻ ወደ ትዳር ዘልቆ በመግባት ጥንዶችን እንዳይግባቡና እንዲጋጩ ሊያደርግ ይችላል። በተቻለ መጠን ለምን እንደ ተጋጨን፣ ግጭቱን የፈጠረውን ወይም ያባባሰውን ችግርና ሊደረግ የሚገባውን ነገር ጠንቅቆ በማወቅና መፍትሔ እንዲያገኝ በመጣር እንደ ቤተሰብ ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ *"ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።"* /ሮሜ 12፡ 18/ በማለት እንደሚናገር ለመኖር ራስን መስጠት የትዳር ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ጊዜ ልንከተለው የሚገባ የክርስቲያናዊ ሕይወት ኃላፊነት ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት በቅድሚያ የምንወጣበትና ለመተግበር የምንለማመድበት የመጀመሪያው ቦታ ግን የጋብቻ ሕይወታችን ነው፡፡

## 6. ከቤተሰብ ጋር በአንድ አካባቢ በመኖር የትዳር ግንኙነት ለቤተሰብ ግልጥ መሆን

አንዳንድ ጊዜ ካለን ቅርበትና ከቤተሰብ ጋር ለመለያየት ከመቸገር የተነሳ፣ በጊዜው አዲስ ተጋቢዎችና ቤተሰብ ካላቸው ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትና ለጊዜውም ሆነ በቋሚነት በአንድ አገር፣ ከተማ፣ ሰፈር፣ ግቢ ወይም ቤት ውስጥ አብረው በመኖር የሁለቱም ወገኖች ሕይወት፣ መውጣትና መግባት፣ ስሜትና ኑሮ ... በጣም የሚታወቅ ወይም ግልጥ ይሆናል። በተቻለ መጠን አብሮ ከጋብቻ በኋላ ከቤተሰብ ጋር አንድ ሰፈር፣ ግቢና ቤት መኖርን በማስወገድ የግል ኑሮን ከቤተሰብ ፈቀቅ ብሎ መምራት ለተጋቢዎች የትዳር ግንኙነት ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው። አብሮ የመኖር ግዴታ ከተፈጠረ ደግሞ በገደብ፣ በመከባበር፣ አንዱ በሌላው ኑሮ አላስፈላጊ የሆነ ጣልቃ ገብነት በሌለበትና ሁሉን የትዳር ሕይወት ግልጥ ባለማድረግ ለመኖር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።

# IV. በቤተ-ዘመድ ጣልቃ ገብነት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

## 1. ማስተካከል፡- ትክክለኛ ባልሆነ ግምት የተበላሸ አእምሮን ማስተካከል

አስቀድሞ በተለያዩ ምክንያቶች፣ ትክክለኛ ባልሆነ መረጃና ባልተፈጸመ ተስፋ የተበላሸ አእምሮን ማስተካከል ተገቢ ነው። እንዲሁ በደፈናው ከሌሎች ሰዎች በሰማነው ወሬ ብቻ ምንም ማስረጃ ሳይኖረን የተበላሸን ህሊና ማስተካከል ችግሮችን የመፍታት የመጀመሪያው እርምጃ ሊሆን ይገባል። ይህን ማድረጋችን ነገሮች እንደ ጠበቅናቸው ሳይሆኑ በመቅረታቸው ከማፈርና ከመልካም የትዳር አጋሮቻችንና አማቾቻችን ጋር መልካም ግንኙነት ሳይኖረን በመቅረቱ ጸጸት ውስጥ ከመግባት ራሳችንን

ለመጠበቅ ይረዳናል። በመልካም አእምሮ በተቻለ መጠን ከትዳር ጓደኞችን ብሎም ከአማቾች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረን የበኩላችንን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። እንደ ሙሴ አማት ዓይነት መልካም ምክር የሚመክሩ አማቾች እንዳሉ መዘንጋት የለብንም። *"የሙሴም አማት አለው። አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም። ይህ ነገር ይከብድብሃልና አንተ ከአንተም ጋር ያለው ሕዝብ ትደከማላችሁ አንተ ብቻህን ልታደርገው አትችልም። አሁንም አመክርሃለሁና ቃሌን ስማ፥ እግዚአብሔርም ከአንተ ጋር ይሆናል አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለሕዝቡ ሁን፥ ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ ሥርዓቱንም ሕጉንም አስተምራቸው፥ የሚሄዱበትን መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው።"* /ዘጸ 18: 17-20/::

## 2. ማሳየት፡- የትዳር አጋርና የትዳር ግንኙነት ቀዳሚ ኃላፊነታችን እንደሆነ ማሳየት

የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ማለት ቤተሰቦቻችን ከትዳር አጋሮቻችን በበለጠና ቀዳሚ በሆነ ሁኔታ ጊዜ፣ ትኩረት፣ ዋጋና ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የመፈለግና እኛም እድሉን የመስጠት ሂደት ነው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ፣ ፍላጎትና እንቅስቃሴ በቤተሰብ አካባቢ ከመጀመሩ በፊትና ሲጀመር ትዳራችን ቁጥር አንድ ኃላፊነታችን መሆኑን ለሁሉም ቡድኖች በግልጥ ማሳየት አስፈላጊ ነው። ይህም ምናልባት ውሳኔ በሚጠይቁ ሁኔታዎች በጋራ በመመካከር፣ በአማቾች ፊት በእውነተኛ ፍቅር የትዳር አጋሮቻችን በማክበርና በተለያየ ጊዜ ከቃል ባለፈ በድርጊት አስፈላጊውን ነገር በአስፈላጊ ጊዜና ቦታ በማቅረብ፣ ቅድሚያ በመስጠትና በመንከባከብ አጋርነታችንን የምናሳይበት መልካም አጋጣሚ ይሆንልናል:: በዚህ መንገድም መጽሐፍ ቅዱስ *"ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፤ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤"* /ሮሜ 12፡ 9-10/ በማለት በሚሰጠን ምክር በመኖር የትዳራችንን ጤንነትና ደስታ እንድንጠብቅ ያስችለናል።

## 3. ማስለመድ፡- ቤተሰቦቻችንን ማክበርን እንጂ በሁሉም ነገር መታዘዝ የሌለብን መሆኑን ማሳየትና ማስለመድ

ወላጆቻችን መሆናቸውንና የትዳር አጋሮቻችንን ወልደውና አሳድገው እንደ ሰጡን በመረዳት ቤተሰቦቻችንን በልባችንና በተግባር ልናከብራቸው ይገባል። *"እግዚአብሔር አምላክህ እንዳዘዘህ አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ እንዲረዝም፥ መልካምም እንዲሆንልህ።"* /ዘዳ 5፡ 16፤ ማቴ 15፡ 4/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እውነትም የሚያሳየን ይህንን ነው:: ወላጅን ማክበር ማለት ግን በሁሉም ነገር ወይም የሚሉንን ሁሉ ለእነርሱ በመታዘዝ የመፈጸም ግዴታ አለብን ማለት አይደለም:: በወላጅና ባለትዳር በሆኑ ልጆች እንዲሁም በአማቾች መካከል የጋራ ሁለትዮሽ የሆነ መከባበር መፈጠርና መጠበቅ ይኖርበታል። ነገር ግን በሰው ፊት የግል ሚስጥሮቻችንንና መረጃዎቻችንን ሲያወጡ፣ መብቶቻችንንና ኃላፊነቶቻችንን ሲጋፉ፣ በሌሎች ሰዎች ፊት ሲያሸማቅቁን፣ ሲዘልፉንና ሲያቃልሉን ያደረጉትን በማሳየትና ያለፈውን ችግር በማስተካከል ቀጣይ ግንኙነታችን በመከባበር ላይ የተመሠረተ





እንዲሆን መጠየቅ ተገቢ ነው። በተለይ ልጅ የሆነው አካል ለቤተሰቡ በትዳር አጋሩ ላይ የሚባለውን፣ የሚደረገውንና እየተፈጠረ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በጥበብ ቃል፣ በትዕግስትና አክብሮት በተሞላው ማንነት በማሳየት ገደብ እንዲኖራቸው ማስለመድ ተገቢ ነው። ይህንን ማድረግ ስንችል ነው *"ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልን ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው።"* /ምሳሌ 16: 16/ የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ አግኝተናል ማለት የሚቻለው::

## 4. ማቆም፡- በትዳር የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ወደ ቤተሰብ አባላት ይዞ መሄድን ማቆም

በትዳር መካከል አለመግባባትና ግጭት መኖሩ አይቀሬ ነው። በግጭት ወቅት የሚፈጠረው አሉታዊ ስሜት ቀላል ላይሆን ይችላል:: ነገር ግን የትዳርን ችግር ወደ ቤተሰብ አባላት ይዞ መሄድ ይበልጥ ችግሩን ሊያባብስ ይችላል። የትዳርን ችግር ይዞ መሄድ ችግሩን ሊያባብስ የሚችልበት ምክንያት ቤተሰቦቻችን ከመሆናቸው የተነሳ አድሎ ማድረጋቸው አይቀሬ ስለሚሆን ነው:: አልያም አድሎ አደረጉ እንዳይባሉ በሚያደርጉት ጥረት ችግሩ የበለጠ ሌላ አቅጣጫ ሊይዝና ሊባባስ ይችላል።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው ባንድ ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር "ቤተሰብን ስለችግሮቻችን ማማከር ቆይቶ የሚያዳልጥ ዳገት (አቀበት) ሊሆን ይችላል"[7] በማለት አስገንዝቧል። ስለዚህ ባለ ትዳሮች ራሳችንን ችለን በተረጋጋ፣ በስክነና ትዕግስት በሞላበት ስሜት መወያየት፣ አብረን መወሰንና ችግሮቻችንን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ማለት ግን ከእኛ አስቀድመው ረጅም ዘመን በትዳር የሕይወት ልምድ ውስጥ ያለፉት ወላጆቻችን ከልምምዳቸው የሚጠቅም፣ የሚያስተምር፣ የሚያስጠነቅቅና የሚመክር ነገር የላቸውም በዚያም አንጠቀምበትም ማለት አይደለም። ነገር ግን ይህንን ጠቃሚ አስተዋጾ ፍለጋ በስሜታዊነት፣ እውቀትና ብስለት በሌለበት ሁኔታ ወደ ወላጆች ሄደን መፍትሔ ለማምጣት ጥረት ስናደርግ ችግሩን የሚያባብስና የሚያወሳስብ ሌላ ችግር ወደ ትዳራችን እንዳንጎትት በእውቀትና በጥንቃቄ ልናደርገው ይገባል:: ይህንንም ማድረግ ያለብን በጣም አስገዳጅ ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ ቢሆን ይመረጣል።

## 5. ማስወገድ፡- ሚዛናዊነቱን ያልጠበቀ እርዳታና እንክብካቤን ለአንደኛው ቤተሰብ ብቻ ማድረግን ማስወገድ

በጋራ ተነጋግሮና ተስማምቶ በተገቢው መንገድ ቤተሰብን መርዳት ትዳርን ከቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ለመከላከል ይጥቅማል። ከትዳር አጋር ተደብቆ ቤተሰብን

---

[7] Focus on The Family, The first Five Years of Marriage: Tyndale House publishing Inc Carol Stream: Illinois, 2006. page 316

የመርዳት ልምድ በመጀመሪያ በትዳር ውስጥ በመሳቀቅና በድብብቆሽ የሚከናወን ተገቢ ያልሆነ የስረቆት ተግባር ሲሆን በኋላም በታወቀ ወቅት በትዳር ውስጥና በቤተሰባዊ ግንኙነት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። የሚጠይቁትንና የሚያስፈልጋቸውን እርዳታ ከትዳር አጋሮቻችን ጋር በጋራ ተወያይተን እንደምንወስን ማሳየትና የትዳርን ግንኙነት ጤንነት መጠበቅ ይኖርብናል። ሁልጊዜ ልጆች እንደሆንን ብቻ በማሰብ አለመግባባትና አለመረዳዳት እንዳይፈጠር በግላችንና በጋራ እንደ ባለትዳር መምረጥና መወሰን እንደምንችል ማስገንዘብ ተገቢ ነው። *"ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልን ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው።"* /ምሳሌ 16: 16/።

## 6. ማጠናከር፡- ለመልካም ቤተሰባዊ ግንኙነት የሚጠይቀውን ዋጋ በመክፈል ሕብረትን ማጠናከር

ከወላጆቻችንና ከትዳር አጋሮቻችን ወላጆች ጋር እንደ ወላጅና እንደ ቤተሰብ መልካም ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። በትዳር የተሳሰረ ቤተሰባዊነትን መፍጠርና መጠበቅ የጋራ ብርቱ ጥረትን ይጠይቃል። መልካም ቤተሰባዊነት እንዲፈጠርና መልካሙ ግንኙነት ለረጅም ዘመን ዘላቂ እንዲሆን በደስታና በሐዘን ጊዜ ፈጥኖ ምላሽ መስጠት፣ ክፉን በክፉ አለመመለስ፣ መልካም የሆነውን ማሰብ፣ በሰላም ለመኖር ጥረት ማድረግና ክፉውን በመልካም ማሸነፍ በጣም አስፈላጊ ነው። *"ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ። ... ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ። ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። ... ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።"* /ሮሜ 12: 15-21/

እንደ ቤተሰብ እርስ በእርስ በመጠያየቅ፣ በበዓል ጊዜ በመገባበዝ፣ የቤተሰብ የመገናኛ ፕሮግራም በመፍጠር፣ ለእርፍት ወደ ቤተሰብ በመሄድና ቤተሰብን እኛ ወዳለንበት በማምጣት፣ በስልክ በመደዋወል፣ በጋራ በመጸለይና መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን በመካፈል ከቤተሰብ ጋር ግንኙነትን ማጠናከር መልካም ነው። *"ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።"* /ዕብ 10: 24-25/





## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስድስት (6)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱ ጋር ይጣበቃል የሚለው ቃል እንዴት ትረዱታላችሁ?
2. በባለትዳሮች መካከል የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተፈጠረ የምንለው መቼና ምን ሲፈጠር ነው?
3. በባለትዳሮች መካከል በቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ለግጭት የሚዳርጉ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?
4. በእናንተ የትዳር ሕይወት የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ችግር ተከስቶ ያውቃልን? ከተከሰተስ በምን መልኩ ነበር የተከሰተው? በአግባቡ ተወያዩበት፡፡
5. በእናንተ የትዳር ግንኙነት የተፈጠረ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት የግጭት ምክንያት በሄነ ጊዜ ግጭታችሁን ባግባቡ መፍታት ቻላችሁን? ከፈታችሁት ግጭታችሁን የፈታችሁት እንዴት ነበር? ችግሩ እስካሁን ካልተፈታ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
6. በጋራ ለጋራ ለሆነው የትዳር ግንኙነታችሁ በተረጋጋ መንፈስ፣ የትዳርን ግንኙነት ለማደስና መልካም ቤተሰብ ለመመሥረት ዛሬ ልትወስዱት የሚገባ የመፍትሔ እርምጃ ምንድን ነው? እንደሚገባ በሰፊው በመነጋገር በነገሩ ላይ ለመጸለይ በጋራ አቅዱ።

# ምዕራፍ ሰባት(7)

# ተግባቦት (ኮሙኒኬሽን)

በባለትዳሮች መካከል በጣም አስፈላጊ ከሆኑትና ልዩ ትኩረት ከሚያሻቸው ጉዳዮች አንዱ በመካከላቸው ያለው የተግባቦት ሂደት ነው፡፡ የባለትዳሮች መግባባት፣ የተግባቦት ደረጃ፣ የተግባቦት እንቅፋቶችና አለመግባባትን ለመፍታት የሚጠቀሙበት መንገድና ዘዴ በትዳር ጉዞ ላይ ከፍተኛ ሚና አለው። በቅርብ አመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮችንና መፍትሔዎችን በመጠቆም፣ በማስጠንቀቅ፣ በማስተማርና በማበረታታት የተግባቦት ደረጃዎቻቸውን ከፍ እንዲያደርጉ መርዳት የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ ነው

## 1. የተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ምንነት

### 1. ተግባቦት በሰዎች መካከል ግንኙነታዊ ትስስር የሚፈጥር ነው

ተግባቦት በንግግር ወይም በቃላትም ሆነ ያለቃላት በሚደረግ የሰውነት እንቅስቃሴ ራስን ለሌሎች የመግለጽ ሂደት ነው። በትዳር ውስጥ ከትዳር ጓደኛ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ሰዎች ጋር በሰላም አብሮ ለመኖር፣ አብሮ ተግባብቶ ለመስራትና ተስማምቶ ለመጓዝ ተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) አስፈላጊ ነው፡፡ ተግባቦት በአጠቃላይ በሕይወት ጉዞ ውስጥ ምትክ የለሽ ሚና ይጫወታል። መጽሐፍ ቅዱስም *"በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ በአንድነት ይሄዳሉን?"* **/አሞ 3፡ 3/** በማለት ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር እንኳን ስርዓት ያለው ሕብረት ለማድረግ ተግባቦት አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁመናል። ያለመልካም ተግባቦት በሰዎች መካከል ግንኙነትና ትሥሥር ሊኖር አይችልም። መልካም ግንኙነት መልካም ተግባቦትን ይጠይቃል።

### 2. ተግባቦት ግልጽነትና እውነተኝነትን የሚፈልግ ነው

ተግባቦት በተሳካ መልኩ እንዲከናወን ግልጥነት በጣም ጠቃሚ ግብዓት ነው፡፡ ግልጽ የሆነ ተግባቦት ወደ መረዳዳት ይመራል። ግልጥነትና እውነተኝነት በሌለበት መግባባት ሳይሆን ግራ መጋባት ይፈጠራል። ወደ ትዳር ዓለም ስንመጣ ጥንዶቹ የራሳችን የሆነ የቃላት ምርጫ፣ ትርጉም፣ አገላለጽና ዘይቤ ሊኖረን ይችላል። የተለያየ ዘይቤ ያለን ከመሆናችን የተነሳ ለመግባባት ሲባል ግልጽ ያልሆኑ ቃላቶችን፣ ትርጉሞችን፣ አባባሎችንና የምንጠቀምባቸውን ምሳሌዎች ለማብራራት እንገደዳለን፡፡ *"በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ፡- አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤ "* **/ማቴ 11፡ 25/**፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋና ምክንያቱ ጥበበኞችና አስተዋይ የሚባሉ እያሉ ነገር ግን ሰማያዊና መንፈሳዊ የሆነው የእግዚአብሔር ሃሳብ ለሕጻናት መገለጡ፣ እነርሱም አሳቡን ተረድተው ምላሽ በመስጠት መግባባት መቻላቸው ነው።





ንግግራችንን እንደሚገባ ማቅረብ አለመቻልና አድማጫችንን እንደሚገባ አለማድመጥ ይህን ባለማድረግ ምክንያት የሚፈጠር አለመግባባት እንዲያጋጥመን ያደርጋል፡፡ እንዲህ ዓይነት ችግር ሲያጋጥመን እንደገና በተሻለ ግልጥነት ለማስረዳት ጥረት በማድረግ ወደ መግባባት ለመድረስ ተግባቦት ግልጥነትንና እውነተኝነትን የሚፈልግ ሂደት መሆኑን ማሳየት አለብን፡፡ ተግባቦትን በዚህ መልኩ ማካሄድ ካልቻልን የምንፈልገው ጤናማ ግንኙነት ሊከናወን ካለመቻሉም ባሻገር በዚያው ልክ መግባባት አቅቶን ወደ መጋጨት እንገባለን።

### 3. ተግባቦት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል የሚከናወን ነው

ተግባቦት በሁለትና ከሁለት በላይ በሆኑ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ተቋማት መካከል የሚከናወን ሂደት ነው፡፡ ተግባቦት መልዕክት ሰጭ ወይም ላኪ እና መልዕክት ተቀባይ አለው፡፡ በትዳር ሕይወት ውስጥም ተግባቦት ሁለቱን በጋብቻ የተጣመሩ ግለሰቦች እንዲሁም ባለትዳሮችና ቤተሰቦች በነፃነት የሚያሳትፍ ሊሆን ይገባል። ተግባቦት ተካሄደ ማለት የሚቻለው በሁለቱም በኩል ግልጥ የሆነ ንግግር፣ ማስተዋል፣ ትኩረት የተሞላው መልዕክት የመለዋወጥ ሂደት ሲኖርና መልዕክቱን በተመለከተ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ሲቻል ነው። ተግባቦትን ሁለትዮሽ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ ተናጋሪ አድማጭን ማሳተፍ መቻሉ ነው። ተግባቦት ሁለትዮሽ የሆነ ያልተከፋፈለ ሙሉ ትኩረትንና ሌላው ሰው የተናገረውን ማድመጥ፣ ማሰብና መረዳትን የሚጠይቅ ነው፡፡

**የኢየሱስ ንግግር ምሳሌ፡-** ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ ስለሞቱና ስለትንሳኤው በተናገረ ጊዜ እነርሱ ግን ንግግሩን በተሳሳተ መንገድ በመተርጎም ስለሕንጻ እንደተናገረ አስበው ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ የነበረውን ሕንጻ እንዴት በሶስት ቀን ውስጥ መልሶ ሊሠራው ይችላል? በማለት ግራ ሲገባቸው ታይቷል፡፡ ደቀ መዛሙርቱም እንኳ ከሞት ከተነሳ በኋላ ነበር ትክክለኛ ትርጉሙ ገብቷቸው ቃሉን አምነው የተቀበሉት። *"ኢየሱስም መልሶ፡- ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው። ስለዚህ አይሁድ፡- ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።"* **/ዮሐ 2፡ 19/**

ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በወንጌላት ውስጥ የሰጣቸውን ማስጠንቀቂያም ደቀ መዛሙርቱ ሊረዱት አልቻሉም ነበር፡፡ *"እርሱም፡- ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው። እርስ በርሳቸውም። እንጀራ ስለሌለን ይሆናል ብለው ተነጋገሩ። ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው፡- እንጀራ ስለሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላስተዋላችሁምን? ልባችሁስ ደንዝዞአልን? ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን?"* **/ማር 8፡ 15 -18/**፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ ስለመሆኑ በተናገረ ጊዜም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በትርጉም መግባባት አቅቷቸው

እንደነበር እንዲያውም ንግግሩ አስጨናቂ እንደሆነ እርስ በእርሳቸው ሲንሾከሾኩ የነበረ መሆኑን *"... ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ። ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?።"* /ዮሐ 6፡ 51-60/ ከሚለው ክፍል መገንዘብ እንችላለን።

## II. ከተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የግጭት መንስኤዎች

ጤነኛና ደስተኛ ትዳር ያላቸው ባለትዳሮች ከሌሎች የሚለዩበት አንዱ ምክንያት ደስተኝነታቸው ከመልካም ተግባቦት የተገኘ መሆኑ ነው። የተግባቦት ጠንቆችን በመረዳት የተግባቦት ደረጃችንን ከፍ ማድረግ የትዳራችንን ጤንነትና ደስታ ለመጠበቅ ይረዳናል። ብዙ ጊዜ በባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮች ከትዳር ዘመናችን ጋር ይያያዛሉ። በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮችን መመልከት በተግባቦት ውስጥ እንቅፋት ከሚሆኑ ነገሮች ለመጠንቀቅ፣ የተግባቦትን ሂደት ለማሻሻልና የተግባቦት ደረጃን ከፍ ለማድረግ ይጠቅማል። የተግባቦትን ጥራትና ስኬታማነት ለማሳደግ በመጀመሪያዎቹ አስር የጋብቻ አመታት ክልል ውስጥ የሚገኙ ባለትዳሮች የሚከተሉትን ከተግባቦት ጋር በተያያዘ ለግጭት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች መረዳት ይጠቅማቸዋል፡-

### 1. የተግባቦት መልዕክት የተዋቀረባቸውን ሶስት ነገሮችን እንደሚገባ አለማወቅ

አንድ እንዲተላለፍ የምንፈልገው መልዕክት ከሶስት ነገሮች መሠራቱን መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህን ባለመረዳት መልዕክታችን እንደሚገባ ተላለፈ ሲባል ሳይተላለፍ፣ ያልተፈለገ ትርጉም ሲይዝና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲያጋጨን ይታያል። የምናስተላልፈው የመልዕክት ይዘት /Content/ **7%** ነው። መልዕክቱን ለማስተላለፍ የምንጠቀመው የድምጽ ከፍና ዝቅ ማለት እንዲሁም መወፈርና መቅጠን /Tone/ **38%** መሆኑን መረዳት ጠቃሚ ነው። ሌላው በንግግር የማይገለጽ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ /Non-Verbal/ **55%** በመሆን ከፍተኛውን ቁጥር እንደያዘ መረዳት እንችላለን።[8]

ድምጽ የሚያስተላልፈው መልዕክት ያላሰብነውን ወይም ያልተናገርነውን መልዕክት ሊሆንና ከሰዎች ጋር ወደ አልተፈለገ ግጭት ሊያስገባን ይችላል። ዝቅ ባለ ድምጽ ሊነገር የሚገባው ሞቅ ባለ ድምፅ ሲነገር የሚሰጠው መልዕክት ምናልባት የቁጣና የንዴት ወይም ነገሩ አሳሳቢነት ያለው መሆኑን የሚያሳይና ሌላ ያልታሰበን መልዕክት የሚያስተላልፍ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ከባለቤቴ ጋር ስንነጋገር ድምጼን ከፍ አድርጌ በምናገርበት ወቅት ይታወቅሃል ድምጽህ እኮ ከተለመደው ለየት ይላል ትለኛለች፡፡ አንዳንዴም ትንሽ ጊዜ ቆይቼ እኔው እራሴ የድምጼ ከፍ ማለት የሰጣትን ትርጉም በማሰብ "ድምጼ ትክክል አልነበረም!" በማለት ይቅርታ እጠይቃለሁ።

---

[8] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 99, 100





ይህን ለምሳሌ ለማንሳት የሞከርኩት ከንግግራችን ይዘት ይልቅ ድምጻችን ከፍተኛ የሆነ መልዕክትን የማስተላለፍ አቅም እንዳለው ለማስገንዘብና ድምጻችንን ባለመቆጣጠር የተዛቡ መልዕክቶችንና የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመቀነስ እንዲቻል ለማሳየት ነው።

ከፍተኛውን ቁጥር የያዘ መልዕክት የሚፈጠርበት ሌላው የመልዕክት ቅብብሎሽ ሂደት የአካል ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ ነው። ከመልዕክታችን ይዘትና ድምጽ ጋር ተደምሮ የሰውነታችን እንቅስቃሴ የሚያስተላልፈው መልዕክት ከፍተኛውን ቦታ እንደሚይዝ መረዳት ይቻላል። የፊት መኮሳተርና ሳቅ፣ መወራጨትና አለመንቀሳቀስ፣ የደስታና የሐዘን ፊት፣ እጅን ኪስ ውስጥ ከቶና ሳይከቱ መናገር፣ ተቀምጦና ቆሞ መናገርና ሌሎችም የሰውነት እንቅስቃሴዎች እያንዳንዳቸው እንደ አካባቢው፣ እንደ ቤተሰብ ልምድና እንደ ባለትዳሮች ሁኔታ የተለያዩ መልዕክቶች ሊኖራቸውና ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ መገንዘብ ይኖርብናል። የሰውነት እንቅስቃሴያችን ላለመግባባት መንስኤ ሊሆን፣ አለመግባባትን ሊያባብስና ከፍተኛ ግጭት ሊፈጥር ሚችል እንደሆነ ማጤን ተገቢ ነው።

### 2. ምቹ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን አለመምረጥ

በባለትዳሮች መካከል ከኮሙኒኬሽን ጋር በተያየዘ ከሚፈጠረው ችግር አንዱ ምቹ ጊዜን አለመምረጥ ነው። የትኛው ጊዜ ምቹ ነው? በየትኛው ጊዜ ማለትም በማለዳ፣ በቀን፣ በማታ... መወያየት አለብን የሚለውን ጥያቄ በመመለስ አመች የሆነውን ምቹ የተግባቦት ጊዜ መምረጥ ለተሳካ የተግባቦት ሂደት የሚኖረው አስተዋጾ ከፍተኛ ነው፡፡ እንደ አርስተ ጉዳዩ አስፈላጊነት፣ አንገብጋቢነትና በጊዜው የትዳር አጋር እያከናወነው ያለውን ሁኔታ በመቃኘት ምቹ የሆነ የተግባቦት ጊዜ መምረጥ አስፈላጊ ነው። **90%** በተግባቦት መካከል የሚፈጠሩ ችግሮች ዋና ምክንያት ትክክለኛ ያልሆነን ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ለተግባቦት ክንውን ከመምረጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ።[9]

ትክክለኛ ጊዜ አለመምረጥ ችግር እንደሚፈጥር ሁሉ ምቹ የሆነ ቦታ አለመምረጥም ሌላው ችግር ፈጣሪ ጉዳይ ነው። በልጆችና በሰዎች ፊት፣ መኝታ ቤትና አልጋ ላይ፣ በሥራ ቦታ፣ ከቤት ውጭ ወጣ ብሎ የርዕስ ጉዳዩን አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት በመለየት ለተግባቦት ምቹ ቦታ መምረጥ አስፈላጊ ነው። ምቾትና ነጻነት የሚሰጥ ቦታ ባለመምረጣቸው በቀላሉ መግባባት የሚችሉበት ጉዳይ ግጭትና የከፋ ግንኙነትን የሚያሻክር ሁኔታ በጥንዶቹ መካከል እንዲፈጠር ያደርጋል።

ለመልካም ተግባቦት አስተዋጾ ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል ሌላው ትክክለኛና ምቹ ሁኔታዎችን መምረጥ ነው። ባለትዳሮች መልካም ግንኙነት እንዲኖራቸው ለሚነጋገሩበት ርዕስ ጉዳይ ምቹ ሁኔታን የመምረጥን አስፈላጊነት መረዳት አለባቸው። ያሉበትን ሁኔታ፣ በሐዘን፣ በደስታና በንዴት ስሜት፣ በውጥረትና በመረጋጋት፣ በሞትና

---

[9] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.

በወሊድ፣ በሴቶች የወር አበባ መምጣት ወቅት፣ በተለያዩ አደጋ ጊዜዎች፣ የተለያዩ እንግዳ ስሜቶች በተፈጠሩ ጊዜ ሁኔታዎችን አለመቃኘትና እንደ ሁኔታው ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አለማንሳት ላለመግባባትና ለግጭት ሊዳርግ ይችላል። እንደ ባለትዳር ባል የሚስትን ሚስት ደግሞ የባልን ሁኔታ መረዳት አለመግባባትንና ግጭትን ይቀንሳል።

**እርስ በእርስ መረዳዳት ይጠብቃል ከተለያየ ጉዳት !**

## 3. ስሜትን በነፃነት መግለጽ የማይቻልበት የተግባቦት ደረጃ ላይ መሆን

በትዳር ግንኙነታችን ያለ የተግባቦት ደረጃ ዝቅተኛና ነፃነት የሌለው ግንኙነት መሆን በቅርብ ወደ ትዳር በገቡ ተጋቢዎች መካከል ከሚፈጠሩ ችግሮች መካከል አንዱ ነው። በእርግጥ የተግባቦት ደረጃ በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ቢሆንም የእድገቱ ፍጥነት ግን በጥንዶቹ ማንነት፣ ትውውቅ፣ ግንኙነት፣ ብስለትና ግልጥነት ይወሰናል። በቅርብ የተጋቡ ባለትዳሮች በመካከላቸው ሊኖራቸውና ሊያሳድጉት የሚገባ የተግባቦት ደረጃን መለየትና መረዳት መቻላቸው ተገቢና አስፈላጊ ነው።

የተግባቦትን ሂደት ለማሳደግ የሚጠቅሙ አምስት የተለያዩ የተግባቦት ደረጃዎች እንዳሉ ይታመናል እነርሱንም እንደሚከተለው እንቃኛቸዋለን፡-[10]

**የመጀመሪያው ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነን ቅርበት** የሚያሳይ የተግባቦት ደረጃ ነው። ይህ የተግባቦት ደረጃ አንዳንድ ሐቆችን፣ ታሪኮችን፣ መረጃዎችን በማብራራት፣ ሰላምታን፣ ዜናን፣ የጋዜጣን፣ የመጽሔትን...አሳብና መረጃን በመለዋወጥ የሚገለጽ የተግባቦትደረጃ ነው። ከዚህ ያለፈ በግልጽ መነጋገርና መግባባት የማይችሉ ባለትዳሮች እጅግ በጣም ዝቅተኛ የሆነ ቅርበት ያላቸው ባለትዳሮች ናቸው። ዝቅተኛ ቅርበት ያላቸው ባለትዳሮች ከዚህ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከሆነ የተግባቦት ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ተግባቦታቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት ሊያደርጉ ያስፈልጋል።

ሌላው **ሁለተኛው ደረጃ ዝቅተኛ የሆነን ቅርበት** የሚያሳይ የተግባቦት ደረጃ ነው። ይህ የተግባቦት ደረጃ በባለትዳሮች መካከል ስለሌሎች ሰዎች ሃሳብንና አስተያየቶችን በመለዋወጥ የሚደረግ የተግባቦት ደረጃ ነው። ሁለተኛው ደረጃ ዝቅተኛ የሆነ ቅርበት ያላቸውና ስለሌሎች ሰዎች እንጂ ስለራሳቸው ለመነጋገር ግልጥነትና ነጻነት የሌላቸው ጥንዶች ያሉበትን የተግባቦት ሂደት የሚያሳይ ነው። በዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ጥንዶች እርስ በርሳቸው ስለራሳቸው መነጋገር የማይችሉ፣ ከተነጋገሩ የማይግባቡና የሚጋጩ ሊሆኑ

---

[10] David M. Ephraim. http://www.touchoffaith.org/family_ministry/communication/five_levels.Htm: The Five Levels of Communications accessed Feb.12, 2014.





ይችላሉ። በትዳር የተጣመሩ ጥንዶች ይህን ደረጃ የዘለለ ተግባቦት ሊኖራቸው ግድ ይላል።

**ሶስተኛው ደረጃ መካከለኛ የሆነ መቀራረብ** ያለበት የተግባቦት ደረጃ ነው። በዚህ ወቅት ባለትዳሮች በሌሎች ነገሮች ላይ የራሳቸውን ሃሳብ፣ አስተያየት፣ እምነት፣ እይታ በማቅረብ የሚነጋገሩበትና መረጃ የሚከፋፈሉበት ደረጃ ነው። ከሁለተኛው ደረጃ የሚሻለው ጥንዶቹ ስለሌሎች ሰዎችና ጉዳዮች ከመናገር ባለፈ የራሳቸውን አሳብ፣ አስተያየትና እምነት የሚገልጹበት ሁኔታ ላይ መድረሳቸው ነው። ጥንዶች እንደ ባለትዳር ግንኙነታቸውን ወደ ጠለቀ የተግባቦት ደረጃ በመቀራረብና በመግባባት ሊያሳድጉት ይገባቸዋል።

**አራተኛው ደረጃ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ** ያለበት የተግባቦት ደረጃ ነው። ባለትዳሮች በተወሰነ መጠን ስለራሳቸው ግልጽ የሚሆኑበትና ስለእያንዳንዳቸው የግል ያለፈና የአሁን ታሪክ በመወያየት የሚቀራረቡበት የተግባቦት ደረጃ ነው። ካሁን በፊት የነበራቸውና ያላቸው ልምምድ ምን ይመስል እንደ ነበር የራሳቸውን የግል መረጃና ስሜት አንዱ ለሌላው ማካፈል የሚጀምሩበት ወቅት ነው። ይህ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ ያለበት የተግባቦት ደረጃ ቢሆንም ባልና ሚስት እንደ ባለትዳር በመካከላቸው ያለው የተግባቦት ሂደት ወደ ሚቀጥለው ደረጃ እንዲያድግ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

**አምስተኛውና የመጨረሻው ደረጃ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መቀራረብ** የሚታይበት የተግባቦት ደረጃ ነው። በዚህ የተግባቦት ደረጃ ባለትዳሮች ማንነታቸውን በነፃነት የሚገልጹበትና በግል ስለሚሰማቸው የውስጥ አሳብ ያለምንም ፍርሃት መናገር የሚችሉበት ነፃነት የሚንጸባረቅበት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ጥንዶቹ ከአእምሮአቸው ከመናገር የውስጥ ስሜታቸውን ወደ መናገር የሚሸጋገሩበትና የልብ ሰዎች የሚሆኑበት ደረጃ ነው። ባለትዳሮች ለግልም ሆነ ለትዳራቸው ያሰቡትንና ያቀዱትን እንዲሁ በነፃነትና በግልጥነት ወደ መነጋገር የሚደርሱበት ደረጃ ነው። ይህን በመገንዘብ በየጊዜው የተግባቦት ከህሎት ከፍ እንዲል የሚቻለውን ዋጋ በመክፈል መቀራረብ አስፈላጊ ነው ።

በቅርብ የተጋባን ጥንዶች የተግባቦት ደረጃችን የት ላይ እንዳለ፡- ምን ያክል በግልጥነትና በነፃነት እየተግባባን ነው? የተግባቦት ደረጃችን ወደ ከፍተኛና ወደ ላቀ ደረጃ እንዳይደረስ እንቅፋት የሆነብን ምንድን ነው? ለመልካም ተግባቦትና የበለጠ ለመቀራረብ ምን ጥረት እያደረግን ነው? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅና እርስ በእርስ ያለምንም ፍርሃት የውስጥ ስሜትን በመግለጥ የልብ ሰው ወደ መሆን ለማደግ ማሰብ፣ ለመሻሻል ጥረት ማድረግና በየጊዜው የተግባቦት ክህሎታችንን ከፍ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ለጤነኛና ደስተኛ ትዳርና ቤተሰብ መፈጠር መሠረታዊ ምክንያት ነውና!!

## 4. ጥሩ አድማጭ አለመሆን

ለመልካም ተግባቦት አንደኛው ምትክ የለሽ አስፈላጊ ነገር ጥሩ አድማጭ መሆን ነው። ያዕቆብ በመልክቱ እንዲህ ይላል፡- *"ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤"* /ያዕ 1: 19/፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ጥሩ አድማጭ ለመሆን ትኩረት ሲሰጡ አይታዩም፡፡ ጥሩ አድማጭ እንዳንሆን ያደረጉን የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህን የጥሩ አድማጭነት እነቅፋቶች ራሳችንን በመመዘን ለይተን ማግኘትና ለማስወገድ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

ከጥሩ አድማጭነት እንቅፋቶች መካከል አንዱ ሳይሰሙ ለመናገር መዘጋጀትና አስደንጋጭ ቃላትን መጠቀም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሰማ መልስ የሚሰጥን ሰው *"ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል።"* /ምሳሌ 18: 13/ በሚለው የጥበብ ምክሩ ሳይሰሙ መናገር ወይም መልስ መስጠት የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ብቻ ሳይሆን ስንፍናና በኋላ የሚያሳፍር መሆኑንም ግልጥ ያደርጋል፡፡ ሌላው በግል ያለን አስተሳሰብና የንግግር ዘይቤ ላይ ብቻ በመመርኮዝ ለሌላው አካል ንግግር እድል ፈንታ አለመስጠት ጥሩ አድማጭ ያለመሆን መገለጫ ነው። ከእነዚህም በተጨማሪ የተናጋሪው ወይም የአድማጩ ሰው ጾታ፣ ዘር፣ ዕድሜ፣ ያለፈ ታሪክና ልምምድ ጥሩ አድማጭ ለመሆን እንቅፋትና ምቾት የማይሰጥ ሊሆንበት ይችላል።[11]

በባልና በሚስት የተግባቦት ሂደት ውስጥ የጾታ ልዩነት አንዱ የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡ሴቶች በክፉና በመልካም ቃላት በንግግር መካከል መልስ የመስጠት፣ ወንዶች አንገት በመነቅነቅ ተቃውሞን ወይም ምላሽን የማሳየትና ብዙ ጊዜ በንግግር መካከል አቋርጦ እርማት የመስጠት አጉል ልማዳቸው የጥሩ አድማጭነት ጠንቅ ሊሆንባቸው ይችላል። ሌላው በባለትዳሮች መካከል የሚፈጠሩ ውስጣዊ የሆኑ የስሜት ትግሎች ማለትም ፍርሃት ሲኖርብን፣ ጭንቀት ሲበዛ፣ ስጋት ሲጨምርና በውስጣችን በሆነ ምክንያት ጥርጣሬ ሲሞላ የማዳመጥ ፍላጎታችንና ችሎታችን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።[12]

መጥፎ ጊዜ ማለትም ትክክለኛ ጊዜን አለመምረጥ ለምሳሌ አካላዊ ድካም፣ የሐዘን ወይም ከፍተኛ የሆነ የደስታ ስሜት በሚፈጠርበት ወቅት የጥሩ አድማጭነት ትኩረት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል። ሌላው ሳይጠቀስ የማይቀረው ከራሳቸው ፍላጎት፣ እይታ፣ እሴትና እምነት አንጻር ብቻ የሚሰሙትን ነገር በመምረጥ የሌላውን አካል ፍላጎት፣ እይታና አስተያየት ለመስማት አለመፈለግ የጥሩ አድማጭነት እንቅፋት ሊሆን ይችላል።[13]

---

[11] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110

[12] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110

[13] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 103-110





## 5. እውነትን በፍቅር አለመናገር

በኮሙኒኬሽን እረገድ በቅርብ በተጋቡ ጥንዶች መካከል ከሚፈጠረውና ሊፈጠር ከሚችለው ችግር አንዱ እውነትን አለመናገር ነው። እውነትን ብናገርና እውነቱ ቢገለጥ በትዳር ጓደኛየ ላይ ጥሩ ያልሆነ ስሜት ሊፈጠር ይችላል የሚል አሳብ በሚኖርበት ጊዜ እውነትን የመደበቅ ተግባር በባለ ትዳሮች መካከል ይከሰታል፡፡ ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ተግባር ትክክለኛነቱ ባልተረጋገጠ ግምት እውነትን በመሰወር የግብዝነት ተግባቦት የማድረግ ጥረት ነው።

ሌላው በአንዳንድ ጥንዶች ዘንድ የሚታየው እንደሚገባ ከመተዋወቅ የተነሳ እውነቱ ቢገለጥ ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባትና ግጭት በመፍራት እውነትን ደብቆ በማመቻመች ለመግባባት መሞከር ነው። ሁለቱም ጤንነት የጎደላቸውና እውነተኛ ያልሆኑ የባለትዳሮች የመልካም ግንኙነት እንቅፋቶች ናቸው። ውሎ አድሮ እውነቱ በተለያየ መንገድ ገሃድ ሲወጣ እውነትን በመደበቅ ይመጣል ተብሎ የታሰበው መግባባት በመረረ አለመግባባት ይተካል፡፡ ከዚህም ባለፈ ከስተቱ ወደፊት ለሚደረገው የተግባቦት ሂደት መሠረታዊ እንቅፋት ይሆናል፡፡ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ልምድ፣ ባሕርይና አስተሳሰብ ያላቸው ባለትዳሮች በጊዜ ራሳቸውን የማሻሻል ጥረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

እውነትን መናገር ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል። እውነትን መናገር ለጊዜው አመኔታ ሊያሳጣ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ እውነትን መናገሩ በአድማጮቹ ዘንድ ሊፈጥርበት የሚችለውን ችግር እንዲህ ሲል ገልጿል፡- *"እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለ ሆንሁ አታምኑኝም።"* /ዮሐ 8: 45/ *"ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።"* /ኤፌ 4: 25/፡፡ በባህላችን እውነትን በግልጥነት ከመናገር ይልቅ ሰላም ሳይሆን ሰላም ነው፣ ትክክል ሳይሆን ትክክል ነው ማለትና ተቃራኒውን ምላሽ ግን ጉዳዩ ለማይመለከተው ሌላ ወገን መናገር ወይንም ወደ ሐሜት መግባት የተለመደ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ልምምድ ባህል በማድረግ ሰዎች በሚኖሩበት በዚህ ዘመን እውነትን መናገርና መስማት ከባድና አስቸጋሪ ቢሆን ምንም የሚያስገርም ነገር አይደለም።

እውነትን በመነጋገር በአጭር ሊቀጭ የሚችል ችግር ሰነባብቶ ለቤተሰብ መበተን ምክንያት የሚሆን ከፍተኛ የትዳር ችግርን ያስከትላል። የተሰወረ እውነት አንድ ቀን መገለጡ አይቀሬ ነው። እውነት በተገለጠ ጊዜ አንዱን አካል ነፃ ሲያወጣ ሌላውን አካል ሊያጋልጥና ሊያዳልጥ ይችላል። እውነትን ባለመነጋገር ከትዳር ጓደኞችን ጋር የሚኖረንን የተግባቦት እድገት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲቆም ማድረግ የለብንም፡፡ ይህ እንዲሆን ከፈቀድን በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ከፍተኛ አለመግባባትና ግጭት መንስኤ ሊሆን ስለሚችል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። *"እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው"* /ዮሐ 8፡ 32/

እውነትን አለመነጋገር ብቻ ሳይሆን እውነትን የምንናገርበት መንፈስ ሌላው የአለመግባባትና የግጭት መንስኤ ነው። እውነት ብቻውን በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ሕመም ሊፈጥር ይችላል፡፡ ነገር ግን ፍቅርና ምህረት ቢታከልበት የሚፈጠረውን ሕመም ይቀንሰዋል። እውነትን በፍቅር፣ በምህረትና በትዕግስት መነጋገር፣ መያዝና መግባባት አስፈላጊ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ክርስቲያኖች *"ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤"* /ኤፌ 4: 15/ በማለት የመከራቸው እውነትን በፍቅር የመግለጥን አስፈላጊነት እንዲረዱ በመፈለጉ ነበር፡፡

## 6. ቴክኖሎጅን ተጠቅሞ ለመግባባት ጥረት በሚደረግበት ወቅት እንደታሰበው ሳይሆን ሲቀር

በአሁኑ ዘመን የመረጃና የኮሙኒኬሽን መንገዶች በብዛት መገኘታቸውና የመለወጥ ፍጥነታቸው ከመቼውም ዘመን በበለጠ የጎላ ነው፡፡ እንደዚህ ዘመን ብዙ ሰዎች የቴክኖሎጅ ተጠቃሚ የሆኑበት ጊዜ የለም። ቴክኖሎጅ ፈጣን በሆነ መንገድ ለመገናኘት፣ መረጃና መልዕክት ለመለዋወጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ እየሰጠ ይገኛል። ቴክኖሎጅ አፈራሽ የሆነውን የመገናኛ ዘዴ ተጠቅሞ አሳብን መለዋወጥ ጠቀሜታው አጠያያቂ አይደለም ነገር ግን ማንኛውንም ዘዴ ተጠቅመው ለመገናኘትና ለመግባባት የሚሞክሩ ጥንዶች በልባቸው ውስጥ ያለውን የልብን ቅንነት መግለጽ ባለመቻል የሚፈጠር አለመግባባት በለውጡ ሂደት ውስጥም በመታየት ላይ ያለ ችግር ነው።

ቴክኖሎጅ አፈራሽ የሆኑ የመገናኛ ዘዴዎችንና ማሕበራዊ ድረ ገጾችን ተጠቅሞ ግንኙነት ለመፍጠርና ለመግባባት በሚደረገው ሙከራ ቴክኖሎጅው የሚጠቀመውን የተለየ ቋንቋ ለምሳሌ የእንጊሊዘኛን የቋንቋ ተጠቃሚው በሚገባ ባለማወቁ ምክንያት የሚገጥመው የቋንቋ ውስንነት በባልና ሚስት መካከል የተግባቦት እንቅፋት ይሆናል፡፡ ይህ የቴክኖሎጂውን ቋንቋ ያለማወቅ የቋንቋ ውስንነት የሚፈጥረው የትርጉምና የመረዳት ልዩነት ባለትዳሮች እንዳይግባቡ ምክንያት ሊሆን ብሎም ከፍተኛ ለሆን

**ግምታችን ሊሳሳት ይችላልና ምክንያቱን ጠይቀን ባልተረዳነው ሁኔታ ላይ ሌላውን አካል ፈጥኖ ከማኩረፍ፣ ከመቆጣትና ከመፍረድ እንጠበቅ!**

ግጭት መንስኤ ሊሆን ይችላል። በስልክ በመነጋገር፣ በስልክ የጽሁፍ መልዕክት በመጻጻፍ፣ ኢሜል በመደራረግና ማሕበራዊ ድረ ገጽ በመጠቀም አሳብን ለመግለጥና መልዕክት ለመለዋወጥ በሚደረገው ሂደት አንዳንድ ጊዜ የሰው ሥራ ፍጹም አይደለምና በኔት-ዎርክ ላይ በሚፈጠሩ የመልዕክት ቅብብሎሽ እንቅፋቶች፣ በቂ የሆነ አገልግሎት የአለማግኘት ወይም ፈጽሞ አገልግሎት ባለመኖሩ ምክንያት የተላከው ፈጽሞ ላይደርስ ወይም መልእክቱ በከፊል ሊሸራረፍ ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ተከስቶ የተላከው ፈጽሞ





ሳይደርስ ሲቀር ወይም ከተፈለገው ወቅት ዘግይቶ ሲደርስ፣ የተላከ መስሎን ሳይላክ ሲቀር ወይም ስልክ የጠራ እየመሰለን ሌላው አካል ላይ ጥሪው ሳይደርስ ሲቀር እንዲሁም በተፈጠረ ስህተት ምክንያት ወዳልተፈለገ ቦታ መልዕክቱ ሲላክ በባልና በሚስት መካከል የተዛባ ግንዛቤ፣ ጥርጣሬ፣ አለመተማመን፣ አለመግባባትና ግጭት ሊፈጠር ይችላል።

ሌላው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የምንጠቀምባቸው የስልክና የማሕበራዊ ድረ ገጾች በየጊዜው ተጠቃሚ አለመሆን ሌላው ተጠቃሽ የግጭት መንስኤ ነው። የሚጠቀሙበትን ስልክ ድምጽ በመቀነሳቸውና በማጥፋታቸው ከዚያም ለረጅም ሰዓት ስልክና ኢሜል መመልከት ባለመቻላቸው ምክንያት አንዱ የትዳር አካል ግጭት ሊፈጠር ይችላል። በሥራ፣ በስብሰባ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመሆንና በማይመች ሁኔታ ውስጥ በመገኘት የስልክ ጥሪና መልዕክት አለመመለስ በሌላው አካል ላይ ቁጣ፣ የስሜት መለወጥና የማኩረፍ ሁኔታ ሊፈጠርና ከዚያም ለግጭት ምክንያት ሊሆን ይችላል። እነዚህን የግጭት መንስኤዎችን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ያለብን የግጭት ምክንያቶችን ለመቀነስና እርስ በርስ ለመረዳዳት እንድንችል እንጂ ለግጭት ፈቃድ ለመስጠት አይደለም። ይህ ክስተት ሲያጋጥመን ቶሎ ብለን በቁጣና በብስጭት የትዳር አጋርን ከማነጋገር ይልቅ በእርጋታ ለምን ሁኔታው እንደተፈጠረ በመጠየቅ ምክንያቱን ለማወቅ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ከመቆጣትና ከመፍረድ በፊት ምክንያቱን ማወቅ ከፍርድና ከግጭት ይጠብቃል። ካልተመለሰው የስልክ ጥሪና መልዕክት ይልቅ የትዳር አጋር ይበልጣልና አንዱ ለሌላው በማሰብ ደህንነትን በፍቅር መጠያየቅና ቁጣን ማብረድ ብስለትና መንፈሳዊነትም ነው።

## III. በተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ላይ ለሚፈጠሩ የግጭት መንስኤዎች መፍትሔዎች

ለጤነኛና ለደስተኛ ትዳር መልካም ተግባቦት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። መልካም ተግባቦት በሌለበት አብሮ መኖር፣ መስራት፣ መቀመጥ፣ ረጅም ጉዞ መጓዝና ሰላምና ነፃነት የተሞላው ስሜት ሊኖር አይችልም። በመልካም ተግባቦት ጠንካራ፣ ቀጥተኛና ግልጥነት የሞላበት ግንኙነት እንዲኖረን ማድረግ እንችላለን፡፡ በየጊዜው የተግባቦትን ክህሎት በማሳደግና አለመግባባትንና ግጭትን በመቀነስ በጋራ መኖር አስፈላጊ ነው። ከዚህ በመቀጠል የምንዳስሳቸው እውነቶች የተግባቦትን ክህሎት ለማሳደግና የተሳካ ግንኙነት በትዳር ውስጥ እንዲኖረን ለማድረግ ከፍተኛ ገንቢ ሚና ይኖራቸዋል፡-

### 1. መገንዘብ፡- መልካም ተግባቦት የጤነኛና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ እንደሆነ መገንዘብ

መልካም ተግባቦት እንዲኖር የመጀመሪያው ሊስተካከል የሚገባው አስተሳሰባችን ነው። መልካም ተግባቦት የጤነኛና የደስተኛ ባለትዳሮች መለያ እንደሆነ መገንዘብና

በቀጣይ የተግባቦት ክህሎትን ለማሻሻል ራስን ማዘጋጀት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። የጤነኛና ደስተኛ ትዳር መለያው ጥንዶቹ እርስ በርሳቸው በነፃነት ሰፋ ላለ ጊዜ መወያየትና መነጋገር የሚችል አቅም ያላቸው መሆኑ ነው። ይህም አስፈላጊ የሚሆነው ባለትዳሮች እንዲወያዩ የሚያደርጓቸው ሰፊና ብዙ የመነጋገሪያ ርዕሶች ስላሏቸውና ስለሚኖሯቸው ነው።

ከፍተኛ የሆነ የተግባቦት ደረጃ ላይ የደረሰ ውጤታማ የተግባቦት ሂደት እንዲኖራቸው ጥረት የሚያደርጉ ባለትዳሮች በጋራ በሚነጋገሩ ወቅት አንዱ የሌላውን የጠለቀ ስሜት መረዳት ይጀምራሉ። የተለያዩ የመግባቢያ መንገዶችን በመጠቀም የመግባባት ክህሎታቸውን ያሻሽላሉ፡፡ አንዱ የሌላውን ቋንቋና ስሜት በመገንዘብ እርስ በእርስ ስለሚረዳዱ፣ ጥንቃቄ ስለሚያሳዩና ስለሚጠባበቁ በመካከላቸው የሚካሄደው ተግባቦት ወደ ላቀ ደረጃ ያድጋል። ይህ የጤነኛና የደስተኛ ትዳር መለያ የሆነው ቁም ነገር በትዳራችን እንዲገለጽ ግንዛቤያችን ከፍ ሊል ይገባል። ግንዛቤያችን ከፍ እንዲልም በትዳር ውስጥ ያለን ጥንዶች አስበንበት በጋራ መትጋት ይጠበቅብናል፡፡

## 2. *መረዳት፡- የተግባቦት መሠረታዊ እውነቶችን መረዳት*

ለመልካም ተግባቦት ክህሎት መኖር በማዳመጥና በመስማት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት መረዳት ጠቃሚ የተግባቦት መሠረታዊ እውነት ነው። መስማት የምንፈልገውን አሳብ ይዘት ወይም መረጃ የያዘ ሲሆን ማድመጥ ግን ስለሚናገረው ሰው ማሰብንና መጨነቅን ያካተተ ነው። መስማት ማለት በንግግር ወቅት በውስጣችን ምን እንደሚከናወን ማሰብ ላይ ያተኮረ ሲሆን ማዳመጥ ግን የተናጋሪውን ሰው ስሜት ለመረዳት መጣርና ለሚናገረው ሰው ሙሉ ትኩረት መስጠትን ያካትታል።

**የማዳመጥ ምንነት፡-** የትዳር አጋር በሚናገርበት ወቅት ምን መናገር እንዳለብን ማሰብንና ጣልቃ ገብተን መናገርን በማቆም ተናጋሪውን ለመስማት ሙሉ ትኩረትን መስጠት የማዳመጥ ሂደት ነው።[14] ባግባቡ ሳይሰሙ መናገር መጽሐፍ ቅዱስ **በምሳ 18፡ 13** *"ሳይሰማ ነገርን በሚመልስ ስንፍናና እፍረት ይሆንበታል።"* ብሎ እንደተናገረው ውጤቱ ስንፍናና እፍረት ይሆናል። ማዳመጥ ተናጋሪ የሆነው የትዳር አጋር ምን፣ ለምንና እንዴት እንደተናገረ ሳይፈርዱ ሙሉ በሙሉ በመረዳት መቀበል ነው። ይህ ሲባል በሁሉ ነገር ተስማምተናል ማለት አይደለም! በሃሳብ፣ በድምጽ፣ በአገላለጽ የምንሰማው ነገር አንዳንድ ጊዜ ላይመቸን ይችላል፡፡ ነገር ግን ማዳመጥ ይህን ሁሉ ከፈራጅነት በጸዳ ልቦና መስማትን ይጠይቃል። ማዳመጥ የመላ ሰውነት እንቅስቃሴን፣ በቃላት የማይገለጹ አገላለጾችንና የአይን ምልከታን ሁሉ በመከታተል እውነተኛውን መልዕክት ለማግኘት የማድረግ ጥረት ነው።[15]

[14] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97
[15] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97





**ማዳመጥ**፡- የተናጋሪውን የመልዕክት ይዘት፣ እውነተኝነትና ስሜት በተናጋሪው ስሜት ውስጥ ሁኖ መስማት፣ የሌላውን ስሜት፣ ፍላጎትና አስተያየት ለመረዳት በመጣር ሙሉ የሆነ ትኩረትን የሚጠይቅና በየጊዜው እየተማርነው የምንሄደው ችሎታ ነው።[16] **ሳይኮሌጅስቶች፡-** የሰዎች የማዳመጥ ችሎታ ከመናገር ችሎታቸው ጋር ሲነጻጸር አምስት እጥፍ እንደ ሆነ ይናገራሉ። አንድ ሰው **ሁለት መቶ** ቃላት ቢናገር **አምስት እጥፍ** ማለትም **አንድ ሺ** ቃላት መስማት ይችላል **(200 ቃላት መናገር X 5= 1000 ቃላትን መስማት)**፡፡[17] የእግዚአብሔር ቃል ከመናገር ይልቅ ለመስማት ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ እንዲህ ሲል ያረጋግጣል፡- *"ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤..."* **/ያዕ 1፡ 19/**፡፡

በመስማትና በማዳመጥ መካከል ልዩነት አለ፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። እየሰማን እያለ እያዳመጥን እንዳይመስለን ወይም እያዳመጥከኝ/ሽኝ/ አይደለም በሚል እሰጣገባ እንዳይፈጠር ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ማለትም ስልክ፣ አይፓድ፣ ኮምፒዩተርና ሌሎች ተቀራራቢ የሆኑ ትኩረት የሚስቡ መሳሪዎችን በውይይት ጊዜ ከአካባቢያችን ማስወገድ ተገቢ ነው፡፡ ይህንን ማድረግ መሳሪያዎችን እየነካኩና እየተጠቀሙ ትኩረት ባለመስጠት ምክንያት አለመግባባት እንዳይፈጠርና ይበልጥ ግጭቱ እንዳይባባስ ይረዳል። *"ጆሮህ ጥበብን እንዲያደምጥ ታደርጋለህ፥ ልብህንም ወደ ማስተዋል ታዘነብላለህ"* **/ምሳሌ 2፡ 2/**፡፡ መግባባት ለሚፈልጉ ባለትዳሮች ጥሩ አድማጭ መሆን ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው።

**መግባባት ለሚፈልጉ ባለትዳሮች ጥሩ አድማጭ መሆን ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነው!!**

መጽሐፍ ቅዱስም አስቀድሞ እንደተገለጠው በያዕ 1፡ 19 ላይ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ መሆን እንዳለበት ግልጥ መመሪያ ሰጥቶናል፡፡ ለዚህ አምላካዊ መርህ ራስን በማስገዛትና በመታዘዝ መኖር በትዳር ውስጥ ለሚኖሩ ጥንዶች የጋብቻ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ክርስቲያናዊ ኃላፊነታቸውም ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ይህንን ኃላፊነት የመወጣቱን ተግባራዊ ሕይወት የሚለማመዱበት የመጀመሪያው የመታዘዝ መሠረት መጣል ያለበት ደግሞ በቤታቸው ውስጥ ነው፡፡ *"... እነሆ፥ መታዘዝ ከመሥዋዕት፥ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል።"* **/1ኛሳሙ 15፡ 22/**

[16] Wright H. Norman: communication key to your marriage page 96, 97
[17] Chapman, Gary. Marriage Works helping couples God's way, publishing light university: Forest, Virginia, 2011.

## 3. መምረጥ፡- ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን መምረጥ

ለተሳካ ተግባቦት ሂደት ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ምቹ ሁኔታን ባለመቃኘት የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በቀላሉ ሊፈቱ የነበሩ ግጭቶች ያልተፈለገ አቅጣጫ እንዲይዙ የማድረግ ተጽዕኖ ስላላቸው ሊታሰብባቸው ይገባል። *"ለመቅደድ ጊዜ አለው፥ ለመስፋትም ጊዜ አለው ዝም ለማለት ጊዜ አለው፥ ለመናገርም ጊዜ አለው"* /መክ 3፡ 7/ የሚለው የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገረው ለመግባባት የምንናገረውንና ልንደመጥበት የምንችልበትን ጊዜ፣ ቦታና ምቹ ሁኔታን መምረጥ ብልህነት ነው። *"የወርቅ እንኮይ በብር ፃሕል ላይ የጊዜው ቃል እንዲሁ ነው።"* /**ምሳሌ 25፡ 11**/ የሚለው የመጽሐፈ ምሳሌ ምክር ግልጽ እንደሚያደርገው የጊዜው ቃል ወይም መልዕክት መልካም ነው። *"ሰው በአፉ መልስ ደስ ይለዋል ቃልም በጊዜው ምንኛ መልካም ነው!"* /**ምሳሌ 15፡23**/

ትክክለኛ ጊዜና ቦታ እንዳንመርጥ ከሚያደርጉን ምክንያቶች መካከል የቁጣ ስሜት፣ ያለመረጋጋት መንፈስ፣ ለነገሮችና በነገሮች ላይ ትዕግስት ማጣት፣ ከኋላ በመሆን የሚገፉፉን ሶስተኛ ወገን ሰዎች መኖራቸውና የነገሩ አስቸኳይነትና አንገብጋቢነት ወ.ዘ.ተ. የሚጠቀሱ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ግፊቶች ቢኖሩም ግንኙነታችንን በመልካም ተግባቦት ለማስቀጠል ግን ትክክለኛ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን መምረጥ የአድማጭን ሁኔታ መረዳትና አንዱ የሌላውን ስሜት መጠበቅ የግድ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ ለሕዝቡ፣ ለካህናት… ምቹ የሆነ ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ በመጠቀም ሊገባቸው በሚችል ምሳሌና ማብራሪያ መልዕክቱን ያስተላልፍ ነበር። *"መስማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር፤ …"* **ማ4:33**

## 4. መለወጥ፡- በየጊዜው የተግባቦት ደረጃዎችን ከፍ ለማድረግ መለወጥ

ሌላው የተግባቦት ደረጃዎች በባለትዳሮች መካከል እንዲኖሩና በየጊዜውም እያደጉ እንዲመጡ ለለውጥ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው። ይህ የተግባቦት እድገት ወደ ሕብረታችን እንዲመጣ ለውጥ የሚያሻቸው ጉዳዮችን ማለትም ሌላው ሲናገር የማዳመጥ እንቅፋቶችን ለማስወገድና የትዳር አጋሮች ምን እንደሚሰማቸው የመረዳት አቅምንና በሁለንተናዊ አካል ለማድመጥ ራስን የመስጠት ሂደትን ለይቶ በማወቅ ለለውጥ የመሥራት ፍላጎት ያለንና የምንተጋ ሰዎች መሆን አለብን፡፡ ነገሮችን ግልጥ በማድረግ ማስተዋል፣ በትክክል ማዳመጣችንን በማንጸባረቅና ደግሞ ለማዳመጥ ፍላጎትን በማሳየት ለውጣችንን ማሳየትና ለውጥ በሚያሻው ጉዳይ ላይ ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆንም ተገቢ ነው።

ትዕግስት በማጣት ከሚፈጠሩ አለመግባባቶች ለመጠበቅና ወደ ተባባሰ ግጭት ላለመግባት ታጋሽ መሆን አስፈላጊ ነው፡፡ በመታገስ መግባባት ላይ ለመድረስ፡- ፈጥኖ ፍርድን ከማስተላለፍ፣ ያልታሰበበትን ተጨማሪ አሳብ ድንገት በውይይት መሃል ከማቅረብ፣ ለግላችን የተስማማን አሳብ ብቻ ትክክለኛ እንደ ሆነ አድርጎ ከመቁጠር፣ ምን አገባኝ በማለት ከነገሮች ትኩረትን ፈጥኖ ከማውጣት፣ አዕምሮን ከመዝጋት፣





የምኖትን መግለጫን ፈጥኖ ለመስማትና ለማሰማት ከመጣደፍ፣ የተለያዩ ትርጉሞችን ባልገባን ነገር ላይ ከመስጠት፣ ቸኩሎ ሳይሰሙ ለመመለስና ለማመጣጠን ብሎ ፈጥኖ ከመሸሽ ራሳችንን ነፃ ለማውጣትና ለመለወጥ ጥረት ማድረግ በጣም ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡

እንዴት ንግግራችን መጀመርና በመልካም ንግግር መልካም ተጽዕኖ በማምጣት መግባባት እንችላለን? የሚል አግባብነት ያለው ጥያቄ በማንሳት ምላሽ ማግኘት መቻል ለተሳካ ተግባቦት መኖር አጋዥ ለውጥ ልናመጣ በምንችልበት መስመር ላይ እንድንሠራ ወደሚያስችል አቅጣጫ ይመራናል። ለመልካም ንግግር፡- ልንነጋገርበት የምንፈልገውን ርዕሰ ጉዳይ መለየት፣ የትኛው ትክክለኛ ጊዜ እንደሆነ መምረጥ፣ የትዳር አጋርን በአግባቡ ማናገር፣ አሳባችንን በጥሩ መልኩ ማጠቃለል፣ ምላሽ ለመስማት ጊዜ መስጠት፣ ለትዳር ጓደኛ አክብሮትን ማሳየት፣ ሃሳብን ለመግለጥ የሰውነት እንቅስቃሴን በአግባብ መጠቀም፣ የትዳር አጋርን የመግባቢያ መንገድ ግምት ውስጥ ማስገባትን አለመርሳት፣ የትዳር አጋርን ፍላጎቶች መጠበቅ፣ በተቻለ መጠን ንግግራችን ተደማጭነት ያለው እንዲሆን በሚስብ መልኩ ማቅረብ፣ እውነተኛ ሁኖ መቅረብ፣ ለመቀባበልና ለመደሰት አጥብቆ መፈለግ፣ ንግግርን በአድናቆትና ተስፋ ጫሪ በሆነ አቀራረብ መጀመርና መግባባት መቻል የንግግር ግብዓቶች ሆነው በበሰለ መንገድና በተሟላ ሁኔታ መቅረብ አለባቸው፡፡[18]

## 5. መለማመድ፡- የተግባቦት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን በመረዳት መለማመድ

በትዳር ውስጥ ግጭትን ቀናሽ መልካም ተግባቦት እንዲኖር ስለመልካም ተግባቦት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችና መርሆችስ ምንድን ናቸው? … የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስና ያሉትን እውነቶች በተግባር መለማመድ ተገቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከምናገኛቸው የተግባቦት መርሆዎች አንዱ አንደበትን መግራት ነው፡፡ አንደበትን ያለመግራት ችግር ብዙ ጊዜ ኃይለኛነት በሞላበት ንግግር ይገለጣል፡፡የቃላት (የንግግር) ኃይለኛነት በተለያዩ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተገልጧል። ለሌሎች ሰዎች የምንናገረውን ቃል ጉልበት ለማሳየት ሌሎች ጉልበት ያላቸውን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ **ያዕ.3፡ 3-10** የምላስን ጉልበት ***"ከጉልበታም ፈረስ"*** ና ***"ከግዙፍ መረከብ"*** ጋር ያነጻጽረዋል፡፡

የጉልበታም ፈረስ ጉልበተኝነት በልጓም የሚገራ ሲሆን የግዙፍ መርከቦች እንቅስቃሴ ደግሞ ምንም ያክል ትልቅ ቢሆኑና ማዕበልም ቢያናውጣቸው እንኳን በመቅዘፊያ ይመራል፡፡ ያዕቆብ በመልክቱ እንደገለጠው አንደበት ግን ከሁለቱም ምሳሌዎች ይለያል፡፡ ምክንያቱም አንደበት ለመገራት የሚያስቸግር በብልቶቻችን

[18] Focus on the family, the first five years of your marriage, PP.216-218

መካከል አመጸኛ ዓለም በመሆን ስጋን ከማሳደፉም በላይ የፍጥረትን ሩጫ ያቃጥላል፡፡ ይህንን እውነታ በማሳየት ያዕቆብ አንደበትን ጫካን ሁሉ በሚያቃጥል ትንሽ እሳት በመመሰል *"የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት"* ይለዋል፡፡ አስፈሪ የሆኑ እንስሶችና መርከቦች ሰዎች በሠሯቸው የመቆጣጠሪያ መሳሪያዎችና ሰዎች በሚሰጧቸው ስልጠናዎች ይገራሉ፡፡ ነገር ግን ሌሎችን አስቸጋሪዎች የሚገራበት መሳሪያ መፍጠር የቻለው ሰው ምላሱን ለመግራት እንደሚቸገር ያዕቆብ በመልዕክቱ ያሳየናል።

የአንደበት አስቸጋሪነት የገባው ሌላው ሰው ሐዋርያው ጴጥሮስ በ1ኛጴጥ 3፡ 10 *"ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው ምላሱን ከክፉ ከንፈሮችንም ተንኮልን ከመናገር ይከልክል..."* ሲል ይመክራል፡፡ በየጊዜው ስለራሳችን የምንናገረው ቃል ለቁጣ፣ ለጭንቀት፣ ለበደለኝነት ስሜትና ለድብርት ተጋላጭ እንድንሆን ሊጋብዘን ይችላል። በተደጋጋሚ ስለራሳችን የምንናገረው የሕይወታችን አስተሳሰብ፣ እሴትና እምነት ወደ መሆን ሊለወጥ ይችላል።

ከመናገር በፊት ማሰብና አንደበታችንን መግራት በንግግር የትዳር አጋርን እንዳንጎዳ ይጠብቀናል፡፡ የአንደበትን ቃል መጠበቅን ለመለማመድ *"አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፥ የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።"* /መዝ 141፡ 3/ ብሎ ዘማሪው እንደጸለየው ብርቱ ጸሎት ያስፈልገናል። ምክንያቱም *"እንደሚዋጋ ሰይፍ የሚለፈልፍ ሰው አለ የጠቢባን ምላስ ግን ጤና ነው። "* /ምሳ 12፡ 18/ እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል በልፍለፋችን የምንዋጋ ሰዎች ሳይሆን በጠቢብ ምላሳችን ለትዳር ጓደኞችንና ለቤተሰባችን ጤና ምክንያት እንድንሆን የሚያስችለን የእግዚአብሔር ፀጋ ያስፈልገናል፡፡ አንዴ ከአንደበታችን የወጣ ቃል አይመለስምና በምናወጣቸው ቃላት የምንጸጸት እንዳንሆን እንጠንቀቅ። ከአንደበታችን ያወጣነውን ቃል ምናልባት ልናብራራ፣ ልናስተባብል ወይም ይቅርታ ልንጠይቅበት እንችላለን እንጂ መመለስ አንችልም። ቃላት ግን አንድ ጊዜ ከአንደበታችን ከወጡ የፈጠሩትን ችግር ያስተካከልን ቢመስለንም እንኳን በአድማጩ አዕምሮ ውስጥ በመቆየት ጊዜ እየጠበቁ ቆስቋሽ አጋጣሚ ሲያገኙ የሚፈነዱ በትዳር ውስጥ መልካም ተግባቦትን የሚያቃውሱ ግጭት ፈጣሪ ፈንጅዎች ይሆናሉ፡፡ *"አፉንና ምላሱን የሚጠብቅ ነፍሱን ከመከራ ይጠብቃል።"* /ምሳሌ 21፡ 23/

ከዚህም በተጨማሪ ሐሰትን መለማመድን ከሕይወታችን ማስወገድና እውነተኛነትን የዘወትር ልምዳችን ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ እግዚአብሔር የሚጠላውን በመጥላት የሚወደውን በመውደድ ቃሉን መታዘዝን መለማመድ ያስፈልጋል። መጽሐፈ ምሳሌ እንደሚናገረው እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ሰባት ነገሮች መካከል አንዱ ሐሰተኛ ምስክር ነው /ምሳ 6፡ 16-19፤ 12፡ 17፤ 28፡ 23፤ ኤፌ 4፡ 15፣25፣ ቆላ 3፡ 9/፡፡ ሌላው ልንለማመደው ከሚገባን ነገር አንዱ ጠብን ማስወገድ ነው /ያዕ 4፡ 1-3፣ ምሳ 11፡ 12፣ ምሳ 17፣ 14፤ 20፡ 3፤ 26፡ 21፤ ሮሜ 12፡ 18፣ ኤፌ 4፡ 31፣ ዕብ 12፡ 14/፡፡ *"ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ የሚፈልግ ሰው፥ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም ተንኰልን ከመናገር ይከልክል"* /1ኛ ጴጥ 3፡ 10/፡፡





ለማነጽ የማይጠቅም አሉታዊ የሆነ ትችት ለተግባቦት እንቅፋት ነውና ፈጽሞ አለመሞከርና ለማስወገድ መልመድ ተገቢ ነው /ሮሜ 14፡ 13፤ ማቴ 7፡ 3-4/። ለማነጽ ከማይጠቅሙ አሉታዊ የሆኑ ትችት አይነቶች መካከል በቀልድ መንፈስ በመሆን ሁልጊዜ መቀለድ አንዱ ነው፤ *"ትንታግንና ፍላጻን ሞትንም እንደሚወረውር እንደ ዕብድ ሰው፥ ባልንጀራውን የሚያታልል። በጨዋታ አደረግሁት የሚል ሰውም እንዲሁ ነው።"* /ምሳ 26፡ 18-19/፡፡ ሌላው ጠቀሜታ የሌለው ሁልጊዜ ስህተት በመፈልግ መተቸት ነው *"እንደሚዋጋ ሰይፍ የሚለፈልፍ ሰው አለ የጠቢባን ምላስ ግን ጤና ነው።"* /ምሳ 12፡ 18/፡፡ የመጨርሻው የሚነገሩ ቃላትን በማጣጣል ወይም ዋጋ በማሳጣት መተቸት ናቸው። እንደ ክርስቲያን ባለትዳር መልካም ተግባቦት እንዲኖር ከተፈለገ እነዚህን የተግባቦት እንቅፋቶች በማስወገድ አንደበትን መጠበቅ፣ አንደበትን አጥብቆ መግራትና መልካም መናገርን መለማመድ በጣም አስፈላጊ ነው።

## 6. መቃኘት፡- በጥንቃቄ ሁኔታዎችን መቃኘት

*"ጥንቃቄ ይጠብቅሃል ማስተዋልም ይጋርድሃል፥"* /ምሳሌ 2፡ 11/ እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል መልካም ተግባቦት በትዳር መካከል እንዲኖረንና ግንኙነታችንን ያለምንም ፍርሃትና በነፃነት ማከናወን እንድንችል አስተዋይ መሆን ይገባናል፡፡ በግድ የለሽነት ሳይሆን ጥንቃቄ በተሞላ አካሄድ ለጋብቻ ሕይወታችን ጥበቃ የምናደርግ ባለትዳሮች ልንሆን ያስፈልጋል። ለመልካም ተግባቦት ጥንቃቄ የሚያሻው፡- ለምንናገረው ቃል፣ ለምንናገርበት መንፈስና ሁኔታ፣ ልንጠብቀው ለምንፈልገው ወዳጅነትና ለልባችን ሃሳብ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ በጥንቃቄ መቃኘትና በጤናማው መንገድ ላይ እንዲቀጥሉ በመቆጣጠር የተሳካ ተግባቦት ከትዳር ጓደኛችን ጋር እንዲኖረን ኃላፊነታችንን መወጣት ተገቢ ነው ምክንያቱም ብዙ ጉዳት የሚፈጠረው ጥንቃቄ ከጎደለው ንግግር ባጠቃላይም የተግባቦት ሂደት ነውና። *"አቤቱ፥ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።"* /መዝ 19፡ 14/

በተግባቦት ሂደት ውስጥ በአእምሮችን የሚወጡና የሚወርዱ የተለያዩ አሳቦችን የመምረጥ፣ ደግሞ ደጋግሞ የማሰብ፣ የማሰላሰልና በማስተዋል የመቃኘት ኃላፊነት አለብን፤ አለበለዚያ ለከፉ ድርጊት አልፈን ልንሰጥ እንችላለን። *"ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።"* /2ኛቆሮ 11፡ 3/ አጥብቀን ልባችንን እንጠብቅ የሕይወት መውጫ ነውና!! ስለዚህ እንደ ንጉስ ዳዊት *"አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።"* /መዝ 119፡ 11/ ብለን በመጸለይ ለቃሉ ለመታዘዝ በልባችንና በኑሯችን ስፍራ እንስጥ፡፡

# ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ሰባት (7)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. የተግባቦት (ኮሙኒኬሽን) ምንነት በማብራራት ግለጡ::
2. በባለትዳሮች መካከል ትክክለኛ የሆነ ተግባቦት አለ የምንልለው መቼና ምን ሲፈጠር ነው?
3. ባለትዳሮች እንደሚገባ እንዳይግባቡ ሊያደርጓቸው የሚችሉ ምክንያቶች ምንድን ናቸው ትላላችሁ?
4. የእናንተን የትዳር ግንኙነት ደረጃ ስትገመግሙት የት ላይ ነው ያላችሁት? እንደሚገባስ እንዳትግባቡ ያደረጋችሁና ለግጭት የዳረጋችሁ ምክንያትስ ምንድን ነው?
5. ጥንዶች በትዳር ሕይወታቸው መልካም ተግባቦት እንዲኖር ምን ማድረግ አለባቸው? በሰፊው ተወያዩበት::
6. የእናንተን ተግባቦት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ? የተግባቦት ደርጃችሁን ከፍ ለማድረግ ዛሬ አብራችሁ አቅዱ።





# ምዕራፍ ስምንት(8)

# ገንዘብና ንብረት

## I. የገንዘብና የንብረት ምንነት

ገንዘብና ንብረት የምንለው ጥንዶቹ በግልም ሆነ በጋራ በሥራ፣ በንግድ፣ በውርስ፣ ያገኙትንና የሚያገኙትን ለጋራ ትዳራቸው የሚጠቀሙበትን ጥሬ ገንዘብ፣ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት፣ ብር፣ ወርቅና ገቢ ሊያመጣ የሚችል ማንኛውንም ዓይነት ንብረት ሁሉ ያጠቃለለ ነው። ክርስቲያን ባልና ሚስት አንድነታቸው የሚገለጥበት አንዱ ጉዳይ የጋራ ገንዘብና ንብረት ባለቤት መሆናቸው ነው። ይህ ርዕሰ ጉዳይ በዚህ የጋብቻ ዘመን ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዘው ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ የግጭት ምክንያቶችንና መፍትሔዎቻቸውን በማሳየት የጥንዶችን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር የሚረዳና አቅጣጫ የሚጠቁም ነው።

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር አንዳችን ለአንዳችን ራሳችንን የመስጠት ኃላፊነትን የመተግበርን አስፈላጊነት መረዳት ብቻ ሳይሆን ያለን ሁሉ የጋራ እንደሆነ ልናውቅና ልናምን ይገባል። በትዳር ውስጥ አንድነት ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ ገንዘባችንና ንብረታችን ነው። ክርስቲያን ባለትዳሮች ያለንን ሁሉ በመካፈልና በጋራ በመጠቀም ለመኖር የጀመርነው የአብሮነት ጉዞ ሁለንተናዊ መሰጠትን የሚጠይቅ ነው። ክርስቲያን ባለትዳሮች ይህንን ሕይወት መግለጥ የሚችሉት ገንዘባቸውን ያለ አድሎና ከፍፍል ለእኔ ብቻ ከሚል ገንዘብን የመውደድ ግለኝነት በጸዳ መልኩ አብረው መጠቀም ሲችሉ ነው *"አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤..."* /ዕብ.13:5/::

## II. ከገንዘብና ከንብረት ጋር የተያያዙ የግጭት መንስኤዎች

በባለትዳሮች መካከል ላለመግባባትና ለግጭት ቀዳሚ ከሚሆኑት ምክንያት መካከል አንዱ ገንዘብ ነው። በቅርብ አመታት በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ሆነ በቆዩት ከገንዘብና ከንብረት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩና ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮችን መለየትና ማወቅ መፍትሔ ለማፈላለግ እገዛው ከፍተኛ ነው። እነዚህን በገንዘብና በንብረት ላይ ባለትዳሮች እንዳይግባቡ የሚያደርጉ የግጭት ምክንያቶች እንደሚከተለው እንቃኛለን:-

### 1. ለሰርግና ከሰርግ ጋር ተያይዘው በወጡ የተለያዩ ወጭዎች

ጥንዶች ከእጮኝነት ወደ ባለትዳርነት መሸጋገር በሚያስቡና በሚወስኑበት ወቅት ከፍተኛ ባጀት የሚጠይቁ የሰርግና ከሰርግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጭዎች አሉ። የሰርግ ድግስ ማድረግ አለብን ወይስ የለብንም? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚወሰነውን ውሳኔ ለጥንዶች መተው የግድ ነው። የሰርግ ድግስ መተው ማለት ግን ጋብቻችንን በቤተ ክርስቲያን በኩል ማድረግን፣ በቤተክርስቲያን የሚጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላትንና በጽድቅ በእግዚአብሔርና በምስክሮች ፊት በይፋ ቃልኪዳን በመግባት መጋባትን መርሳት እንዳይደለ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።

ሰርግ ሲታሰብ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከጓደኞች ጋር ለመወዳደርና የእኔ ወይም የእኛ ሰርግ ለየት ያለ ነበር የሚል ዝና ፍለጋ ወደ ሰርግ ውሳኔ ከመምጣት ራስን መጠበቅ ተገቢ ነው። ዛሬ በሰርግ ከሌሎች ጋር መወዳደር ከጀመርን ይህ የውድድር ስሜት ከእኛ ጋር አብሮን በመቀጠል ሁልጊዜ ባለን ነገር እንዳንረካና ሌሎች የእኛ የቅርብ ሰዎች ባላቸውና በሚኖራቸው ንብረት፣ ገንዘብና ሐብት በመቅናት ደስታ የራቀንና የሰዎችን የማግኘት ሳይሆን የማጣት ዜና መስማት እንድንናፍቅ ሊያደርገን ይችላል። ሌሎች ሰዎች የሆነ ነገር ባገኙ ጊዜ ሁሉ ደስታ የራቀን ከመሆናችንም ባሻገር ከሌሎች ሰዎች በልጦ ለመገኘት የምናደርገው አቅምን ያላማከለ የተለያየ ወጭ ከትዳር አጋራችን ጋር ያጋጨናል፡፡ ይህ ክስተት ባግባቡ ካልተስተካከለ የመለያየት ምክንያት ሊሆንም ይችላል።

ስለዚህ ይህን እውነታ በመረዳት ሰርግ ለመደገስ የሚያስቡ እጮኛሞች አቅማቸውን ማገናዘብና ያሉበትን ሁኔታ በማስተዋል ማየት ቢችሉ መልካም ነው። ሰርግ መደገስ መቼ፣ እንዴትና ምን ያክል ወጭ ይጠይቀናል ብለን ስናስብ በቀጣይ ኑሯችን ላይ አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ሳያሳድር ልንወጣው መቻላችንን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ትዳር ለመመሠረት ብለን የምናደርጋቸው ነገሮች የትዳራችን እንቅፋት ሊሆኑ አይገባም። ለሰርግና ከሰርግ ጋር ተያይዘው ልናወጣቸው የሚታሰቡ ወጭዎችን በሚመለከት በጋራ በመወያየት አስፈላጊነታቸውንና አቅማችንን መቃኘትና ስምምነት ላይ መድረስ ተገቢ ነው። ትናንት እንዴት ባለ መልኩ ገንዘቡን ለማግኘት ዋጋ እንደከፈልን ማሰብ፣ ዛሬ ያለንን አቅም መመልከትና ነገ በትዳራችን ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ተጽዕኖ መቃኘት እንደገና ለሌላ ችግር አልፈን እንዳንሰጥ ይጠብቀናል፡፡ የትዳር ግንኙነታችንም በጤንነትና ደስታ በተሞላ ሁኔታ እንድንመራ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት መዘንጋት የለብንም።

ሰርግን ከአቅም በላይ በሆነና በብድር ደግሰው የተጋቡ የቅርብ ተጋቢ ባለትዳሮች ወደ ኋላ ተመልሰው መጸጸትና አንዱ በሌላው ማሳበብ ከሰርግ ማግስት የሚያጋጥማቸው ተግዳሮት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ሲያጋጥማቸው መካሰስንና መወቃቀስን አስወግደው በጋራ ካሉበት ዕዳ ለመውጣት ማቀድ መቻል አለባቸው። ጥንዶቹ በጋራ በመስማማት ከትናንቱ አባካኝ የሆነ ውሳኔ በመማር ዛሬ ብድር ውስጥ የሚያስገቡ ሁኔታዎችን ማቆምና ማስወገድ መቻል ይኖርባቸዋል። ከሌሎች ጋር ተወዳድሮ በልጦ መገኘት ከሚባለው መጥፎ የውድድር መንፈስ ራስን ነጻ በማድረግና በመጠበቅ የራስን ኑሮ መኖር ተገቢ ነው፡፡ ይህን መርህ የሚከተሉ ጥንዶች ነገ ልጆች ሲወለዱ፣ ሲያድጉና ትምህርት ቤት ሲገቡ የሚጠብቃቸውን ወጭና ሌሎች ያልታሰቡ ወጭዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአቅማቸው በመኖር የቤተሰባቸውን የሰላምና የደህንነት መሠረት ዛሬ መጣል ተገቢ ነው፡፡ በሚወስዱት መልካም እርምጃም ቤታቸውን ነገ ከሚያጋጥም





ግጭት አስቀድመው ይጠብቃሉ፡፡ ይህ ዓይነቱ የጠቢብ ሰው ተግባር ትዳርንና ቤተሰብን ለመጠበቅ አንዱ ብስለት የተሞላ እርምጃ ነው።

## 2. ጥንዶች በገንዘብ ላይ ያላቸው የአመለካከት (የእይታ) ልዩነት

ባልና ሚስት በገንዝብ ላይ ያላቸው የአመለካከት ልዩነት አለመግባባትና ግጭት በትዳራቸው እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል። **የመጀመሪያው** በአመለካከት ልዩነት ቀውስ የሚፈጠርበት ምክንያት ባልና ሚስት ገንዘብን በተለያየ አመለካከት በማየታቸው ነው። አንዱ የትዳር አጋር ገንዘብ እጅግ በጣም አስፈላጊና ዋና ነገር እንደሆነ ሲያስብና ሲያምን ሌላው አካል ደግሞ ገንዘብ ዋና ነገር እንደሆነ ሳያስብ ወይም ምንም እንዳልሆነ ሲያስብ በመካከላቸው አለመግባባት የሚፈጠርበት ሰበብ አለ ማለት ይቻላል። በሁለቱ መካከል ያለው የእይታ ልዩነት ገንዘብን ለማግኘትና ለመጠቀም ተነሳሽነታቸው እንዲለያይ በማድረግ አንዱ አካል ሌላውን ወደ ራሱ አመለካከት ለማስገባት የሚያካሂደው ትግል ውጥረት ያስከትላል፡፡ ጥንዶችንም ለግጭት ይዳርጋል።

**ሁለተኛው** በአመለካከት ልዩነት ምክንያት ቀውስ የሚፈጠረው ገንዘብን ሠርቶ ለማግኘት አንደኛው አካል ደሞዝና ክፍያ ላይ ሲያተኩር ሌላው አካል ደግሞ ከክፍያ ይልቅ ከሥራው ዓይነትና ቦታ፣ ከቤተሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከወዳጆችና ከልጆች ትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ለማሰብ ቅድሚያ በሚሰጥበት ጊዜ ነው፡፡ በእይታቸው መለያየት መነሻነት ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የሚኖሩበትንና የሚሠሩበትን አገር ወይም አካባቢ ጫና እና የሚጠብቃቸውን ወጭ በመመልከት ፍላጎታቸውን ለማሟላት በሚያራምዱት አስተሳሰብ መለያየት ጥንዶች ወደ ግጭት ሊገቡ ይችላሉ።

**ሶስተኛው** ከጥንዶች የእይታ ልዩነት ጋር የተያያዘ ችግር በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠረው አንዱ አካል ዛሬ ላይ ብቻ በማተኮር ገንዘብን ለዛሬ እንጠቀም ነገን በእግዚአብሔር እንታመን የሚል አመለካከት ሲኖረውና ሌላው ደግሞ ከዛሬ ይልቅ ብዙ ነገዎችን በማሰብ ለወደፊት ወይም ለአደጋ ጊዜ የሚሆን የኢኮኖሚ መሠረት እንጣል የሚል አቋም ሲይዝ ነው፡፡ እይታቸው መለያየቱ ሁለቱ ተጋቢዎች ለዛሬ ብቻ ደስ ብሎን እንኑር ወይንስ ለቀጣዩ ሕይወታችንና ኑሯችን እናስብ በሚል መንታ ሃሳብ እንዲሟገቱና እንዲጨቃጨቁ ያስገድዳቸዋል፡፡ በዛሬና በነገ መካከል ባላቸው የአመለካከት ልዩነት ሰበብም በጥንዶቹ የትዳር ሕይወት ውስጥ ገንዘብ ያለመግባባትና የግጭት አብይ ምክንያት ይሆናል።

**አራተኛው** በአመለካከት ልዩነት ምክንያት ቀውስ የሚፈጠረው አንዱ የትዳር አካል ለቤተ ክርስቲያን፣ ለችግረኞች፣ ለቤተሰብ፣ ለወዳጅና ለሌሎች ጉዳዮች ገንዘብ መስጠት አስፈላጊና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ በሚያምንበትና ሌላው አካል ደግሞ የራስ የወደፊት ኑሮና አስፈላጊ ወጭ ላይ ብቻ እናተኩር በሚልበት ጊዜ ነው፡፡ አንደኛው አካል ለሌሎች የገንዘብ ድጋፍ ካላደረግን ሲል ሌላኛው አካል ደግሞ

መስጠትን ሲከለክልና መስጠት ሊያመጣ ይችላል ብሎ የሚያስበውን ክስረት በየምክንያቱ እያነሳ ማስጠንቀቅ ሲጀምር ገንዘብን ለሌሎች የመስጠት አስፈላጊነት ላይ ተጋቢዎች ያላቸው የአመለካከት መለያየት ግጭት እንዲፈጠር ዋና ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**አምስተኛው** የአይታ ልዩነት በትዳር ውስጥ ለቀውስ ምክንያት የሚሆንበት ጊዜ የአንዱ አካል ብቻ በቤት ውስጥ ላሉ ለተለያዩ ወጭዎች በቂ ገቢ ለማግኘት፣ ኑሮን ለመሸፈን፣ እዳን ለመክፈልና ለወደፊት ለታቀዱ ታላላቅ ወጭዎች ለመዘጋጀት ሲባል መደበኛ የገቢ ምንጭ ከሆነው ስራ በተጨማሪ ሌላ ስራ በመስራት ገቢን ለመጨመር ማሰብና መጣር ነው። ሌላው አካል ደግሞ ለተጨማሪ ገቢ ተጨማሪ ሰዓታትን መስራትን በመቃወም እንደ ባለትዳር የጋራ ጊዜን አብሮ በማሳለፍ የትዳርን ግንኙነት መገንባት ላይ ሲያተኩር በመካከላቸው ላለመግባባትና ለግጭት አልፈው ሊሰጡ ይችላሉ።

**ስድስተኛው** በጥንዶች መካከል በአይታ ልዩነት ሰበብ ችግር የሚፈጠረው አንዱ የትዳር አካል የገቢንና የወጭን ሂደት መከታተልና መቆጣጠር የሚፈልግ ሲሆንና ይህንንም ፍላጎቱን በሁሉም የወጭና የገቢ እንቅስቃሴ ላይ በቁጣና በተቆጣጣሪነት መንፈስ በመናገር ለማሟላት ሲሞክር ነው፡፡ ሌላው አካል ደግሞ በተቃራኒው እርሱ ራሱ ሠርቶ የሚያስገባውን ገቢ እንዲሁም በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች የሚገባውንና የሚወጣውን ገንዘብ የማወቅም ይሁን የማሳወቅ አስፈላጊነት ላይ ግድ የማይሰጠው ምን እንደተደርገና እንደሚደረግ የማያውቅ ሊያውቅም የማይፈልግ ይሆናል፡፡ ወይንም አስቦበት የተደበቀ ዓላማ ያለው ሰው ይሆንና ወጭና ገቢ ላይ ድብብቆሽ ይጫወታል፡፡ እነዚህ ተቃራናዊ መስመር ያላቸው የዕይታ ልዩነቶች፣ ፍላጎቶችና ድርጊቶች በጥንዶቹ መካከል በየጊዜው ያለመግባባትና የግጭት መነሻና ማደጊያ የውጥረት አካባቢዎች ሆነው ይቀጥላሉ ።

**የመጨረሻው** ጥንዶቹ በገንዘብ ላይ ባላቸው የተለያየ አመለካከት መነሻነት ላለመግባባትና ለግጭት የሚዳረጉት ወጭ በሚያወጡበት ወቅት ቅድሚያ በሚሰጧቸው ነገሮች ላይ ልዩነት ሲኖራቸው ነው። አንዱ አካል ለልጆች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ፣ ሌላው አካል ለወላጆች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ወይም የቅንጦት እና የመዝናኛዎች እቃዎች ላይ ሲያተኩር በመካከላቸው ጭቅጭቅና የውድድር መንፈስ ይፈጠራል፡፡ ይህ በውድድር መንፈስ ጥንዶቹ ወደ ፉክክር መግባታቸው በእልህ በሌላኛው አካል አሳብ አቅራቢነት ከወጣው ወጭ ጋር የሚመጣጠን አቻ የወጭ በጀት ለእርሱም እንዲበጀትለት ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ንብረቶች፣ ያልታሰበባቸው አዳዲስ እቃዎች እንዲገዙ ወይም የግል መብቱ እንዲከበርለት ከጥንዶቹ አንደኛው ግትር አቋም እንዲይዝ ያደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ላይግባቡና ግጭትም ሊፈጠር ይችላል።





## 3. ዕዳ ውስጥ በመግባትና ለመውጣት በሚደረግ ውጥረት

ወደ ትዳር ዓለም ከመግባታቸው በፊት ለትምህርት፣ ለንግድ፣ አንዳንድ ከፍተኛ ወጭን የሚጠይቁ ንብረቶችን ለመግዛት ሲባል፣ ለሚደግሱት የሰርግ ወጭና ለሚያዘጋጁት አዲስ ቤትና የቤት ዕቃ ግዥ ከመንግሥትም ሆነ ከግለሰብ በተበደሩት እዳ ምክንያት ጥንዶች ላለመግባባትና ለግጭት ሊዳረጉ ይችላሉ። ወይም ለግላቸው፣ ለትዳራቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለንግድ እንቅስቃሴያቸው የተበደሩት ብድር ባጀትን ባገናዘበ መንገድ በግልጥና በጋራ በመስማማት የተፈጸመ ካልሆነ ከጋብቻ በፊትና በኋላ በሚፈጠረው ግጭት ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል ላይሆን ይችላል።

ቤተሰብን የሚመሩ ጥንዶች ቀውስን በቀነሰ ሂደት ብድር ለመበደርና እዳቸውን ከፍለው ከብድር ተጽዕኖ ለመውጣት ከፈለጉ በቅድሚያ የራሳቸውን አቅም ያገናዘበና ምክንያታዊ የሆነ ባጀት በመበጀት በፕሮግራም ትዳራቸውን ሊመሩት ይገባል፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ ባለትዳሮች ገቢን ያገናዘበ በጀትን በምክክር ወስኖ በፕሮግራም መመራትን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት አሉታዊ ቅድመ እሳቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ በዚህ መንገድ ቤተሰብን የማስተዳደሩንና የመምራቱን ጉዳይ ችላ ሲሉት ይታያሉ፡፡

ባጀትን መሠረት ባደረገ የታሰበበት መንገድ መኖርንና ቤተሰብን መምራትን ነፃነትን እንደሚነፍግና የማያምን ክርስቲያን የኑሮ ዘይቤ እንደሆነ በማሰብ የሚፈጠረው ሽሽት ለግዴለሽነታቸው ዋናው ምክንያት ነው። በትዳር ውስጥ ለሚያስፈልገው ገቢና ወጭ በቂ የሆነ የታሰበበት፣ በግልጥ ምክክር ውሳኔ ላይ የተደረሰበትና አቅምን ያገናዘበ በጀት አለመኖር ባለትዳሮችን ያለአግባብ ለብድር ተጋላጭ ሊያደርጋቸው ይችላል።

በእርግጥ ባጀት በጀትን ማለት በዚህ ብዙ ነገሮች በቅጽበት በሚለዋወጡበት ዓለም ውስጥ ዛሬ ላይ የወሰንነው ባጀት በየቀኑ የሚያጋጥሙንን ያላወቅናቸውን ገጠመኞችና ለውጦች ተከትሎ የሚፈጠሩ ወጭዎችን ሁሉ ፍጹማዊ በሆነ መንገድ ያሟላል ማለት አይደለም፡፡ ባለትዳሮች በሳሎችና በገሃዱ ዓለም ላይ ያሉ እውነታዎችን በማገናዘብ ሕይወታቸውን፣ ትዳራቸውን፣ ቤተሰባቸውንና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸውን ሁሉ የሚመሩ ኢጋሮች መሆን አለባቸው፡፡

በትዳር ውስጥ ያለው የሕይወት ጉዞ ደግሞ በግትርነት ሳይሆን በተገቢው ጊዜ ተገቢውን ወጭ በማውጣት መሆን ያለበትን ነገር የማድረግንም ብስለትና ውሳኔ ሰጭነትን የሚጠይቅ ኃላፊነት ነው፡፡ የታሰበበት ባጀት መኖር የምናወጣውን ወጭ በዘፈቀደ ሳይሆን በዕቅድ እንድናወጣ ይረዳናል፡፡ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከአላስፈላጊ ብድር እንድንቆጥብ ያበረታታናል፡፡ በገቢና በወጭ አለመመጣጠን የሚፈጠርን ውጥረት ይቀንሳል፡፡ ላልተጠበቀ ወጭ ዝግጅት እንድናደርግ ያነቃናል፡፡ ንፉግነትን ሳይሆን የታሰበበትን የመስጠት ሕይወት እንድንለማመድ ያበረታታናል፡፡ በትዳራችን መካከል ግልጥነትና መተማመን ይበልጥ እየዳበረና እያደገ የትዳራችን ደህንነት እንዲጠበቅ ሰላም በቤታችን እንዲበዛ ገንቢ አስተዋጾ ያበረከትልናል፡፡

ጥንዶችን አንዱ ለሌላው እንዲታዘዙ ያበረታታል፡፡ ደግሞም አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠር ወይንም ስናምንበት ዕቅዳችንን እንደ ሁኔታውና እንደ አስፈላጊነቱ እንድንለውጥ ግልጥ መነሻ መሠረት በመሆን ይረዳናል። ቤተሰባችንንም ግልጥ በሆነ ሁለንተናዊ የእድገት ጎዳና ካለንበት የመንፈሳዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊ፣ የትምህርትና የአኗኗር ደረጃ ወደ ቀጣይ ከፍተኛ ደረጃ የምናሳድግበት ሂደት እንዲኖር እድል ይሰጠናል።

በተለይ በውጭ አገር ለምንኖር ሐበሾች በግድሌሽነትና በውድድር መንፈስ የክሬድት ካርድ ተጠቃሚ በመሆን ብድራችን ጨምሮ መውጫ እንዳይቸግረንና ለትዳራችን ግንኙነት ችግር እንዳይሆንብን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከገቢያችን ጋር በማይመጣጠን መንገድ ኑሯችን በብድር ይሸፈናል ብለን በማሰብ በግዴለሽነት ዕዳ ውስጥ መዘፈቅ ቆይቶ ለማንወጣው ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ችግር ተጋላጭ ያደርገናል፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን በሁለንተናዊ ጤንነታችን ላይ የሚፈጥረው ችግርና በትዳራችን ውስጥ የሚፈጥረው የቀውስ በሽታም በቀላሉ የሚፈወስ አይሆንም።

## 4. አንዱ የትዳር አጋር የበለጠ ገንዘብ አባካኝ መሆን

በቅርብ በተጋቡ ባለትዳሮች መካከል ከገንዘብ ጋር ተያይዞ ችግር እንዲፈጠር ከሚያደርጉ ምክንያቶች መካከል በዚህ ርእስ ውስጥ የምንዳስሰው አንዱ አካል በተለያየ ምክንያት የበለጠ ገንዘብ አባካኝ የመሆኑን ጉዳይ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከጥንዶቹ አንዳቸው ዋጋቸው ውድ የሆኑ እቃዎችን በመግዛት ማለትም ዕቃው ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ የእቃው ብራንድ፣ ስምና ዋጋ ውድነት ላይ በማተኮር ከፍተኛ ወጭ የማውጣት ችግር ያለባቸው ይሆናሉ። በአንዳንድ ቤተሰቦችም ዘንድ በየጊዜው ገበያ በመውጣት ውድ ነገር የመግዛት፣ ያዩትንና ያላሰቡበትን ድንገት ወጥተው ገዝተው የመግባት ችግርና ሱስ ያለባቸው ጥንዶች መኖራቸውም የአደባባይ ሚስጥር ነው ቢባል ግነት አይሆንም።

በሌሎች ባለትዳሮች ዘንድ ደግሞ ከማባከን ችግር ጋር በተያያዘ ሊጠቀስ የሚችለው ጉዳይ ምናልባትም ሰዎችን በችግራቸው ለመርዳት ያላቸውን የሚያካፍሉ (የሚሰጡ) የትዳር አጋሮች መኖራቸው ሊሆን ይችላል። ያለንን ለችግረኞች ማካፈል በመልካም ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር በመኖር ክርስቲያናዊ ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር ነው፡፡ ነገር ግን ያለንን ለችግረኞች የማካፈል ተግባር መልካም ክርስቲያናዊ ስነ-ምግባር መሆን የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል መርህ መሠረት በትክክለኛው መንገድ ሲከናወን ነው፡፡ አንዳንድ ባለ ትዳሮች እንደዚህ ዓይነቱን መልካም ስነምግባር የሚፈጽሙት አቅምን ባላገናዘበና ገደብ የለሽ በሆነ መንገድ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር ድብብቆሽ በመጫወትና ከትዳር ጓኛቸው እውቅና ውጭ ለሌሎች ተቸግረዋል ብለው ለሚያስቧቸው ሰዎች በመስጠት ነው፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ትዳርን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን መርህ በመጣስ የትዳር አጋራቸውን ዋሽተውና አታልለው እንዲሁም ሰርቀው ነው፡፡ ይህን ዓይነት ድርጊት የሚፈጽሙ ባለትዳሮች





ተደራራቢ ጥፋትና ኃጢአት ከመፈጸማቸውም በላይ በትዳር ሕይወታቸው ውስጥ በቀላሉ ሊስተካከል የማይችል ችግር ይፈጥራሉ፡፡

ሰዎችን ለመርዳት የሚፈልጉ በትዳር ውስጥ ያሉ ሰዎች ለእርዳታ ወጭ ማድረግ ባለባቸው ገንዘብ ላይ ከትዳር አጋራቸው ጋር በአንድነት መወሰን ያለባቸው መሆኑን በግዴለሽነት ማለፍ ወይም መርሳትና በግላቸው የሚፈልጉትን ወደ ማድረግ መግባትን ፈጽሞ ማስወገድ አለባቸው፡፡ አባካኝ የሆነውን የትዳር አጋር ለመረዳትና ለመርዳት ጥረት በማድረግ ማለትም ለሌላ ሰው ገንዘብ በመስጠት ሂደትም ውስጥ ሆነ በግዥ ወቅት ስንት እንደምናወጣና በየስንት ጊዜው ግዥ ማከናወን እንዳለብን በመመካከር ከገቢያችን በታች መኖር መቻል ችግሩን ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ችግሩ ያለበት የትዳር ጓደኛም እውነታውን በመገንዘብ ራሱን ለማሻሻልና ቤተሰቡን የሚጠቅም አቅጣጫን ተከትሎ ለመኖር ፈቃደኝነት ሊኖረው ይገባል፡፡ የማያቋርጥ ጥረት ማድረግም ይጠበቅበታል፡፡

## 5. ሚዛኑን ባልጠበቀና ታማኝነት በጎደለው መንገድ ቤተሰብን መርዳት

በቅርብ ተጋቢዎች መካከል አንዱ ያለመግባባትና የግጭት ምክንያት የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ነው። ባለትዳሮች ወላጆቻቸውን ባለመተው ወይም በትዳራቸው ውስጥ የቤተሰብን አስተዳደር ምርጫና ውሳኔ በማሳተፍ ለቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ ይሆናሉ። ይህ ተጋላጭነት ባለትዳሮች የጋራ ውሳኔ በሌለበት፣ ሚዛኑን ባልጠበቀ፣ ግልጥነትና ታማኝነት በጎደለው መንገድ ለቤተሰቦቻቸው በድብቅ የገንዘብና የቁሳቁስ ... ድጋፍ በማድረጋቸው ይፈጠራል፡፡ አስቀድሞ የተፈጠረ ከሆነ ደግሞ ይባባሳል። በድብቅ እርዳታ መቀበላቸውን የሚያውቁ ቤተሰቦችም ይበልጥ በድብቅ መረዳታቸው እንዲቀጥል ዕድሉን የመጠቀም ፍላጎትና ጥረት ሊያሳዩ ይችላሉ። በአድሎና በድብቅ ይደረግ የነበረው እርዳታ በተገለጠ ወቅት የሚፈነዳው የግጭት ደማሚት የሚያካልለው የጥንዶችን ትዳር ብቻ ሳይሆን ወላጆችን ጭምር ሲሆን መተማመን እንዳይኖርም ፈጥሮ ሊያልፍ የሚችለው ችግር በቀላሉ የሚፈታ አይደለም።

## 6. የሚስት በገቢ ባሏን መብለጥና እርሷ ብቻ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ መሆን

ሚስት ከባሏ በገቢ በምትበልጥበት ወይንም ብቸኛዋ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ በምትሆንበት ወቅት ለዘመናት በነገሰው የባህል ተጽዕኖ፣ በቤተሰብና በሌሎች ሰዎች ተጽዕኖ፣ በአመለካከት መዛባት ወይንም ገንዘብ ለሰዎች በሚሰጠው የኃይል የበላይነት ምክንያት በባልና በሚስት መካከል ያለመግባባትና ግጭት ይፈጠራል፡፡ ከባህላችን አንጻር ወንድ ልጅ (ባል) የገቢ ምንጭ በመሆን ቤተሰቡን በማስተዳደር አብዛኛውን የቤተሰቡን አቅርቦት እንዲያሟላና ቤተሰቡን እንዲመግብ ይጠበቅበታል። ነገር ግን ጊዜያዊ ወይም ቋሚ በሆነ ምክንያት የባል ከሥራ መቀነስ፣ ወደ ሌላ ስራ ለመዘዋወር በሽግግር ወቅት ላይ መገኘት፣ በተማረበትና በሰለጠነበት ሙያ ሥራ አለማግኘት፣ የቤተ

ክርስቲያን አገልጋይ በመሆን አነስተኛ በሆነ የቤተ ክርስቲያን ክፍያ ማገልገል፣ ይሠራበት የነበረው መሥሪያ ቤት (ድርጅት) ፈጽሞ መዘጋትና ከሚስት ጋር በትምህርትም ሆነ በደሞዝ አለመመጣጠን በመሳሰሉት ምክንያቶች ባል በሚስቱ በገቢ መበለጥ ወይም የሚስት ብቻ የገቢ ምንጭ የመሆን ክስተት ፈጠራል፡፡ ባልም የሚጠበቅበትን ቤተሰቡን ዋና የገቢ ምንጭ በመሆን የመመገብ ኃላፊነቱን የማይወጣበት ሁኔታ ያጋጥመዋል። በዚህ ወቅት ባል ኃላፊነቴን መወጣት አልቻልኩም በሚል ስሜት የስነ ልቦና ተጽዕኖ ይፈጠርበታል። ጭንቀትና የበታችነት ስሜትም ሊረብሸው ይችላል፡፡ ሚስትም ካደገችበት የባህል ተጽዕኖና ዋና የገንዘብ ምንጭ መሆኗ በውስጧ ከፈጠረው የኩራት ስሜት በመነሳት ባሏን ዝቅ አድርጋ የመመልከት ዝንባሌ ሊኖራት ይችላል፡፡

በተፈጠረው ሁኔታ ምክንያት በቤተሰብ፣ በጓደኞችና ቅርበት ባላቸው ሰዎች ዘንድም ባል አስቀድሞ ይሰጠው የነበረው ከበሬታ እየቀነሰ የሚመጣበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ እነዚህ ተደማምረው በሚያስከትሉት አሉታዊ ተጽዕኖ ባል ነጭናጫ፣ ስሜቱ በቶሎ የሚነካ፣ ትካዜ የሚያበዛ፣ ቁጣ የሚቀድመውና መረጋጋት የራቀው ሊሆን ይችላል፡፡ በተቃራኒው ሚስት ደግሞ የቀድሞ ትህትናዋ እየቀነሰ ወደ አዛዥነት፣ ወደ ባለስልጣንነት፣ ከውይይትና የባሏን አሳብ በማድመጥና በማክበር ነገሮችን ከማድረግ ይልቅ ልክ ነው ብላ ያሰበችውን ነገር በራሷ ውሳኔ ወደ መፈጸም ትገባለች፡፡ እነዚህን ነገሮች በተረጋጋና ጤናማ በሆነ አስተዋይነት ማስተካከል ካልቻሉ በጥንዶቹ መካከል የከፋና መራራ አለመግባባትና ግጭት ሊከሰት ይችላል፡፡

በእርግጥ በአሁኑ ወቅት በዘመናዊው ባህል እየተቀረጸ ያለው ትውልድና ከአገር ቤት ውጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በዚህ ጉዳይ ላይ ከቀድሞው ትውልድ የተሻለ አመለካከትና አቋም ያለን መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው። የሴቶችም ከወንዶች ባላነሰና በበለጠ ሁኔታ የመማር፣ የመሰልጠንና በሙያቸው በደህና ክፍያ ተቀጥሮ ወይም ሥራ ፈጥሮ የመኖር ባህል እየተለመደ ለመምጣቱ የአይን ምስክሮች ነን። ነገር ግን እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ለመቀበልና ተዋዶና ተቀባብሎ ለመኖር በቂ ዝግጅት አድርገናል ማለት የምንችልበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ገና ብዙ ረጅም መንገድ ይጠብቀናል፡፡ ይህ ጉዳይ በየቤታችን በአግባቡ ሊታሰብበት ካልቻለ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል። ይህ ጉዳይ ለባለትዳሮቹ ችግር ባይሆንም እንኳን ሕብረተሰባችን ማለትም የባለትዳሮች ቤተሰብና ጓደኞች የሴቶችን (የሚስቶችን) በገቢ ምንጭ መብለጥና እነርሱ ብቻ የቤተሰቡ የገቢ ምንጭ መሆን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ አስተያየቶችና ቃላቶች እየሰነዘሩ ጥንዶችን በነገር ሊሸነቁጡአቸው ይችላሉ፡፡

ሰዎች የሚናገሯቸው አሽሙሮችና ቀጥተኛ ስድቦች የጥንዶችን ህሊናና ስሜት በመጉዳት፣ ያላሰቡትን ነገር እንዲያስቡ በማንቃትና ለጠብ በሚያነሳሳ መንገድ ስሜታቸውን በመቀስቀስ ለግጭት ሊዳርጓቸው ይችላሉ። በሕበረተሰባችን ዘንድ አንዱ ስለሌላው ትዳር በመልካምም ሆነ በመጥፎ ስሜት መነጋገር፣ ጣልቃ መግባትና





አስተያየት መስጠት የተለመደ ነው። በዚህ ልምምድ ሂደት ውስጥ አፍራሽ ተጽእኖዎችን በመቀነስና በማስወገድ ራስንና የትዳርን ግንኙነት በሰላም ጠብቆ መኖር በሳልነት ነው። እንኳን በብዙ ነገር ተበልጠው ያለዚያም ተሽለው ተገኝተውና እንዲሁ ከባህርያቸው ነገር የሚተርጉሙና እንዲተረጎም በማድረግ የሚናገሩ፣ ነገር የሚያካብዱና የሚያቃልሉ፣ ስሜታቸው ቶሎ የሚነካና የሌላውን ስሜት የሚነኩ፣ ያላቸውን ንብረት በመቆጣጠር ራስ ተኮር የባለቤትነት ስሜት የሚገዛቸውና የባለቤትነት ስሜት የማይሰማቸው፣ በነገሮች ሁሉ የሚያሽሟቅቁና በሁኔታዎች የሚሽሟቀቁ … ሁለት ተቃራኒ ገጽታዎች በጥንዶቹ የትዳር ሕይወት መፈራረቃቸው የተለመደ ነው፡፡ ሁኔታውም የትዳር ግንኙነታቸውን ደስታ የራቀውና ውጥረት የበዛበት እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል።

በተፈጠሩት ውጥረቶች ምክንያትም ጥንዶቹ የጋራ ከሆነው የባንክ አካውንት በተጨማሪ በግል ድብቅ የባንክ አካውንት በመክፈት ገንዘብን የማስተዳደር መንገዶችን መከተል ሊጀምሩ ይቻላሉ። አንዱ የሌላውን ገቢና ወጭ አለማወቅ፣ የማያገባው ሆኖ መቆጠርና ተጠያቂነት የሌለበት የገንዘብ አወጣጥ ሂደት ይከተላል። እንዲህ ዓይነት ኑሮ የሚኖሩ ጥንዶች በመብዛታቸው በሌሎች ነገሮች ብቻ አንድነታቸውን እየገለጡ በገንዘባቸው ላይ አንድ ያልሆኑ ባለትዳሮች ቁጥራቸው እየጨመረ ነው። በተለይ አሁን ስልጣኔንና እድገትን በአግባብ ባለመያዝ፣ ባልና ሚስትም እኩል ሠርተው የገቢ ምንጭ ባለቤት መሆናቸውን በአግባቡ ለማስተናገድ ባለመዘጋጀታቸውና ከበፊቱ ይልቅ በዓለም ላይ ብዙ ምርጫና ውሳኔ እየበዛ መምጣቱ በቤተ ክርስቲያን እንኳን ፍች እየበዛ እንዲመጣ አፍራሽ ተጽዕኖ በማሳደሩ ችግሩ እየተባባሰ ይገኛል። የችግሩ መባባስም የጋራ የባንክ አካውንት በመክፈት በጋራ ገቢንና ወጭን በመቆጣጠር ለጋራ ጥቅም አብሮ መትጋት እየጠፋ እንደ እድር፣ እቁብና በመዋጮ አንድን ወጭ እንደሚሸፍኑ ጓደኞች በመዋጮ በመኖር የክርስቲያኖች ትዳር የአንድነት መገለጫ የሆነውን ገንዘብን በመለያየት ኑሮን ለማሸነፍ ጥረት የማድረጉ ሂደት ቤተሰብን የሚያመሰቃቅል የግጭት ምክንያት እየሆነ ነው፡፡

## 7. ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ወይም ያፈሩትን ንብረት የጋራ እንዳይደለ በማሳወቅ መፈራረም

ወደ ጋብቻ ውሳኔ በሚመጡበትና በሚያገቡበት ወቅት ሌላው የግጭት ምክንያት በአንዳንድ ባለትዳሮች መካከል የጋብቻ ውል ሲፈረም ቀደም ብሎ ያፈሩት ወይም በውርስ ያገኙት ንብረት የጋራ እንዳይደለ ነገር ግን ከተጋቡበት ጊዜ አንስቶ በጋራ ያፈሩት ገንዘብና ንብረት ብቻ የጋራ እንደሚሆን በመተማመን መፈራረም ነው። ከጋብቻ በፊት በአጭር ጊዜ በሥራና በንግድ ውጤታማ በመሆን ያፈሩት፣ ከቤተሰብና ከሌሎች ቅርብ ከሆኑ ግለሰቦች በውርስ ያገኙት ንብረት ሲኖር፣ ከጥንዶቹ አንዱ ወይም ሁለቱም አስቀድመው ሌላ ጋብቻ የነበራቸውና ከቀድሞ የትዳር አጋሮቻቸው ጋር በመሆን ያፈሩት ሀብት ሲኖርና ከቀድሞው ትዳራቸው የተወለዱ ልጆች በውርሱ

የተካተቱ ሲሆን ወ.ዘ.ተ የልጆችን መብት ለመጠበቅ ወይም 'ንብረት'ን ለመጠበቅ ሲባል እንዲህ ዓይነቱን እርምጃ ለመውሰድ ይገደዳሉ።

እንዲህ ዓይነቱን አስቀድሞ መፈራረም የሚፈልጉበት ምክንያት አላቸው:: የመጀመሪያው ምክንያታቸው ባላቸው የግል የንግድ ድርጅት ከስረት እንዳይገጥማቸውና በከስ ወደ ሌላ ክስረት እንዳይገቡ በማሰብ ነው። ሌላው ወደ ትዳር የሚገቡ ሰዎች ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት በትዳር ውስጥ ለትዳር አጋር ታማኝ ባለመሆን በዝሙትና እንዲሁ የትዳርን አጋር ትቶ በመሄድ ወቅት ከሚፈጠር ችግር ንብረትን ለመከላከልና ለመጠበቅ ይረዳል ብለው ስለሚያስቡ ነው። አንዳንድ ሰዎች ከሚያገቡት ሰው ይልቅ ያላቸውን ንብረት በማየት ከእነርሱ ዕድሜና ስብዕና ጋርና ሌሎች ከየራሳቸው መለኪያ ጋር የማይመጣጠን ሁኔታ እንዳለ እያወቁና እየታወቀ እንዲሁ በጊዜው በገንዘብ በታወረ አእምሯቸው ወደ ትዳር የሚገቡና ከፉ ምኞታቸውን ለመፈጸም የሚፈልጉ ሰዎች ከሚፈጥሯቸው ችግሮች ራሳቸውን ለመከላከል በማሰብ ይህን ያደርጋሉ።

ከእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ጋር የተያያዘውን ችግር በሁለት አቅጣጫ ልንተረጉመው እንችላለን። የመጀመሪያው ባለሃብት የሆነው አካል በገንዘቡ የፈለገውን ማድረግ እንደሚችልና የትዳር አጋር መግዛትና መቆጣጠር እንደሚችል በማሰብና ለእርሱ ጥሩ አጋር የምትሆን አቻ ሚስት በማግባት ፋንታ ሚስትን ባለሃብቷ ሴት ከሆነች ደግሞ ባልን ከብዙ ሰዎች መካከል መርጠው ለማግባትና የግል ንብረታቸው ለማድረግ በማሰብ የትዳር ጓደኛ ግዥ መፈጸማቸው ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ችግር አንዳንድ በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ሀበሻ አገር ቤት በመሄድ ባጭር ጊዜ የትዳር ጓደኛ ፈልጎ ወይም አስፈልጎ ጋብቻ በመፈጸም ትዳርን ለመመስረት የሚደረጉ ጥረቶች በምሳሌነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል ዋነኛዎቹ ናቸው። ተፈልጎ የተገኘው ወገን ደግሞ ገንዘብና ንብረትን ወይም በትዳር ሰበብ ወደ ውጭ አገር መውጣትን ብቻ በማየትና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ራሱን ለሽያጭ ያቀርባል:: በዚህ መንገድ የሚደረጉ ትዳሮች በአብዛኛው ስጋት የሞላባቸው የትዳር ስምምነቶች በመሆን መቀጠላቸውና ስጋቶቹም የተመሠረተውን ትዳር በአጭር ጊዜ እንዲፈርስ የሚያደርጉ የጤነኛ ትዳር እንቅፋቶች መሆናቸውን ለአንባቢ ለማስረዳት መሞከር ለቀባሪ እንደማርዳት የሚቆጠር ይመስለኛል።

ሌላው ባለጠጋ ወይም ባለንብረት የሆኑ ሰዎች በሚያገቡበት ወቅት ለትዳር የሚያስቧቸውን ወገኖች ለትዳር የሚያነሣሣቸው ፍቅር እንጅ ገንዘብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ሂደቱ በትክክለኛው መንገድ ካልተፈጸመ እንዲህ ዓይነቱ ድርጊት በአብዛኛው ውሎ አድሮ ጥንዶችን ለፍች የሚያነሳሳና የሚያዘጋጅ ነው። በሌላ በኩል ባለሃብት የሆነው የትዳር ጓደኛ ደግሞ በአብዛኛው የገንዘብ አቅም ለሌለው የትዳር አጋር የማያስብ እንዲሁም የማይጠነቀቅ እንዳይሆንና ራስ ወዳድነት የተሞላው





አካሄድ በመሄድ በትዳር ውስጥ ለሚፈጠር ስምምነት እንቅፋት እንዳያስቀምጥ ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ለማስተናገድ የማይፈቅድ፣ መበለጥን የሚፈራና ግትር አቋም ያለው መሆንና አለመሆኑ ላይ ራሱን መመርመርና ማስተካከል ይጠበቅበታል። ክርስቲያናዊ ትዳር ሁለንተናዊ መሰጠት ያለበት የዕድሜ ልክ ቃል-ኪዳናዊ ትሥሥር መሆኑን ከማሳየትና ከማስለመድ ይልቅ ጊዜያዊ የሆኑ ጥቅሞችና መብቶች ላይ በማተኮር ጊዜያዊ ኮንትራትና ስምምነት እንዳናደርገው በትዳር ውስጥ ያለን ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል በተገራና በሰለጠነ አስተሳሰብና ስብዕና የተለወጠ ማንነት ሊኖረን ይገባል።

## III. በገንዘብና በንብረት ምክንያት ለሚፈጠሩ ግጭቶች መፍትሔዎች

### 1. መቀየር፡-በገንዘብ ላይ ያለንን ትክክለኛ ያልሆነ አስተሳሰብና እምነትን መቀየር

በክርስቲያን ባለትዳሮች መካከል ገንዘብን በጋራ ማስተዳደርና መጠቀም ጥንዶቹ አንድነታቸውን ከሚገልጹበት መንገድ አንዱ ነው። ገንዘብ የምንጠቀምበት መሣሪያ እንጂ በመኖሩ ብቻ ደስታ የሚፈጥር የደስታ ምንጭ እንደሆነ አድርጎ ማሰብንና ገንዘብን አግባብ በአልሆነ መንገድ መውደድን ማስወገድ ተገቢ ነው። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ስር መሆኑን በመገንዘብ አእምሮንና ልብን መጠበቅ ከተለያየ ከፉ አደጋ ሕይወታችንና ትዳራችንን ይጠብቃል። መጽሐፍ ቅዱስ *"ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።"* /1ኛጢሞ 6:10/ እያለ እንደሚመሰከረውም ሕይወታችንንና ትዳራችንንም ብዙ ዓይነት ስቃይ ውስጥ ይጥለዋል:: የእግዚአብሔር ቃል በዕብ 13:5 *"አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤"* በማለት የሚሰጠውን ምክር በመስማትና በመታዘዝ ክርስቲያን ባለትዳሮች ትዳራቸውንና አካሄዳቸውን ገንዘብን ባለመውደድ ሊመሩትና ሊያስተዳድሩት ይገባል::

ገንዘብን መውደድና ለገንዘብ ባሪያ መሆን የክርስቲያን ባለትዳር ባህርይ ሊሆን እንደማይገባ መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች የቅዱሳት መጽሐፍት ክፍሎችም አስረግጦ ይመክረናል /ማቴ. 6:24/። በመጨረሻው ዘመን ሰዎች ስለሚወዱት ነገር ሲናገር *"... ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ... ገንዘብን የሚወዱ..."* እንደሚሆኑ ሐዋሪያው ጳውሎስ ሁላችንን ያስጠነቅቃል /2ኛጢሞ. 3: 2/። ደግሞም እንዲሁ ሳይሠሩ በሰው ትከሻ ለመኖር መፈልግና ጥረት ማድረግም ሌላው ለውጥ የሚያሻው ክርስቲያናዊ ያልሆነ አመለካከት መሆኑን *"ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ።"* /2ኛተሰ.3: 10-13/ የሚለው እውነት ያረጋግጥልናል::

## 2. መገንዘብ፡-ገንዘብን ማግኘት እንድንችል ችሎታን የሰጠን እግዚአብሔር እንደሆነ መገንዘብ

እግዚአብሔር ከፍጥረት ጀምሮና ዳግም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ሥራ ሰውን በመዋጀት የራሱ አድርጎናል። ከዚህ ትልቅ የማዳን ሥራው ባሻገር ለሰው እውቀትን፣ ችሎታንና ልዩ ልዩ ጥበብን የሰጠው እግዚአብሔር ነው:: *"በልብህም ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን ሀብት አመጣልኝ አንዳትል። ነገር ግን ዛሬ እንደ ሆነ ለአባቶችህ የሚለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ፥ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ።"* **/ዘዳ8:17-18 የዳዊት/** ዘማሪው በጉባኤ ስለእግዚአብሔርና ስለሥራው ብሎም የብልጥግናው ምንጭ እግዚአብሔር ስለመሆኑ እውቅና እየሰጠ ሲጸልይ ማየት ልንይዘው የሚገባንን አቋም የሚያሳይ ትልቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ነው። *"ዳዊትም በጉባኤው ሁሉ ፊት እግዚአብሔርን ባረከ ዳዊትም አለ። አቤቱ፥ የአባታችን የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ተባረክ። አቤቱ፥ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና ታላቅነትና ኃይል፥ ክብርም፥ ድልና ግርማ ለአንተ ነው:: አቤቱ፥ መንግሥት የአንተ ነው፥ አንተም በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያልህ ራስ ነህ። ባለጠግነትና ክብር ከአንተ ዘንድ ነው፥ አንተም ሁሉን ትገዛለህ ኃይልና ብርታት በእጅህ ነው ታላቅ ለማድረግ፥ ለሁሉም ኃይልን ለመስጠት በእጅህ ነው።* **/1ኛ ዜና 29: 10-12፤ ምሳሌ 10: 22 እና 1ኛቆሮ 4: 7/**

## 3. መረዳት፡- ያለን ሁሉ የእግዚአብሔር እንደሆነም መረዳት

የእግዚአብሔር ቃል *"ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥ ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።"* **/መዝ 24: 1/** እንደሚል በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ነው:: ታላቅነትና ኃይል፣ ድልና ግርማ፣ መንግሥት ሁሉ የእርሱ ነው:: በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያለ ራስ እግዚአብሔር ነው:: ባለጠግነትና ክብር ከእርሱ ዘንድ ነው:: እርሱ ሁሉን የሚገዛ፤ ኃይልና ብርታት በእጁ የሆነና ቅዱስ ቃሉ እንደሚያስረግጠው ለሁሉም ኃይል ለመስጠት በእጁ ነው። የእኛ የምንለው አንዳች ነገር የለንም ያለን ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ነው:: እኛም እራሳችን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም የተገዛን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን **/1ኛቆሮ 6: 17-18/**::

እኛና የእኛ የምንለው ሁሉ የእኛ ካልሆነ ሃብታችንን መታበያችንና ለትዳራችን የግጭት ምክንያት ማድረጉን ትተን ሰላም ያለበትን መንገድ እንድንፈልግ ቃሉ ያሳስበናል። ወደዚህ ምድር ስንመጣ ምንም ይዘን አልመጣንም ደግሞም ወደ አምላካችን ስንሄድ ምንም ይዘን ልንሄድ አንችልም። በምድር ለዘላለም ልንኖር ሳይሆን እንደ እንግዶችና ምጻተኞች እንድንኖር መጠራታችንን አንርሳ!! *"... እንዲህም አለ፦ ራቁቴን ከእናቴ ማኅፀን ወጥቻለሁ፥ ራቁቴንም ወደዚያ እመለሳለሁ እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔርም ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።"* **/ኢዮብ 1: 21/**::





## 4. መምረጥ፡- ከብርና ከወርቅ የሚበልጡና የከበሩ ነገሮችን እንዳሉ መረዳትና መምረጥ

እንደ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ዕለት በዕለት የሕይወት መመሪያ አድረገን የምንቀበል ከሆነ ቃሉ ከብርና ከወርቅ የሚበልጡ የከበሩ ነገሮች እንዳሉ ያሳየናል። በትዳራችን ጤነኛና ደስተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳይኖረን እንቅፋት ከሚሆንብን ከገንዘብ፣ ከብርና ከወርቅ ይልቅ የትዳር አጋራችን ሕይወትና ነፍስ ይበልጣል። **(ማቴ 16: 26፤ ሉቃ 12: 15)**

በዘመናት ሁሉ ታላቅና የተፈራ የባለጠግነት ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን በመፍራትና በፍቅር በጥቂት ነገር በድህነት መኖር ብዙ ሀብት በሞላበት ነገር ግን የእግዚአብሔር ህልውና በማይገኝበት እንዲሁም የሰላምና የፍቅር ሕይወት ባዶነት ባለበት ከመኖር ይበልጣል፡- *"እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር ሁከት ካለበት ከብዙ መዝገብ ይሻላል። የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል።"* **/ምሳሌ 15: 16-17/**:: በአቋራጭ በመበልጠግ፣ በአመጽ ከሚገኝ ብዙ ብልጥግና ይልቅ በጽድቅ የሚገኝ ጥቂት ነገር ይበልጣል **/ምሳሌ 16: 8/**::

ጥበብና ማስተዋልን ማግኘት **/ምሳሌ 16: 16/** ፣ መልካም ስምና ሞገስ **/ምሳሌ 22: 1/**፣ በሰማይ ሀብት ያለው መሆኑን የተረዳ ሰው መሆን **/ማቴ 6: 19-20/**፤ እግዚአብሔርን መምሰል **/1ኛጢሞ 6: 6ና 9/**፣ የማይታበዩና የማያልፍ ባለጠግነትን ተስፋ የሚያደርጉ መሆን **/1ኛጢሞ 6: 17-19/**፣ ለእኛ ረብ የሚመስለንን ነገር ሁሉ ስለክርስቶስ ጉዳት አድርጎ የመቁጠርን ሕይወት የሚለማመድ **/ፊል 3: 7-9/**፤ የእግዚአብሔርን የአፉን ቃል (ሕግ) ማወቅ **/መዝ 19: 9-10፤ 119: 72/**፣ በአፉ ከሚወሳልት ከሰነፍ ሰው ይልቅ ያለ ነውር የሚሄድ ድሃ ሰው የሚሻል እንደሆነ መረዳት **/ምሳሌ 19: 1/**፣ የተመሰገኑ ልባምና አስተዋይ ባለትዳሮች መሆን **/ምሳሌ 31: 10፤ ምሳሌ 19: 14/** እና መንግሥቱንና ጽድቁን የሚያስቀድሙ አማኞች መሆን ከዚህ መርህ ውጭ በሆነ የተቃወሰ ኑሮ ውስጥ ከሚገኝ ከማናቸውም ስኬት የተባለ ነገር ሁሉ ይበልጣል **/ማቴ 6: 33/**::

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር በጋራ ቃሉ የሚያስበልጠውን አብልጦ መውደድ፣ የሚሻለውን መምረጥ፣ የሚቀድመውን ማስቀደም፣ የከበረውን አክብሮ መያዝ፣ እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚጠላውን ለይቶ መምረጥና ተጠንቅቆ መያዝ ለዘላለም ሕይወት ጉዞ፣ ጤነኛና ደስተኛ ለሆነ የትዳር ሕይወት፣ መንፈሳዊ እሴቶችን የሚከተልና የሚያከብር ቤተሰብ ለመመስረት የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው *"የሚበልጥና ለዘወትር የሚኖር ገንዘብ በሰማይ ራሳችሁ እንዳላችሁ አውቃችሁ፥ በእስራቴ ራራችሁልኝ የገንዘባችሁንም ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ። እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና።"* **/ዕብ 10: 34-36/**::

## 5. መኖር፡- በጋራ በመነጋገርና በመግባባት መኖር

አለመግባባትንና ግጭትን ለመቀነስ በጋራ ለኑሯችን ስንት ማውጣት እንደሚኖርብን በመነጋገር ገቢና ወጭን መቆጣጠር ተገቢ ነው። ሥርተን ከምናስገባው ያነሰ የወጭ ባጀትን ማቀድና ለወጭአችን ገቢያችንን መሠረት ያደረገ ገደብ (ልክ) ማስቀመጥ ባቀድነው ለመኖርና በዕቅዳች ለመቀጠል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ በጋራ ራሳችንን በዚህ መርህ ለመኖር በማስለመድ መግባባትን የትዳራችን ጣዕም ልናደርገው ይገባል፡፡ ለተለየ ለውጥ ከፍት በመሆን ወጭን በመቆጣጠር ሊፈጠር ያለን ውጥረትና ግጭት መቀነስ ተገቢ ነው። በጋራ በመነጋገር ባጀትን መበጀትን መለማመድ፣ ብድርን ለማቆም ዝርዝር ማውጣት፣ ስልቶችን መቀየስና በቀላሉ ወይም አባካኝ በሆነ መንገድ ወጭን ማውጣትን ለማስወገድ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ የእርስ በርሳችንን ደስታና የትዳራችንን መልካም ግንኙነት ለመጠበቅ ይረዳል።

እንደገና በፈተና ላለመውደቅ ገንዘብን እንደ አስፈላጊ መሳሪያ እንጅ እንደ ደስታ ፈጣሪ አለመመልከት፣ ወጭን በመቀነስ ሂደት እድገትን መጠበቅ /**ሮሜ 5፡ 3-4/**፣ በፈተና ለሚወድቀው የትዳር አጋር ይቅርታን እየሰጠን መተማመንን ማዳበር፣ አስፈላጊ የሆኑ ወጭዎቻችንን መጻፍ፣ ያለ ዓላማ ማውጣትን ማስወገድ፣ ገቢያችንን ከወጭአችን ጋር ትክክለኛ በሆነ መንገድ ማወዳደር፣ አቅማችንን ግምት ውስጥ ያስገባ የዕቃ ግዥ ማካሄድና ውጥረትንና ግጭትን በመቀነስ የትዳርን ደስታ መጨመር አስፈላጊ ነው።

## 6. መሥራት፡- ሥራን ያለመውደድና የመናቅ ልማድን ማስቀረት

እንደ ክርስቲያን ባለትዳር እርስ በእርስ በኑሮ መደጋገፍ አንዱ የባለትዳሮች ኃላፊነት ነው። አንደኛው የትዳር አጋር ሥራ ባይኖረውና ሥራን የሚጠላ ሳይሆን መሥራት የማይችልበት ሁኔታ ላይ የሚገኝ ቢሆን ሌላው የትዳር አካል አእምሮውን በበጎ አመለካከት በማነጽ የተፈጠረውን ከፍተት በትህትናና በኃላፊነት ስሜት መሸፈን ይጠበቅበታል፡፡ ሥራ መሥራት ባለመቻልና ሥራ ባለመውደድ መካከል ከፍተኛ የትርጉም ልዩነት አለ። ሥራ መሥራት አለመቻል በጤንነት ችግር፣ ለጊዜው ሥራ ባለማግኘትና ከሥራ በመውጣት ምክንያት ሊፈጠር የሚችል አንዱ የግለሰቦች፣ የባለትዳሮች፣ የቤተሰብና የማሕበረሰብ ችግር ነው። እንዲህ ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ግለሰቦች፣ ባለ ትዳሮችና በአጠቃላይ ክርስቲያኑ ማሕበረሰብ ወይም በአጠቃላይ ማሕበረሰቡ ጭምር አንዱ የሌላውን ሸክም የመጋራትና የመደጋገፍን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ መተግበርን መለማመድ ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን ብዙ የሥራ አማራጮች እያሉ ሥራ መሥራትን ባለመውደድ ብዙ ሰበቦችን እየደረደሩ ራስን ሥራ ከመሥራት ተፈጥሯዊ፣ ክርስቲያናዊ፣ ግላዊ፣ ቤተሰባዊና ማሕበራዊ ኃላፊነት ማራቅ በየትኛውም መለኪያ ሊበረታታ የማይችል መለወጥ ያለበት ችግር ነው፡፡ ይህ ችግር በትዳር ውስጥ የከፋ አለመግባባትና ግጭት ከሚፈጥሩ ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው፡፡





ብዙ የሥራ ዕድሎች እያሉ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆንና ሥራን አለመውደድ በትዳር ውስጥ የቀውስ መፈጠር መንስኤ ከመሆኑም ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስ የሚቃወመው ተግባርም ነው። *"ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘዝናችሁ ነበርና።ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ።"* /**ኛተሰ 3፡ 10-13/**፡፡ ስለዚህ ሥራን አለመውደድ ሊወገዝና ከማናችንም በተለይም የትዳርን ኃላፊነት ከተሸከምን ወገኖች ሕይወት ፈጽሞ ሊወገድ የሚገባው ልምምድ ነው።

## 7. መጣር፡- ለቁሳቁስ መጨነቅን ለማስወገድ መጣር

ከሌሎች ሰዎች ጋር መወዳደርና እኩል ለመሆን ከተቻለም በልጦ ለመገኘት የባልጀራን ገንዘብና ንብረት መመኘት የተከለከለ መሆኑን *"የባልጀራህን ሚስት አትመኝ የባልንጀራህንም ቤት እርሻውንም ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም፥ ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።"* /**ዘዳ 5፡ 21/** በማለት ቃለ እግዚአብሔር ይነግረናል። ከፉ ምኞት፣ ጣዖትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ከሕይወታችን ሊወገድ የሚገባው ነው /**ቆላ 3፡ 5/**፡፡ አረማመዳችንን ገንዘብን ባለመውደድ ማድረግ አለብን /**ዕብ 13፡ 5/**፡፡ የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ከመጎምጀትም ሁሉ በመራቅ ራስን ከኃጢአት በመጠበቅ /**ሉቃ 12፡ 15/** ስለሚበላና ስለሚለበስ እንዳንጨነቅ ቃሉ ይመከረናል /**ማቴ 6፡ 25፣ 31፣ 34/**፡፡ በዚህ እውነት ላይ በመመሥረት ለቁሳቁስ ከመጨነቅ ይልቅ ትዳር ከገንዘብ የሚበልጥ ኃላፊነት መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በከፉ ምኞት ላለመጠመድ ያለኝ ይበቃኛል የሚል መርህን መከተል ደግሞም በከፉ ምርጫና ውሳኔ እንዳንወሰድ የከበረውን ከተዋረደው በመለየት መምረጥ አስተዋይነት ነው፡፡ የገንዘብ ፍቅር ለሌሎች ከፉ አመጾች አልፎ የመስጠት መንገድ መሆኑን በመገንዘብ ከዚህ መራቅ ጠቢብነት ነው፡፡ በአጠቃላይ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁህ ነው ለሚለው አምላካዊ መርህ በመገዛት መስጠትና ማካፈልን መልመድ፣ለጌታና ለትዳር አጋር ፍቅር መጠንቀቅ ላይ በማተኮር በማግኘትና በማጣት ውስጥም ታማኝ ልንሆንለት የገነባነውን የጋብቻ ቃል ኪዳን ማሰብና መጠበቅ የክርስቲያን ባለትዳሮች የሕይወት ዘመን ኃላፊነት ነው።

## ለጥንዶች በግላቸውና በቡድን ለማጥናት የሚረዷቸው የውይይት ጥያቄዎች

## የምዕራፍ ስምንት (8)

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን የአይታ ልዩነትና አንድነት በመዘርዘር ተወያዩበት::
2. በገንዘብና በንብረት ላይ ያላችሁን ልዩነት ለማጥበብና አንድነታቹህ ላይ በጋራ አጠናክሮ ለመቀጠል ምን ማድረግ አለብን ትላላችሁ?
3. የጋራ የሆነ ገንዘብና ንብረት በፍጹም ግልጥነትና ነፃነት እየተጠቀማችሁ ነውን? ካልሆነ ችግሩ ምንድን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ ከገንዘብና ከንብረት ይልቅ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጣቸውን የከበሩ ነገሮች በመዘርዘር ተወያዩባቸው::
5. እንደ ክርስቲያን ባለትዳር ገንዘብን በጋራ እንዴት እንደምታስተዳድሩና እንደምትጠቀሙበት በፍጹም ግልጥነት፣ ነፃነት በተሞላውና የለውጥ እርምጃ ለመውሰድ በተዘጋጀ አቋም ተወያዩ::
6. በእናንተ ቤት ከገንዘብና ከንብረት ጋር ተያይዞ የተፈጠረና ሊፈጠር የሚችል ግጭት አለን? ካለ በምን ምክንያት ተፈጠረ? ግጭቱን ለመፍታትስ ምን እርምጃ መውሰድ አለብን ትላላችሁ?
7. በገንዘብና በንብረት ምክንያት በትዳራችሁ ግጭት እንዳይፈጠር አስቀድሞ የመከላከያ እርምጃ ለመውሰድ ከወዲሁ በመመካከር ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ አቅዱ::





## ምዕራፍ ዘጠኝ(9)

## የግብረ ስጋ ግንኙነት

### I. የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንነት በትዳር ውስጥ

የግብረ ስጋ ግንኙነት ወይም ሩካቤ ስጋ ማለት ባለትዳር በሆኑ ጥንዶች መካከል ማለትም በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ለጠለቀ ግንኙነት፣ ለስሜት እርካታና ልጅን ለመውለድ የሚደረግ አካላዊ ወይም ወሲባዊ ግንኙነት ነው:: የግብረ ስጋ ፍላጎትን በማሟላት ፍቅርን የመሥራት ወይም የመገንባት ሂደት ነው። በትዳር በኩል የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት የከበረ፣ ንጹህ፣ አርኪና ለባለትዳሮች የተፈቀደ ነው። (ዕብ13፡4) በክርስቲያን ባለትዳሮ መካከል ችግሮችና አለመግባባቶች እንዲፈጠሩ ከሚያደርጉ ምክንያት አንዱ በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣምና አለመርካት ወይም መልካም የሆነ ግንኙነት አለመኖር ነው። በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ራሱን የቻለ ያለመግባባት መንስኤ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በትዳር መካከል የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን የሚያባብስ አቀጣጣይ የመሆን ሚናም ይጫወታል:: በግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም የሚፈጠሩ ችግሮች ግለት ቶሎ እንዳይበርድ የሚያደርግና ቀስ በቀስም የትዳርን ህልውና የሚያጠፉ የተዳፈነ እሳት ሊሆን ይችላል።

ከባህላችን ተጽዕኖ የተነሳ በትዳር ውስጥ ፍላጎታችንና ችግራችንን በፍጹም ግልጥነት የማናወራበትና የማንወያይበት ጉዳይ ቢኖር የግብረ ስጋ ግንኙነት ነው። የጋብቻ አስተማሪዎችም ሆንን አማካሪዎች እንደ ሌሎች ችግሮች በድፍረት የማናስተምርበትና የማናማክርበት ርዕሰ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ችግሩ ከመቹውም በበለጠ እየጨመረና እየተባባሰ በመምጣቱ ብዙዎች ለአለመግባባት፣ ለመለያየትና ለፍች ተጋላጭ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል።

በትዳር ላይ የሚፈጠር የግብረ ስጋ ግንኙነት አለመጣጣም ችግር ጥንዶቹ ሊያስተካክሉት ፍላጎት ካላቸውና ተገቢ ጥረት ካደረጉ በሂደት ሊቀንስ ይችላል:: እንደገናም በተለያዩ እርዳታዎችና ሕክምናዎች የመሻሻልና የመስተካከል ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ልንገነዘብ ይገባል። ያላገቡና ሊያገቡ እየተዘጋጁ ያሉ እንዲህ ዓይነቱን ችግር በመፍራት ከጋብቻ በፊት መሞካከርና ወሲብ መፈጸም ዝሙት የሆነ ኃጢአት እንደሆነ ሊያውቁት ይገባል። በትዳር ውስጥ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፍላጎትና ድርጊት አንዱ የጋብቻ ክፍል እንጂ የትዳር ሁሉ ነገር አድርገን ከማሰብ መቆጠብና ሌላው የትዳር ገጽታ የሚጠይቀውን የሁለትዮሽ መሰጠት፣ መተሳሰብና መረዳዳት መዘንጋት አይገባንም። በሌሎች ጉዳዮች ላይ ስንተሳሰብና ስንረዳዳ በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ ወደ መጣጣም መምጣት የሚያስችለንን መልካም ስሜት መፍጠርና ማሳደግ እንችላለን::

ከችግሩ ጥልቀት፣ አሳሳቢነትና በክርስቲያኖች ትዳር ላይ ከሚፈጥረው አሉታዊ ተጽዕኖ የተነሳ እንደ ባለትዳር በግልጥነት ልንነጋገርበት ይገባል። በርዕሰ ጉዳዩ ላይ